# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

81ኛ ዓመት ቁጥር 300 ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!










# ምክር ቤቱ በዜጎች ላይ የደረሰውን ጭፍጨፋ የሚያጣራ ኮሚቴ እንዲቋቋም

**አብዱረዛቅ መሐመድ**

አዲስ አበባ፡- የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በንፁሓን ዜጎች ላይ የተፈፀሙ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶችን የሚያጣራና ቀጣይ ለሚወሰዱ እርምጃዎች ምክረ ሀሳብ የሚያቀርብ ልዩ ኮሚቴ እንዲቋቋም ወሰኗል።

ምክር ቤቱ ትናንት ባካሄደው አንደኛ የሥራ ዘመን ስድስተኛ ልዩ ስብሰባው በኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በአማራ፣ በአፋር እና በተለያዩ የሀገራችን

ምክር ቤቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ ፡- ኢዮብ ተፈሪ

# ሕወሓት ያመከናቸውን የሰላም እድሎች በመገምገም አሁን በተሰጠው የሰላም እድል እንዲጠቀም ጥሪ ቀረበ

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- ሕወሓት በተደጋጋሚ አግኝቶ ያመከናቸውን የሰላም እድሎች ዞር ብሎ በማየትና በመገምገም አሁን የተሰጠውን የሰላም እድል ሊጠቀምበት ይገባል ሲሉ ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል ገለጹ።አሁን በመንግሥት በኩል የቀረበውን ጥሪ ተቀብሎ ሕዝቡን ከመከራና ስቃይ እንዲያወጣም ጠይቀዋል፡፡

ሕወሐት ያመከናቸውን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በኦሮሚያ ክልል የተፈፀሙ አሰቃቂ ጭፍጨፋዎችን የሚመረምር ልዩ አቃቤ ሕግ በአዋጅ እንዲቋቋም አብን ጠየቀ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- አብን ሰሞኑን በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ አካባቢዎች በንጹሓን ዜጎች ላይ የተፈፀሙ አሰቃቂ ጭፍጨፋዎችን የሚመረምር ልዩ አቃቤ ሕግ በአዋጅ እንዲቋቋም ጠየቀ። የኢትዮጵያን ሰላም የሚፈልግ አካል ሁሉ በአማራ ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን ጭፍጨፋ ለማስቆም ሊሠራ እንደሚገባም አሳሰቧል።

በኦሮሚያ ክልል ባለፉት አራት ዓመታት ማንነትን መሠረት በማድረግ በአማራ ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን ጥቃት ለማስቆም የኢትዮጵያን ሰላም የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሊሠራ እንደሚገባ የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ ጠየቀ።

የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ትናንት በሰጠው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ ባለፉት ዓመታት በተሠራው የተሳሳተና የሐሰት ትርክት በአማራ ሕዝብ ላይ የተቀናጀ ጭፍጨፋ ሲካሄድ ቆይቷል ብሏል።

የአብን ሊቀመንበር ዶክተር በለጠ ሞላ እንደገለጹት፤ የአማራ ሕዝብ በአገር ግንባታ ላይ ከሌሎች ኢትዮጵያዊ ወንድሞቹ ጋር የበኩሉን ድርሻ የተወጣ ሕዝብ ነው።



ፎቶ ፡- ኢዮብ ተፈሪ

የአብን አመራሮች ጋዜጣዊ መግለጫ

ሆኖም ግን አማራ ጠል ኃይሎች ከውስጥም ከውጭም ሕዝቡን እንደ ጠላት በመፈረጅ በከፍተኛ ሁኔታ ሲጎዱት ቆይተዋል። ፍረጃው በታሪክ ሂደት በመዋቅርና ሥርዓት ተበጅቶለት ሕግ ሆኖ ሕዝቡን በተለየ ሁኔታ ሲጎዳ የቆየ ነው። ከ1983 ጀምሮ እስካሁን ድረስ ሕዝቡን

በኦሮሚያ ክልል የተፈፀሙ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# «ከሕወሓት በስተጀርባ ያለውን የሶስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት ለተባበሩት መንግሥታት ማሳወቅ ይገባል»

-ዶክተር ወሂበእግዚር ፈረደ
የፖለቲካ ተንታኝ

ገጽ 4







# ኮሚሽኑ በነዋሪዎች ላይ እየደረሰ ያለው ብሔር ተኮር ግድያ በአስቸኳይ እንዲቆም አሳሰበ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን በዜጎች ላይ እየደረሰ ያለው ብሔር ተኮር ግድያ በአስቸኳይ እንዲቆም ጥሪ አሳሰበ።

ኮሚሽኑ በማኅበራዊ ትስስር ገጹ ላይ እንደገለጸው፤ በኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ ዞን ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ ሰዎች ማንነትን መሠረት ያደረገ በተባለ ጥቃት ተጨፍጭፈዋል።

ኮሚሽኑ በኦሮሚያ ክልል ሃዋ ገላን ወረዳ በቄለም ወለጋ ዞን መንደር 20 እና መንደር 21 ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ ሰዎች ስለመጭፍጨፋቸው መረጃ ደርሶኛል ብሏል።

ኮሚሽኑ እንዳለው ያነጋገራቸው ከጥቃቱ የተረፉ ከአካባቢው የሸሹ ሰዎች ግድያው ሰኔ 27 ቀን 2014 ዓ.ም ማለዳ መጀመሩን ጠቅሶ ነፍሰ ገዳዮቹም የኦሮሞ ነፃነት ጦር ወይም መንግሥት ሸኔ የሚለው ቡድን አባላት መሆናቸውን ተናግረዋል።

ኢሰመኮ ግድያው የተፈጸመበት የመንደር 20 እና የመንደር 21 ነዋሪዎች በዋነኛነት የአማራ ተወላጆች መሆናቸውን መረዳቱንም ገልጿል።

የመንግሥት ፀጥታ ኃይሎች ከአዲስ አበባ 400 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው በዚህ ስፍራ ደርሰዋል ቢባልም ነዋሪዎች አሁንም መጠለያ ፍለጋ ላይ ናቸው ብሏል።

የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ወደ አካባቢው መድረሳቸው ተነግሯል ያለው ኢሰመኮ ነዋሪዎቹ ግን ወደ ሌላ ቦታ ሄደው መጠለላቸውን ቀጥለዋል ሲል ሁኔታውን አስረድቷል።

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ዶ/ር ዳንኤል በቀለ " በአካባቢው የቀጠለው የጸጥታ ችግር እና በነዋሪዎች ላይ እየደረሰ ያለው ብሔር ተኮር ግድያ በአስቸኳይ መቆም አለበት " ሲሉ አሳስበዋል።

በአካባቢው ሊፈጸም የሚችል ተጨማሪ «የሲቪሎች» ግድያን ለመከላከልም የመንግሥት ጸጥታ ኃይሎች በአስቸኳይ በአካባቢው እንዲሰማሩም ጥሪ አቅርበዋል።

# «የትጥቅ ትግል የሚያካሄዱ ኃይሎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሰላማዊ ትግልን ምርጫቸው ማድረግ አለባቸው»

-አቶ አራርሶ ቢቂላ
የኦነግ ሊቀመንበር

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- በትጥቅ ትግል የሚታገሉ ኃይሎች ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሰላማዊ ትግልን መከተል እንዳለባቸው የኦሮሞ ነጻነት ግንባር(ኦነግ) አስታወቀ ።በትጥቅ ትግል ስም በሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን እኩይ ተግባር አውግዘዋል።

የኦነግ ሊቀመንበር አቶ አራርሶ ቢቂላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ትጥቅ ትግል በሚካሄድበት ጊዜ በመሐል በሠላማዊ ዜጎች ላይ ጉዳት እየደረሰ በመሆኑ በትጥቅ ትግል የሚታገሉ ኃይሎች ለሕዝባቸው ጥቅም ሲባል ሰላማዊ ትግልን ምርጫቸው ማድረግ አለባቸው።

በአሁኑ ወቅት የኦሮሞን ሕዝብ ጥያቄ ለመመለስ ትጥቅ ትግል ውስጥ የሚያስገባ ሁኔታ የለም ያሉት አቶ አራርሶ፤ በሕዝብ ትግል የተገኘውን ድል መጠበቅ እንደሚገባም ገልጸዋል።

እንደ አቶ አራርሶ ገለጻ በአሁኑ ወቅት የክልሉ ሕዝብና በክልሉ ውስጥ አብረው በሚኖሩ ሕዝቦች ላይ ጉዳት እየደረሰ ስለሚገኝ የድርጊቱ ፈጻሚዎች ከዚህ ድርጊታቸው ሊታቀቡ ይገባል።

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ወደ ትጥቅ ትግል የገባው ባለፉት ሥርዓቶች በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ሲደርስ የነበረውን በደል ለመታገል ለረጅም ዘመናት ትጥቅ ትግል ውስጥ ቆይቷል ያሉት አቶ አራርሶ፤ ግንባሩ ለውጡን ተከትሎ ከኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግሥት ጋር ተወያይቶ ሀገር ውስጥ ሲገባ ያልተመለሱ የኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄዎችን በሰላማዊ ትግል ታግሎ ለመመለስ የሚያስችል ሁኔታዎች በመፈጠራቸው ነው ብለዋል።

ግንባሩ ሀገር ውስጥ ገብቶ በሰላማዊ ትግል ለመታገል መወሰኑ ሀገሪቱን ካለችበት ጦርነትና ግጭት አዙሪት በማላቀቅ የሕዝቦችን ጥቅም ለማስጠበቅ ጉልህ ሚና እንዳለውም ገልጸዋል።

የኦሮሞ ሕዝብ ትላንት የተነፈገውን ዕድል ለማግኘት ዛሬ በሩ ክፍት ነው ያሉት አቶ አራርሶ፤ አሁን የተገኘው ሠላማዊ ትግል ዕድል በገዳ ሥርዓት ተቀባይነት ያለው መሆኑንም አብራርተዋል።

ወንድም ወንድሙን ለመግደል ታጥቆ ፤እርስ በእርስ በመከፋፈል መወነጃጀል የኦሮሞ ባህል አይደለም ያሉት አቶ አራርሶ፤ በትጥቅ ትግል ምክንያት የክልሉ ሠላምና ጸጥታ ችግር ተማሪው፣ ነጋዴውንና አርሶ አደሩን ከሥራው በማስተጓጎል ከቀያቸው እንዲፈናቀሉ በማድረግ ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እየዳረገ ይገኛል ብለዋል።

የኦሮሞን ሕዝብ ለትጥቅ ትግል የሚያበቃው ጥያቄ የለም ያሉት አቶ አራርሶ ያልተመለሱ ጥያቄዎች በሰላማዊ ትግል በውይይት ለመፍታት የሚያስችሉ ሁኔታዎች እያሉ እየተካሄደ ያለው ትጥቅ ትግል ሀገርን ሥርዓት አልባ ለማድረግ ካልሆነ በስተቀር የሚጠቅመው አካል የለም ብለዋል።

እንዲህ አይነት አካሄድ ማንንም አይጠቅምም ያሉት አቶ አራርሶ፤ ሱማሊያ አንድ ትውልድ በከተማና በገጠር ተከፋፍሎ እርስ በእርስ በመዋጋታቸው እስከ ዛሬ ድረስ መንግሥት አልባ ሆና መቅረታቸውን ለአብነት አንስተዋል።

አቶ አራርሶ፤ የሰሜኑን ጦርነት በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት መንግሥት የወሰደው እርምጃ መልካምና የሚደገፍ ነው ብለዋል።ይህ የሰላም ጥሪ ከተሳካ ሀገሪቱን ከጦርነት አዙሪት ውስጥ ለማውጣት ጉልህ ሚና እንዳለውም ገልጸዋል።

የኦሮሞ ሕዝብ ያገኘውን ድል እያጣጣመ ያጣውን ደግሞ በሂደት በሰላማዊ መንገድ እየጠየቀ መሄድ እንዳለበት ያሳሰቡት አቶ አራርሶ፤ የትጥቅ ትግልን አማራጭ ያደረጉ ኃይሎች ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ሰላማዊ ትግልን ምርጫቸው እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።



ዶክተር ጀማል አባፊጣ

# ዩኒቨርሲቲው የማኅበረሰቡን ችግር በሚፈቱ ሥራዎች ላይ ትኩረቱን አድርጎ እንደሚሠራ ገለፀ

ውብሸት ሰንደቁ

ጅማ፡- ጅማ ዩኒቨርሲቲ የማኅበረሰቡን ችግር የሚፈቱ የምርምር እና ፈጠራ ሥራዎች ላይ ትኩረቱን አጠናክሮ እንደሚሠራ ገለፀ።

የጅማ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ጀማል አባፊጣ፤ ዩኒቨርሲቲው መሪ ቃሉ "በማኅበረሰቡ ውስጥ ነን" የሚል መሆኑን በማስታወስ ዩኒቨርሲቲው ከማኅበረሰቡ ጋር እየኖረ ከማኅበረሰቡ እየተማረ እና ችግሮችን በመረዳት የመፍትሔ ሃሳብ እያቀረበ እንዲሁም በተግባርም እየፈፀመ መሆኑን ተናግረዋል።ለወደፊቱም ዩኒቨርሲቲው የማኅበረሰቡን ችግር የሚፈቱ የምርምርና የፈጠራ ሥራዎች ላይ ትኩረቱን አጠናክሮ ይሠራል ብለዋል።

ዩኒቨርሲቲው ለሕዝብ ጥቅም የሚሰጡ እና የማኅበረሰቡን ችግር የሚቀርፉ የተለያዩ ሥራዎች ሲሠራ መቆየቱን የገለፁት ፕሬዚዳንቱ፤ በዚህ ረገድ የዜጎች ጤና የተጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ ከወራት በፊት ለሀገሪቱ ሁለተኛ የሆነውን የካንሰር ሕክምና ማዕከል ወደ ሥራ ማስገባቱን አውስተዋል።ማዕከሉ ከመላው የሀገሪቱ ክፍሎች እና ከጎረቤት ሀገራት የሚመጡ ታካሚዎችን ማስተናገድ መጀመሩን ገልፀው፤ የሕክምና አገልግሎቱን የበለጠ ለማዘመንም የልብ ሕክምና በዘመናዊ መልኩ ለማስጀምር ዝግጅቱን በማጠናቀቅ ላይ ይገኛል ሲሉ አክለዋል።

ሌሎች በርካታ ስፔሻሊቲ እና ሰብ ስፔሻሊቲ የሕክምና አገልግሎቶችን በማስፋፋትም የተጀመሩ የሕክምና ቱሪዝም በማጠናከር ወደውጪ ሀገር ለሕክምና በመሄድ ለከፍተኛ ወጪ እና እንግልት ለሚዳረጉ ዜጎች እዚሁ አገልግሎት ለመስጠት እየሠራን ነው ያሉት ዶክተር ጀማል፤ ለማኅበረሰቡ ችግር ፈቺ ፈጠራዎችን በመሥራት ረገድም በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ ገልፀዋል።

በማሳያነትም፤ ዩኒቨርሲቲው በ2014 ዓ.ም በተካሄዱ በቴክኖሎጂ እና በጤና ኢንስቲትዩቶቹ የሚገኙ መምህራን እና ተማሪዎች በግራንድ ቻሌንጅ ኢትዮጵያ ፈንድ የተደረጉ በ17 የፈጠራ ሥራዎች ግማሽ የሚሆነውን በማሸነፍ እንዲሁም በሳይንስና ቴክኖሎጂ ከተሰጡ ሦስት የግራንድ ኮሜርሺያላይዜሽን ቻሌንጅ ውስጥ ከሦስት ውድድሮች ሁለቱን በማሸነፍ የቀዳሚነት ሥፍራውን አስጠብቋል ብለዋል ዶክተር ጀማል።

በማኅበረሰብ አገልግሎትም ማኅበረሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሥራዎች መሠራታቸውን ያነሱት ዶክተር ጀማል፤ የወላድ እናቶች ማቆያዎች፣ የምንጭ ማጎልበት ሥራዎች፣ የሕክምና ቁሳቁሶች እና የአምቡላንስ እንዲሁም በርካታ ሞተር ሳይክሎችንና መሰል ድጋፎችን በተለይ ለጤና ጣቢያዎች መደገፉን ተናግረዋል።

በተጨማሪም እንደ ሀገር እየታየ ያለውን ሕገ ወጥ ስደት ለመከላከል በዞኑ የሚገኙ ከስደት ተመላሾችን እና ወደ ስደት ሊገፉ የሚችሉ ወጣቶችን በመለየት የተቀናጀ ዘመናዊ ግብርና፣ የዓሳ ማስገር፣ የዶሮ ማርባት፣ የዶሮ ጫጩቶች ማስፈልፈል እና የውሃ ላይ የመዝናኛ አገልግሎቶች ላይ በማሠልጠን እና በማደራጀት ወጣቱ በሀገሩ ሠርቶ መለወጥ እንደሚችል በተግባር እንዲያሳዩ ድጋፍ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ አብራርተዋል።

ዩኒቨርሲቲው በዘንድሮው 2014 ዓ.ም 2 ሺህ 509 ያህል ተማሪዎችን በቅድመና ድሕረ ምረቃ እና በዶክትሬት ዲግሪ እንዲሁም በስፔሻሊቲና ሰብ ስፔሻሊቲ በተለያዩ የትምህርት መስኮች አሠልጥኖ ባለፈው ሳምንት መገባደጃ ላይ አስመርቋል።ከምሥረታው አንስቶም ከ113 ሺህ በላይ ምሩቃንን ለሀገሪቱ የሰው ኃይል ገበያ አቅርቧል።

# የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ 3 ነጥብ 95 ቢሊዮን ብር ትርፍ ማግኘቱን አስታወቀ

ዋቅሹም ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡- የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ በዘንድሮ በጀት ዓመት 3 ነጥብ 95 ቢሊዮን ብር ትርፍ ማግኘቱን አስታወቀ።

የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ጋዲሳ ማሞ ትናንት የባንኩን አጠቃላይ ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም አስመልክቶ ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጡበት ወቅት፣ባንኩ በዘንድሮ በጀት ዓመት ከግብር፣ ንብረት እርጅናና መጠባበቂያ በፊት 3 ነጥብ 95 ቢሊዮን ብር ማግኘቱንና የባንኩ አጠቃላይ ሀብት 114 ቢሊዮን ብር መድረሱን አስታውቀዋል።

የባንኩ አጠቃላይ የሀብት መጠን እድገት ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር 25 ነጥብ 65 ቢሊዮን ብር ወይም 36 በመቶ በላይ መሆኑን የገለጹት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፣ በትርፍ ረገድም የአንድ ነጥብ 56 ቢሊዮን ብር ወይም 65 በመቶ በላይ እድገት ማሳየቱን ጠቅሰዋል።

ባንኩ ከአምስት ዓመት በፊት ራሱን ለመለወጥ ባደረገው ጥልቅ ጥናት ሁሉን አቀፍ የእድገት ስትራቴጂ በመጠቀሙ እንደ አምናው በአፈጻጸም ስኬት መለኪያዎች፣በፋይናንስ አፈጻጸምና በገበያ ውስጥ ባለው ድርሻ የላቀ ውጤት ማስመዝገቡን የተናገሩት አቶ ጋዲሳ፣ የማኅበራዊ ምጣኔ ሀብት እድገት እውን ለማድረግ ባደረገው ሰፊ እንቅስቃሴ አነስተኛ ተቀማጭን መሠረት በማድረግ አስተማማኝ የገንዘብ አቅም መፍጠር መቻሉን አስገንዝበዋል።

ባንኩ የቁጠባ ሂሳብ ያላቸውን የደንበኞች ቁጥር አምና ከነበረበት ከ 7 ነጥብ 73 ሚሊዮን ወደ 9 ሚሊዮን ከፍ በማድረግ 96 ነጥብ 77 ቢሊዮን ብር በመሰብሰብ በደንበኞች ቁጥር ከግል ባንኮች ቀዳሚ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ጋዲሳ፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለመቅረፍ ከዲያስፖራው ማኅበረሰብ ጋር ሰፊ ሥራ በመሠራቱ 437 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ በማግኘት ከአምና ተመሳሳይ ወቅት ጋር የ27 በመቶ ብልጫ ማሳየቱን ተናግረዋል።

የዘንድሮ በጀት ዓመት ባንኩ በተለያዩ ሥራ ዘርፎች 84 ነጥብ 28 ቢሊዮን ብር ብድር መስጠቱን ያነሱት አቶ ጋዲሳ፣የባንኩ አጠቃላይ ካፒታል 12 ነጥብ 28 ቢሊዮን ብር ሲሆን የተከፈለው የአክሲዮን ካፒታልም 7 ነጥብ 73 ቢሊዮን ብር መድረሱን ጠቁመዋል።

የአገሪቱ ምርትና ምርታማነት ለመጨመር አርሶ አደሮችን በማቀፍ የተለያዩ የብድር አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን የገለጹት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፣ ማኅበራዊ መሠረቱን ለማስፋት ሲንቄ የሴቶች ቁጠባ፣ጋሜ የልጆች ቁጠባና የወጣቶች ቁጠባ አገልግሎት ጎን ለጎን ከወለድ ነጻ አገልግሎት በስፋት እየሰጠ ይገኛል ብለዋል።

ባንኩ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን በአግባቡ እየተወጣ መሆኑን የተናገሩት አቶ ጋዲሳ፣ ከዚህ አንጻር ዘንድሮ ከሠራተኞቹ ጋር በመሆን በተለያዩ ክልሎች በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች ከ70 ሚሊዮን ብር በላይ እርዳታ ማድረጉን አስታውቀዋል።

ዜና



ፎቶ ፡- ገባቦ ገብሬ

ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ

# ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ለማጠናከር እየተሠራ መሆኑ ተገለጸ

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ካላቸው የዘርፉ ተዋንያን ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ለማጠናከር እየተሠራ መሆኑን የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ። ዓለም አቀፍ የኮንስትራክሽን አካል የሆነው ዘ ቢግ ፋይቭ ኮንስትራክት ኢትዮጵያ /The big 5 construct Ethiopia/ ኤግዚቢሽን በሚቀጥለው ዓመት እንደሚካሄድ ተገልጿል።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትሯ ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ በዘርፉ የተሠማሩ ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያላቸው ዘ ቢግ ፋይቭ ኮንስትራክት ኢትዮጵያ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ በማድረግ ኮንስትራክሽን እንዱስትሪውን ለማጠናከር እየተሠራ ነው።

የዚህ ኤግዚቢሽን በኢትዮጵያ መካሄድ ሀገራችን በኮንስትራክሽን ዘርፉ ሁለንተናዊ ዕድገት ለማስመዝገብ የላቀ ሚና አለው ያሉት ሚኒስትሯ፤ ዓለም አቀፍ ሕጎችንና አሠራሮች ፣ዘርፉ የደረሰበትን የቴክኖሎጂ ደረጃ ለማሸጋገር ዕድል ይሠጣል ብለዋል። በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩ ድርጅቶች ሰፊ ልምድ በመቅሰም ተጠቃሚ በመሆን ሀገራቸውን እንዲያስተዋውቁም እድል ይሰጣል ሲሉ ገልፀዋል።

ለብዙ ሥራ ፈጣሪ ጥበበኞች ጥሩ አጋጣሚ እንደሚፈጥር ሚኒስትሯ ገልጸው መንግሥት የተጀመረውን ሥራ ውጤታማ ለማድረግ አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ አብራርተዋል። በዘርፉ የተሠማሩ የኮንስትራክሽን ተቋማት፣ ምሑራን፣ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ፣የፈጠራ ባለሙያዎች ኮንትራክተሮችና ኢንቬስተሮች በአጋጣሚው እንዲጠቀሙ ጥሪ አቅርበዋል።

ዲኤምጂ ኢቨንትስ /DMG events/ ምክትል ፕሬዚዳንት ቤን ጊሪኒሽ በበኩላቸው የኤግዚቢሽኑ በኢትዮጵያ መካሄድ በዘርፉ ያሉ ፈጠራዎችን በማፋጠን በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዕድገት እና ኢንቨስትመንት በመደገፍ በዘላቂነት የተገነባ የአካባቢ ምህዳር ለመፍጠር እንደሆነ ገልጸዋል። የዘርፉ ተዋናዮችን በማገናኘት ፈጠራን በማስተዋወቅ በኅብረተሰቡ ዘንድ አዳዲስ የንግድ ግንኙነቶች እንዲፈጠሩ ያደርጋል ።

በሚካሄደው ኤግዚቢሽን ከ100 በላይ የሚሆኑ የኮንስትራክሽን ምርቶች ፣አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና የቴክኖሎጂ ድርጅቶች እንዲሁም ሀገር በቀል ተቋማት እንደሚሳተፉበት ገልጸው ዘርፉን ለማሳደግ የሚያስችል ዕውቀት ለማሸጋገር በር ከፋች እንደሆነ አያይዘው ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ኢንጅነር ዮናስ አያሌው በኤግዚቢሽኑ አስፈላጊነት ዙሪያ በሰጡት ማብራሪያ በዘርፉ ያለውን እውቀትንና ቴክኖሎጂ ሽግግር ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ገልጸው ቴክኖሎጂ ሽግግሩ ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪ በማድረግ ዓለም አቀፍ አምራቾችና ተቋራጮች ጋር በማገናኘት ትልቅ የንግድ ትስስር እንዲኖር ያደርጋል ብለዋል ።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ደረጃ አምርታ መሸጥ የሚያስችል አቅም ለመፍጠር ምቹ ሁኔታዎችን ስለሚፈጥር በ2031 እ.አ.አ ውስጥ ተወዳዳሪ የሆነ አፍሪካዊ ተቋም ለመገንባት ኤግዚቢሽኑ በሀገራችን መካሄዱ ጉልህ ሚና ገልጸዋል።

ኤግዚቢሽኑ በሚቀጥለው ዓመት ከግንቦት 10 እስከ 12 በአዲስ አበባ ሚሊኒየም አዳራሽ ለተከታታይ ሶስት ቀናት እንደሚካሄድ በዚሁ ወቅት ተገልጿል።

# ሕወሓት በመንግሥት የቀረበውን የሰላም ጥሪ ተቀብሎ በክልሉ ሰላም እንዲያሰፍን ጥሪ ቀረበ

**መሠረት ገ/ዮሃንስ**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ላቀረበው የሰላም ጥሪ ሕወሓት ተገቢውን ምላሽ በመስጠት በክልሉ ሰላም እንዲሰፍን እንዲያደርግ በሥራ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ፣ በቢሮ ኃላፊ ደረጃ የመሥሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ዘርፍ ኃላፊ አቶ አስመሮም ብርሃነ ጠየቁ። ሰላም ማምጣት የሚቻለው ቅድመ ሁኔታዎች በማስቀመጥ ሳይሆን ግልፅ የሆኑ ሀሳቦችን በመያዝና በመወያየት ነው ብለዋል።

አቶ አስመሮም ከወጋሕታ ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ መጠይቅ እንደገለፁት ፣ ትግራይ ውስጥ የማፈን ሁኔታ ስላለ እንጂ ጦርነት እንዲቀጥል የሚፈልግ ኣካል የለም። በሰላማዊ መንገድ እንዲጠናቀቅ ፍላጎቱ በጣም ሰፊ ነው። እናቶች መሬት ላይ ተደፍተው ፈጣሪን እየለመኑ ነው ያሉት፣ ይህ ወደ ተደራጀ ኃይል መቀየር አለበት።

አሁን ባለው ሁኔታ ትግራይ ውስጥ የተደራጀ ኃይል መፍጠር ከባድ ቢሆንም፣ በሂደት ግን በሰላማዊ መንገድ እንዲያልቅ እንደ ሕዝብ ተደራጅቶ ድምጽን ማሰማት ይገባል ብለዋል።

እንደ አቶ አስመሮም ገለጻ፤ አሁን ከዚህ በፊት እንደነበረ አይደለም፣ በአሁኑ ወቅት ይህ ግጭት ትክክል አይደለም፤ ወደ ማይሆን መንገድ እያስገቡን ነው የሚል ሀሳብ ከትግራይ ተወላጆች እየተሰማ ነው።



አቶ አስመሮም ብርሃነ

የትግራይ ሕዝብ ብዙ ዋጋ የከፈለ ሕዝብ ነው ያሉት አቶ አስመሮም፤ ከዚህ በፊትም ለሀገር ሰላም ሲል ብዙ ዋጋ ከፍሏል፤ ብዙ ልጆቹን ገብሯል፤ ነገር ግን ይህ የተከፈለ መስዋዕትነት አሁን በተፈጠረው ሁኔታ እንዲረሳ አድርገውታል ሲሉ አብራርተዋል። የትግራይ ሕዝብ ይበቃዋል ፣ በተለይ አሁን የተፈጠረው ግጭት አስፈላጊ ያልሆነ ጦርነት ነው ሲሉም ጠቁመዋል።

በመንግሥት በኩል በተደጋጋሚ እየተሰጠ ያለው የሰላም ዕድል በሕወሓት በኩል ተቀባይነት ካገኘ ቢያንስ ከዚህ በኋላ ሌላ ጥፋት እንዳይመጣ ያደርጋል ያሉት አቶ አስመሮም፤ ይህ እንዲመጣ የትግራይ ሕዝብ በሕወሓት አመራር ላይ ጫና መፍጠር አለበት ሲሉ አሳስበዋል።

አቶ አስመሮም እንዳሉት ፣ ወደ ውይይት ስትቀርብ ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ሳይሆን መወያየት ያለብህን ሀሳብ ትክክል ነው ወይስ አይደለም በማለት ነው። የሰላም ውይይት የሚደረገው እኛ ያልነው ብቻ ከሚል አስተሳሰብ በመውጣት ሀሳብ ሰጥተህ በመቀበል እንጂ ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ አይደለም። አጀንዳውን ወደ ጠረጴዛ በማምጣት ሁሉም ነገር በንግግር ማለቅ አለበት።

ሕወሓት እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች ማስቀመጡ ግጭት የመቀጠል ዝንባሌ ማሳያ ተደርጎ ነው መወሰድ ያለበት ነው ያሉት አቶ አስመሮም በየትኛውም ጊዜ ጦርነት ሊፈጠር ይችላል፤ ይህ ግን ማንንም አይጠቅምም ብለዋል። ከዚህ በላይ ስለጦርነት በማሰብ የትግራይን ሕዝብ ስቃይ ማስረዘም እንደሌለበትም አስገንዝበዋል።

እንደ አቶ አስመሮም ገለጻ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት በዚህ ሰዓት ትክክለኛ አቋም ነው የያዘው፣ ሁሉም ነገር በሰላማዊ መንገድ ለመጨረስ ዝግጁ በሆነበት ሰዓት ይህ ጉዳይ በሰላማዊ መንገድ እንዲያልቅ የማይፈልጉ አሉ። እነዚህ ኃይሎች ደግሞ ሰላም እንዳይመጣ እዚህም እዚያም ብጥብጥ እንዲከሰት ይጥራሉ፤ በመሆኑም መንግሥት የሰላም አቋም በመያዙ ዋጋ እየከፈለ ይገኛል ብለዋል።



# ቡና በዓለም ገበያ ላይ ተፈላጊ እንዲሆን በዓይነትና በጥራት በስፋት መተከል እንዳለበት ተገለጸ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ቡና በዓለም ገበያ ላይ ተፈላጊና ተወዳዳሪ እንዲሆን በዓይነትና በጥራት በስፋት መተከል እንዳለበት የቀድሞው የኦሮሚያ ቡና ገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር መሥራችና ሥራ አስኪያጅ አቶ ታደሰ መስቀሌ ተናገሩ። ቡናን በዓለም ገበያ ላይ ተፈላጊ እንዲሆን የማስተዋወቅ ሥራ በተጠናከረ መንገድ ሊሠራ ይገባል ብለዋል።

የቀድሞው የኦሮሚያ ቡና ገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር መሥራችና ሥራ አስኪያጅ የነበሩት አቶ ታደሰ መስቀሌ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ገበሬዎች የሚሸጡበት የቡና ዋጋ በወደቀበት ወቅት የኦሮሚያ የቡና ገበሬዎች ኅብረት ሥራ ተመሥርቷል። ዋና ዓላማው ገበሬዎች በኢኮኖሚ ያደጉ እንዲሆኑ ታሳቢ ያደረገ ሲሆን ቀጥሎም የሲዳማ ቡና ገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማኅበርና ይርጋ ጨፌ ቡና ገበሬዎች የኅብረት ሥራ እንደተመሠረቱ ገልጸዋል።

የቡና ንግድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመሆኑ በስፋት መተከል አለበት። ቻይና፣ ኮሪያ፣ ኢስቶኒያና ሌሎች በርካታ አገሮች ቡናን በስፋት እየገዙ ነው። የኢትዮጵያ ቡና በዓለም ገበያ ላይ ተፈላጊነቱ ከፍተኛ በመሆኑ ቡናን ኅብረት ሥራ ማኅበራቱን በማጠናከር በዓይነትና በጥራት በስፋት መትከል ያስፈልጋል ብለዋል።

አቶ ታደሰ፤ የቡና ኅብረት ሥራው ከተመሠረተ በኋላ የገበሬው ወኪል በመሆን ከአውስትራሊያ ጀምሮ የተለያዩ የአውሮፓ ሀገራትን በማካለል የቡና ዋጋ እንዲሻሻል ማድረጋቸውን ጠቁመው፤ ቡናን ምርታማና ተፈላጊ እንዲሆን ጣዕም ያለው ቡና መትከል ያስፈልጋል ብለዋል።

በቀድሞ ጊዜ ስለቡና የሚያትት ዶክሜንታሪ ፊልም በማሠራት በ17 ቋንቋዎች ተተርጉሞ በአሜሪካ፣ ላቲን አሜሪካ፣ አውሮፓ፣ ኒዊዚላንድ፣ ቻይና፣ ጃፓንና መሰል አገሮች እንዲታይ በማድረግ የቡና ገበያ ከፍ እንዲል ተደርጓል። ለአብነት የአንድ ኪሎ ቡና ዋጋ አንድ ዶላር በነበረበት ጊዜ የተፈጥሮ ይዘቱን ያልለቀቀ የኢትዮጵያ ቡና እስከ ሶስት ዶላር ይሸጥ እንደነበር፤ አሁንም በስፋት መሠራት አለበት ብለዋል።

እንደ አቶ ታደሰ ገለጻ፤ የኢትዮጵያን ቡና ለዓለም ገበያ ለማስተዋወቅ ከዚህ ቀደም የተሠራውን ያህል አሁን ላይ እየተሠራ አይደለም። ስለዚህ ቡናን ለዓለም የማስተዋወቅ ሥራው ትኩረት ሊደረግ ይገባል። ለዚህም ቡና አምራቹ ብቻ ሳይሆን ቡና ገዥው አካል ማስተዋወቅ አለበት።

መንግሥት የቡና አብቃይ ማኅበራትን አጠናክሮ ጥራቱን እንዲጠብቅ የማድረግ ሥራም ሊሠራ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

# «ከሕወሓት በስተጀርባ ያለውን የሶስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት ለተባበሩት መንግሥታት ማሳወቅ ይገባል»

-ዶክተር ወሂበእግዚር ፈረደ
የፖለቲካ ተንታኝ

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

አዲስ አበባ፡-ከሱዳን ሠራዊት ትንኮሳ እና ከሕወሓት ሴራ በስተጀርባ ያለውን የሶስተኛ ወገን ጣልቃገብነት ለተባበሩት መንግሥታት በአግባቡ ማሳወቅ እንደሚገባ ተጠቆመ።

የስትራቴጂክ ጉዳዮች ተመራማሪው ዶክተር ወሂበእግዜር ፈረደ በተለይም ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለፁት፤ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጣዊ ጉዳዮች ጣልቃ በመግባት በቀጣናው አለመረጋጋት እንዲፈጠር ከፍተኛ ሴራ እየተከናወነ መሆኑን በበቂ መረጃ በማስደገፍ ለተባበሩት መንግሥታት ማሳወቅ ይገባል።

በተለይ የፌደራል መንግሥት ከሕወሓት ጋር የሰላም ውይይት ለማድረግ ውጥን መያዙ የሚያበሳጫቸው የውጭ አካላት የሰላም ውይይቱ እንዳይሳካ ኢትዮጵያን የማተራመስ ስትራቴጂ በመንደፍ ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ነው ብለዋል።

እንደ ዶክተር ወሂበእግዚር ገለፃ፤ ኢትዮጵያን ለማተራመስና ቀጣናውን ሠላም ለመንሳት ለውጭ ኃይሎች ሕወሓት ጥሩ ተላላኪ ከመሆኑም በተጨማሪ እሱ በአምሳሉ የፈጠራቸው ሸኔ እና ሌሎች አሸባሪ ቡድኖች መንግሥትን ውጥረት ውስጥ ለመክተት እየተሯሯጡ ነው ።

መንግሥት ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ከቻለ የውጭ ጠላቶች የሚፈልጉት እንዳይሳካ ስለሚያደርጋቸው በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ኢትዮጵያ ላይ ጫና እየፈጠሩ ነው ብለዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ቀጣናው እንዳይረጋጋ ለአልሻባብና ሌሎች አሸባሪ ቡድኖች ሁለንተናዊ ድጋፍ በማድረግ ኢትዮጵያን የማወክ ስትራቴጂ ነድፈው የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች እንዳሉም ጠቁመዋል። ሰሞኑን በኢትዮጵያ ላይ የሚደረገው ትንኮሳም የዚሁ ቀጣናውን የማወክ ፕሮጀክት አካል ነው ብለዋል።

በሌላ በኩል በቅርቡ የሱዳን ወታደራዊ ክንፍ ከኢትዮጵያ ጋር የገባበት ውዝግብ የሁለቱ ሃገራትን ታሪካዊ ግንኙነት የማይሸረሽር መሆኑን የጠቆሙት ዶክተር ውሂበእግዜር፤የሁለቱ ሀገራት ሕዝቦች ግንኙነት ለዘመናት የሚቀጥል መሆኑንና አሁን የሚደረጉ ትንኮሳዎችም ረብየለሽ እና የሱዳን ሕዝብ ፍላጎት አለመሆናቸውን የታሪክ ድርሳናትን በመጥቀስ አረጋግጠዋል። ድርጊቱም የወታደራዊ ክንፉ ውስጣዊ ጫና መቋቋም ያለመቻልና አጀንዳ ለማስቀየስ የታለመ መሆኑን አብራርተዋል።

የምንገኝበት ጊዜ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሦስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት የሚከናወንበት ወቅት መሆኑን ያስታወሱት ተመራማሪው፤ በዚህ ወቅት ኢትዮጵያን በማወክ ከዓላማዋ ማሰናከል የውጭ ጠላቶች ቀዳሚ አጀንዳ እንደሆነም ጠቁመዋል።

እንደ ዶክተር ውሂበእግዜር፤ ይህን ለማሳካትም በህዳሴ ግድብ አቅራቢያ በተለይም በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል እና በመላ ሀገሪቱ የሚንቀሳቀሱ ፀረ-ሠላም ኃይሎችን እንደመሣሪያ መጠቀም፣ በሱዳን ቀጥተኛ ትንኮሳ መፈፀምና ለጦርነት መጋበዝ የወቅቱ አጀንዳቸው መሆኑን ጠቁመዋል።በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግሥት ለዚህ ተመጣጣኝ የሆነ ስትራቴጂክ መልስ መስጠት እንዳለበት አስረድተዋል።

የውጭ ኃይሎች ቀጣናውን በማወክና በኢትዮጵያ ውስጣዊ ጉዳዮች ጣልቃ እያደረጉ ያለውን ሁለንተናዊ የጥፋት ሴራ፤ በመረጃ በማስደገፍ ለተባበሩት መንግሥታት ማሳወቅ ይገባል ያሉት ዶክተር ወሂበእግዜር፤ ውስጣዊ ሽኩቻዎችንም በሰላማዊ መንገድ በመወያየትና በመፍታት ሀገራዊ አጀንዳዎች ላይ ማተኮር እንዳለበት አሳስበዋል።

በተለይም ከዓባይ ጋር ተያይዞ ከፊታችን በመቆም ለማደናቀፍ የሚጥሩ የውጭ ኃይሎችን እኩይ ዓላማ መረጃ ላይ በመመሥረት ማጋለጥና የኢትዮጵያን አንድነት ለማጠናከር የሀገሪቱ ደህንነት እና ፀጥታ መዋቅር እጅግ ፈርጣማና ዘመኑ የደረሰበትን ቴክኖሎጂ የታጠቀ እንዲሆን መሥራት ዋነኛ ጉዳይ መሆን አለበት ብለዋል።

# ሕወሓት ያመከናቸውን የሰላም እድሎች...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ፕሮፌሰር አደም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ሕወሓት በወደጦርነቱ ከመግባቱ በፊት በተደጋጋሚ የሰላም ጥሪዎች ቀርበውለታል፤ ከጦርነቱ በኋላም ቢሆን ተደጋጋሚ የሰላም አማራጮች እጁ ላይ ገብተው አልተጠቀመበትም።እሳቸውን ጨምሮ በርካታ የሃገር ሽማግሌዎች የሠላም አማራጭ ለማፈላለግ ሕወሐት ሊቀመንበር ዶክተር ደብረጽዮን ገብረሚካኤል ቢሮ ተገኝተው እንደነበር ያስታወሱት ረዳት ፕሮፌሰር አደም፤ ሆኖም አንዳቸውም ሳይሳኩ በመምከናቸው አሁን የተከሰተው ችግር ሊከሰት ችሏል ብለዋል፡፡

እንደ ረዳት ፕሮፌሰር አደም ገለጻ፤ ይህ ቡድን ለሰላም ብቻ ሳይሆን ለልማትም በሩ ዝግ ነበር።ለዚህም ማሳያው በቱሪዝም ገቢ ሕዝብን ተጠቃሚ ለማድረግ የሰላም በር ጠይቀው ዶክተር ደብረጽዮን ገብረሚካኤል ፍቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል ብለዋል።በመሆኑም በሰሜኑ ሀገሪቱ ክፍል ለተከሰተው የጦርነት አዙሪት ምክንያት ሕወሓት ነው፡፡

ረዳት ፕሮፌሰር አደም እንዳሉት፤ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ቱሪዝም ፣ ንግድና ኢንቨስትመንት አስፈላጊ ነው።።እነዚህ ሶስቱ አስፈላጊ ነገሮች ያለ ሰላም ተግባራዊ ሊሆኑ ስለማይችሉ የሕወሐት ሊቀመንበሩ ለትግራይ ሕዝብ ብቸኛው የኢኮኖሚ እድገት አማራጭ የሆነውን ቱሪዝም ሴክተር ገቢውን እንዲያሳድግ ጎብኚ ወደ ክልሉ እንዲገባ ትንሽ የሠላም በር እንዲከፈት ቢጠየቁም ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡

የሕወሓት ሊቀመንበር የሰላም በር በመዝጋት የጦርነት አማራጭ መምረጣቸው ከቱርክ 320 ፣ ከማሌዥያ 80ሺህ ፣ ከፓኪስታን 120ሺህ ፣ ከኢንዶኔዥያ 200 ሺህ በድምሩ ከተለያዩ ሀገራት የተውጣጡ ከ400 ሺህ 320 በላይ ጎብኚዎች የምታገኘውን ገቢ እንዳታገኝ በማድረግ የትግራይ ሕዝብን አሁን ላለበት የከፋ ሁኔታ ዳርገዋል ብለዋል።

በዶክተር ደብረጽዮን ውሳኔ ተከትሎ ብዙ ነገሮች ተበላሽተዋል።የኢትዮጵያን ጦር በመምታት በጦርነት የሚያሸንፉ መስሏቸው ሳይሳካላቸው ሲቀር ዘርፈው በሄዱት ካፒታል ዓለማቀፍ ሚዲያዎችን በመግዛት አዲስ አበባን በሁለት ቀን ፕሮፖጋንዳ የዓለምን ሕዝብ አሳስቷል።እንደማያዋጣቸውም የተማሩበት አጋጣሚ ነው ብለዋል፡፡

"አሁን ሕወሓት መንግሥት ወደ አስቀመጠው የሰላም መንገድ በመግባት በሰላማዊ መንገድ ችግሮችን መፍታት አለበት።በምዕራባውያን ሳንባ መተንፈስ ዩክሬንን ውድቀት ላይ እየጣላት መሆኑን በማየት ከገባበት ግትርነት ሊወጣ ይገባል።አንድ እምነትና ቋንቋ ያለው የመን እና ሶሪያን ያየ ለሁሉም ጦርነት እንደማይበጅ ሊማርበት ይገባል" ብለዋል ።

እንደ አንድ ሽምግልና ቡድን አባል የሕወሓትን ጸረ ሰላም አካሄድ ወደሰላማዊ መንገድ ለመመለስ ብዙ ጊዜ ሙከራ መደረጉን ያስታወሱት ረዳት ፕሮፌሰር አደም፤ የትግራይ ሕዝብ ከሕወሓት ግትርነት በመላቀቅ ሰላማዊ መንገድ መምረጥ እንዳለበትም መክረዋል ።

መንግሥት በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ማሰቡ መልካም እንደሆነ የገለጹት ፕሮፌሰሩ፤ ለትግራይ ሕዝብ ጥቅም ሲባል ሰላማዊ መንገዱን መምረጥ ለሁሉም እንደሚያዋጣ ገልጸዋል።

ለሰላማዊ መንገዱ ስኬታማነት በተለያዩ ቋንቋዎች ሰፊ የሚዲያ ሥራ እንደሚያስፈልግም ረዳት ፕሮፌሰር አደም ጠቁመዋል። የሰላም አማራጭ አስፈላጊነትና የሽምጋዮችን ሙከራ ማሳየት ከሚዲያ እንደሚጠበቅ ገልጸዋል ።

የሀገር ውስጥ ሽምጋዮች ቡድን ፣ የእምነት አባቶች በጋራ ተከታዮቻቸውን በአንድ ላይ አቅፎ የሀገር ጉዳይን በዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ዘንድ ድጋፍ እንዲያገኝ የተለያዩ ኮንፈረንሶች በማካሄድ መንግሥት የጀመረውን የሰላም አማራጭ ስኬታማ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።ይህንን እውን ለማድረግ ጠንካራ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል።

# ምክር ቤቱ በዜጎች ላይ የደረሰውን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ክፍሎች በንጹሓን ዜጎች እንዲሁም ጸጥታና ደኅንነት ለማስጠበቅ በተንቀሳቀሱ የጸጥታ አካላት ላይ ለደረሰው ሕይወት መጥፋት አስመልክቶ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ አጽድቋል።

በዚህም መሠረት፣ በግፍ ለተጨፈጨፉት ዜጎች የአንድ ደቂቃ የኅሊና ጸሎት በማድረግ የጀመረው ምክር ቤት፤ በምክር ቤቱ የበላይ አመራር የሚሰየሙ ስብጥሩ ሁሉንም ብዝኃነቶች ታሳቢ ያደረገ ልዩ ኮሚቴ ተቋቁሞ ጉዳዩን በማጣራት ምክር ቤቱ እና ሕዝቡ በቂ መረጃ እንዲኖረው ለማስቻል እንዲሁም ለቀጣይ እርምጃዎች የሚረዳ ምክረ ሃሳብ እንዲያቀርብ ተወስኗል።

በተጨማሪም፣ በሀገሪቱ በየትኛውም ክልልና አካባቢ በንጹሓን ዜጎች ላይ የሞትና የአካል ጉዳት ያስከተሉና ንብረት ያወደሙ አካላት በሕግ እንዲጠየቁ፤ በየደረጃው ያለው አመራር አካል፣ የጸጥታ አካልና የፍትሕ ተቋም የሕዝቡን ደኅንነትና ሰላም እንዲያስከብርና አጥፊዎችን ለሕግ እንዲያቀርብ፤ ከመንደራቸው የተፈናቀሉ ዜጎች መልሶ የማቋቋም ሥራ በአስቸኳይ እንዲሠራ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕዝቦች በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ከየትኛውም ጊዜ በላይ በወንድማማችነት፣ በአብሮነትና በአንድነት እንዲቆሙ ውሳኔ ተላልፏል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ አቶ ታገሰ ጫፎ የውሳኔ ሃሳቡን ባቀረቡበት ወቅት፤ ኢትዮጵያ በርካታ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ተከባብረውና ተዋደው የሚኖሩባት፣ የተለያዩ ኃይማኖቶችና ባሕሎች ተቻችለው የሚኖሩባት ሀገር ብትሆንም ባለፉት 27 ዓመታት የተዘራው ከፋፋይ የዘር ጥላቻ በሕዝብ ውስጥ ዘግናኝ ድርጊቶች እንዲፈጸሙ በር ከፍቷል ብለዋል።

በዚህም የተነሳ በሀገራችን በተለያዩ አካባቢዎች በንጹሓን ዜጎች ላይ ዘግናኝ ጭፍጨፋዎች ሊፈጸሙ እንደቻሉም ገልጸዋል።

በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በንጹሓን ዜጎች ላይ የተፈጸሙትን ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች በተመለከተ አፈ-ጉባዔው ባቀረቡት የውሳኔ ሃሳብ መስማማታቸው የገለጹት የምክር ቤቱ አባላት፤ ዝርዝር ውሳኔዎቹ በተቀመጠው ልክ ተግባራዊ እንዲሆኑ ጠይቀዋል።

የምክር ቤት አባሉ አቶ ክርስቲያን ታደለ በበኩላቸው፣ የደረሰው ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት በሁሉም ኢትዮጵያውያን የተፈጸመ መሆኑን መታመን አለበት ያሉ ሲሆን፤ በግፍ ለተጨፈጨፉት ዜጎች ብሔራዊ የኃዘን ቀን እንዲታወጅ ምክር ቤቱን ጠይቀዋል።

የሚቋቋመው አጣሪ ኮሚቴ ድርጊቶቹ ወደተፈጸመባቸው አካባቢዎች በሚሄዱበት ወቅት ወንጀለኞቹ መረጃዎችን አስቀድመው እንዳያጠፉ ተገቢውን ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባም አስረድተዋል።

በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በድርጊቱ ላይ እጃቸው ያለበት እንዲሁም ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ያልተወጡ ከቀበሌ እስከ ፌዴራል ደረጃ ያሉ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በሕግ ሊጠየቁ ይገባል ያሉት ሌላኛዋ የምክር ቤት አባሏ ወይዘሮ የሺሃሳብ ጸጋው ናቸው።

ወይዘሮ የሺሃሳብ አክለውም፣ ጉዳዩን እንዲያጣራ የሚቋቋመው ልዩ ኮሚቴ ሁሉም ብዝኃነቶች ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን እንዳለበትም አጽንዖት ሰጥተዋል።

የምክር ቤት አባሉ ፕሮፌሰር መሐመድ አብዶ ደግሞ የሚቋቋመው ኮሚቴ ችግሮች የተከሰቱባቸው ሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ማዳረስ መቻል አለበት ብለዋል።

የደረሰውን አጠቃላይ ጉዳት ከማጣራት በተጨማሪ ኮሚቴው የእለት ደራሽ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው እንዲሁም የደኅንነት ስጋት ያለባቸው ዜጎች ጉዳይ የሚያጣራ ንዑስ ኮሚቴ ሊኖረው እንደሚገባም ምክረ ሃሳብ አቅርበዋል። መንግሥት የዜጎችን ሰላምና ደኅንነት የማረጋገጥ ቀዳሚ ኃላፊነቱን በአግባቡ ሊወጣ ይገባል ያሉት የምክር ቤቱ አባላት፤ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ባልተወጡ በየደረጃው ያሉ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ላይ ተገቢውን እርምጃ መወሰድ እንዳለበትና የሚወሰደው እርምጃም ግልጽና ለሕዝብ ይፋ መሆን እንዳለበትም አሳስበዋል።

በሀገሪቱ በዜጎች ላይ የተፈጸመውን ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት አስመልክቶ የቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ውሳኔ ቁጥር 10/2014 ሆኖ በአንድ ተቃውሞና በአንድ ድምጸ ተዓቅቦ በአብላጫ ድምጽ ጸድቋል።

# የሆቴል ግብዓት አቅራቢዎች ኤክስፖ ሊካሄድ ነው

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የሆቴል ግብዓት አቅራቢዎች ኤክስፖ ከሐምሌ 12 ቀን 2014 ዓ/ም ጀምሮ ለሁለት ቀናት በኤልያና ሆቴል እንደሚካሄድ ተገለጸ። በዚህ ኤክስፖ ከሁለት መቶ በላይ ተሳታፊዎች እና ከ 10 ሺህ በላይ ጎብኚዎች ይሳተፉበታል ተብሎ ይጠበቃል ።

ጉዳዩን በሚመለከት ለጋዜጠኞች መግለጫ የሰጡት የኤልያና ሆቴል የሰው ኃይል አስተዳደር ኃላፊ ወይዘሮ ምስራቅ ሞገስ እንደገለፁት፤ ኤክስፖው በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት የተቀዛቀዘውን የሆቴል ቱሪዝም ዘርፍን ለማነቃቃትና በፍላጎትና አቅርቦት መካከል ያለውን ክፍተት ለመገንባት ታልሞ የተዘጋጀ ነው።

የኤክስፖው አጠቃላይ ጽንሰ ሀሳብ አቅራቢዎችን ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ማሳተፍ ሲሆን ይህ የገበያ ትስስር ሁሉም ዓይነት እና መጠን ያላቸው ኩባንያዎች ምርቶችን እና አገልግሎቶችን እንዲያቀርቡ ፣ እንዲያስተዋውቁ እና እንዲሸጡ ለማስቻል መሆኑንም ኃላፊዋ አመላክተዋል ።

ኤክስፖው በተለይ የሁሉም አቅራቢዎችና ገዥዎች ፍላጎታቸውን ፣ አገልግሎታቸውን በቀላሉ ለማሟላት ፣ ከሆቴል ኢንዱስትሪ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ምርታቸውን ለማስተዋወቅ እና የሆቴል ፍላጐትን እና አቅርቦትን በአንድ ቦታ እና እንደ ሀገር የውጭ ምንዛሪን ችግር ለመቅረፍ ያተኮረ ነው ሲሉም ገልጸዋል።

የግራንድ ኤልያና ሆቴል ማርኬቲንግና ሴልስ ዳይሬክተር ወይዘሪት መርሐዊት ፀጋዬ በበኩሏ፤ ኤክስፖው ሰዎችና አቅራቢዎች አብረው የሚሠሩበትን መንገድ የሚቀይር የትብብር መድረክ መሆኑን ገልፃለች።

በዚህ ኤክስፖ ከሁለት መቶ በላይ ተሳታፊዎች እና ከ 10 ሺህ በላይ ጎብኚዎች ይሳተፉበታል ተብሎ ይጠበቃል፤ ያለችው ወይዘሪት መርሐዊት፤ ኩባንያዎቹ የምርት ስማቸውን ፣ የምርታቸውን ተሳትፎ እና የቡድን ምርታማነትን ለማሳደግ አዲስ ውህደቶችን በመጀመሪያ ማግኘት እንደሚጀምሩም ተናግራለች።

የኤክስፖው አዘጋጅ የሪሊፍ ኤቨንት ኦርጋናይዘር አቶ አቤኔዘር ላቀው በበኩላቸው ኤክስፖው እንደ ሀገር የሆቴሉ ኢንደስትሪ አቅራቢዎችን ባለማወቁ ምክንያት የሚባክን የውጭ ምንዛሪ በማስቀረት ረገድ ጉልህ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ብለው በማመናቸው መዘጋጀቱን ገልጸዋል።

የውጭ ምንዛሪ ከሚያስፈልጋቸው ኢንዱስትሪዎች አንዱና ዋነኛው የሆነው የሆቴል ኢንዱስትሪ መሆኑን የገለፁት አቶ አቤኔዘር፤ ይህንን ከውጭ የሚያስገባቸውን የተለያዩ መገልገያዎች ፣ የምግብ ግብዓቶች ፣ ፈርኒቸሮች ኬሚካሎች እንዲሁም ሁሉም አይነት አስፈላጊ ነገሮችን በሀገር ልጆች በሀገር ማቴሪያሎች እያመረቱ የሚያቀርቡ አካላት እንዳሉ ለማየት ችለናል ብለዋል ። የዚህ ኤክስፖ ዋና ዓላማ በሀገራችን እየተጋፈጥን ያለነውን የውጭ ምንዛሪ ችግር ከመቅረፍ አኳያ ጉልህ ሚና አለውም ብለዋል ።

በኤክስፖ ላይ ለመሳተፍ እና ለመመዝገብ ለሁሉም አይነት ተሳታፊዎች የምዝገባ ቅጽ እንዲሁም የተለያዩ ፓኬጆች ያዘጋጀን ሲሆን ይሄንን ኤክስፖ መሳተፍ የሚፈልግ ማንኛዉም ድርጅት የገበያ ጥናትና ሽያጭ ክፍልን በቀጥታ መግኘት ይችላል ሲሉ አቶ አቤኔዘር ገልጸዋል።

# በኦሮሚያ ክልል የተፈፀሙ አሰቃቂ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በከፍተኛ ሁኔታ ዋጋ ሲያስከፍል ቆይቷል ብለዋል።

እየተጎዳ ያለው የተለየ የፖለቲካ አቋም ያለው ሕዝብ ሳይሆን ምንም የማያውቅ ለፍቶና ጥሮ ግሮ የሚኖር ንጹሕ ዜጋ ነው ያሉት ዶክተር በለጠ፤ ይህ የተቀናጀና መዋቅራዊ ጭፍጨፋና ጉዳት እንዲቆም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ርብርብ በማድረግ ለመፍትሔው ሊሠራ ይገባል ብለዋል። ይህ ካልሆነ ግን አገሪቱን ወደ አልተፈለገ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ የሚከት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

እየደረሰ ያለውን መዋቅራዊ ጥቃት በዘላቂነት ማስቆም የሚቻለው የኢትዮጵያን ሰላም የሚፈልግ አካል ሁሉም ተወያይቶ የጋራ መፍትሔ ሲያበጅ መሆኑን የጠቆሙት ዶክተር በለጠ፤ ሕዝብን ወደ ተሻለ ደረጃ ማሻገር የሚችል መፍትሔ ሊመጣ ይገባል። አብን እያስተጋባው ያለውን ድምጽ ሌላው ኢትዮጵያውያን በተለይም ልሂቁና የፖለቲካ አመራሩ ክፍል ጉዳቱ ጉዳታችን ነው ብሎ ለመፍትሔ ሊሠራ ይገባል ብለዋል ።

ሸኔ በስፋት በአማራ ሕዝብ ላይ ሰፊ ጭፍጨፋ ቢያደርስም መጠኑ ይብዛም ይነስም በኦሮሞ ሕዝብም ጉዳት እያደረሰ ነው ያሉት ዶክተር በለጠ፤ ስለሆነም ሁሉም ሊያወግዝና ሊታገለው ይገባል ሲሉ ተናግረዋል። በሁሉም አቅጣጫ ያሉ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የዲሞክራሲና የሰብዓዊ መብት ዕጦት አለባቸው፤ ይህም ሊፈታ የሚችለው በጋራ በመወያየት መፍትሔ ሲኖር ነው ብለዋል።

የአብን የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ጣሂር መሐመድ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ሸኔ ከይፋዊና ህቡዕ አጋሮቹ ጋር በመተባበርና የመንግሥትን ሀብትና መዋቅር በመጠቀም በአማራ ሕዝብ ላይ እየፈጸሙት ያለውን የዘር ማጥፋት ወንጀል አጠናክረው ቀጥለዋል። በብዙ ምዕራፍ በተከፈለው የዚህ የተቀናጀ ፣ ተከታታይና ስልታዊ የንጹሓን ግድያም ብዙዎች ውድ ሕይወታቸውንናም ሃብትና ንብረታቸውን አጥተዋል።

አብን በወለጋና አካባቢው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲታወጅና በፌደራል የፀጥታ ተቋማት ቁጥጥር ስር እንዲውልና የወንጀል ፈፃሚዎች በግልፅ ችሎት እንዲዳኙ ጠይቋል። ማንነት ተኮር ጭፍጨፋ እንዲፈፀም ቅስቀሳ ሲያደርጉና እያደረጉ ያሉ አካላት መኖራቸውን የገለጹት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው፤እነዚህ አካላት ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ አሳስበዋል።

አጥቂዎች በግልፅ ፍርድ እንዲበየንባቸው፤ ጥቃቱ እንዲባባስ ያደረጉ ሚዲያዎች፣ ፖለቲከኞችና ግለሰቦችም ተጠያቂ እንዲሆኑ አብን በመግለጫው አሳስቧል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከችግሮች በላይ የሚያደርግ የስነ ልቦና ጥንካሬ መፍጠር ያስፈልገናል!

በገነባው ከችግር በላይ የመሆን ስለልቦናዊ ጥንካሬ አሸንፎ ይወጣል እንጂ የትኛውም ሀገር እና ሕዝብ በታሪክ በአንደኛው ምዕራፍ ፈተና ያጋጥመዋል። ይህን ማህበረሰባዊ እውነታ፤ የህይወት ኡደት የማያልፍ ሀገርና ሕዝብ የለም። ፈተናውን በስኬት አሸንፎ የሚሻገር እንዳለ ፤ ተሰነካክሎ የሚወድቅም አለ።

እኛም እንደ ሀገር በዚህ እውነታ ውስጥ በተደጋጋሚ ለማለፍ የተገደድን ህዝቦች ነን ፤በተለያዩ የታሪክ ምዕራፎች ብዙ ፈተናዎች አጋጥመውናል፤ ፈተናዎቹን በአሸናፊነት ለማለፍ ብዙ ዋጋ ብንከፍልም የከፈልነውን ያህል መሻገር ባለመቻላችን እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም ፈተናዎቻችን መልካቸውን እየቀያየሩ እየተፈተኑን ፤ ዋጋ እያስከፈሉን ነው።

አንድም ፈተናዎቻችንን በአግባቡ መረዳት የሚያስችል ስክነትና መረጋጋት መፍጠር አለመቻላችን ፤ከዚያም በላይ አብዛኛዎቹ ፈተናዎቻችን ምንጫቸው ድንበር ተሻጋሪ ፤ ከራስ ወዳድነት እና ከዚህ ከሚመነጭ ስጋት የሚወለድ መሆኑን አለመረዳታችን ፤ ለዚህ የሚሆን ንቃትና ዝግጁነት አለማዳበራችን ከፈተናዎቻችን ጋር አብረን ዘመናት እንድንጓዝ አድርገውናል።

ታሪካዊ ጠላቶቻችን የተፈጥሮ ሀብታችን ተጠቅመን የማደግና የመበልጸግ አቅማችንን ከኛ ቀድመው ተረድተው፤ ይህንን አቅማችንን እውን እንዳናደርግ በእኛ ጉዳይ እንቅልፍ አጥተው ዘመናትን ቆጥረዋል፤ በኛ ጉስቁልና ነገዎቻቸውን ብሩህ ለማድረግ የፈተና ዘመናችንን አስረዝመውታል ።

እንደ ማንኛውም ሕዝብና ሀገር የወደፊት እጣፈንታችን የሚወሰነው ባለን የተፈጥሮ ፤ የሰው ሀብትና ቴክኖሎጂ ነው። በተለይም እንደ ሀገር ካለን ያልተነካ የተፈጥሮ ሀብት አንጻር መጪው ዘመናችን የሚወሰነው ይህንን ሀብት አልምተን የሚጨበጥ ተስፋ ስናደርገው ብቻ ነው። ከዚህ ውጪ ማሰብም ሆነ ማለም የሚቻል አይደለም።

ታሪካዊ ጠላቶቻችን ግን ከቀደመው ዘመን ጀምሮ ይህንን ሀብት የማልማት አቅም ሆነ ተስፋ እንዳንሰንቅ በብዙ ተንቀሳቅሰዋል ። በብዙ ወዳጅነት አብረናቸው ለመኖር የሄድንበትን ርቀት ያህል በግልጽም ይሁን በስውር በጠላትነት ረጅም ርቀት ሄደዋል። በየዘመኑም ስለ ህልማችን ዋጋ እንድንከፍል አድርገውናል።

በርግጥ የተፈጥሮ ሀብታችንን የመጠቀም ተፈጥሯዊ መብት አለን፤ ይህንን ደግሞ የሞራል ሆነ አለም አቀፍ ሕግ ይህንን መብት አይነፍገንም። ትልቁ ችግራችን የተፈጥሮ ሀብታችንን መጠቀም የሚያስችል ሀገራዊ ቁመና መፍጠር አለመቻላችንና ይህንን ቁመና መፍጠር የምንችልበትን ማስተዋል አለመጨበጣችን ነው ።

ሁሌም ጠላቶቻችን በሚቀዱልን የጥፋት ቦይ እየፈሰስን፤ በገዛ ተስፋችንና ነገዎቻችን ላይ አመጸኞች ሆነን ዘመናት ማስቆጠራችን ነው።ይህ እውነታ የዛሬም የእለት ተእለት ሕይወታችን መገለጫ እየሆነ ከመጣ ውሎ አድሯል። በየዕለቱ ከምንሰማው ሞትና መፈናቀል በስተጀርባ ያለው እውነታ ይሄው ነው።

በተለይም የውሀ ሀብታችንን ተጠቅመን ነገዎቻችንን ብሩህ ለማድረግ የጀመርነው ታሪካዊ ጉዞ ለማሰናከል እያጋጠሙን ያሉ ፈተናዎች እንደ ሀገር ያለንን ህልውና የሚፈታተኑበት ደረጃ ላይ ደርሷል።ይህ ደግሞ የጀመርነው የብልጽግና መንገድ የቱን ያህል መራራእና ከፍ ላለ ትግል ዝግጁነትን የሚጠይቅ እንደሆነ አመላካች ነው።

ከመጣንበት የዘመናት ውጣ ወረድና በየዘመኑ ስለተስፋችን ከከፈልነው ዋጋ አንጻር ዛሬ ለሚጨበጠው ተስፋችን ከፍ ያለ መስዋእትነት ለመክፈል መገደዳችን የሚጠበቅ ቢሆንም ፤ ይህንን እውነታ በሚገባው ደረጃ አለመገንዘብ በራሱ ሊያስከፍል የሚችለው ዋጋ ትንሽ የሚባል አይሆንም።

የጀመርነው የብልጽግና ጉዞ አልጋ በአልጋ አይደለም፤ በመፈክርና በዲስኩር ብዛት የምንደርስበትም አይደለም፤ ከጠላቶቻችን የጠላትነት መንፈስና ክፋት አንጻር ገና በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ማለፋችንና መፈተናችን አይቀርም። በዚህ ውስጥ ሳይፈተን የሚያልፍ ዜጋም ሊኖረን አይችልም።

አንዱ በገዳይነት ሌላው በተገዳይነት፤ አንዱ በአፈናቃይነት ሌላው በተፈናቃይነት ፤ አንዱ በሕዝባዊነት ሌላው በጸረ - ሕዝብነት ፤አንዱ በባንዳነት ሌላው በሀገር ወዳድነት ፤ አንዱ በአሻባሪነት ሌላው በተሸባሪነት፤ አንዱ በሌብነት ሌላው በታማኝነት ወዘተ መፈተኑ አይቀርም። ለውጥ /ብልጽግና/ ይህን ሁሉ አልፎ የሚመጣ በብዙ ዋጋ የሚሰላ ማህበራዊ ኩነት ነው።

በዚህ ሄደት ውስጥ የልብ ስብራት የሚፈጥሩ፤ ሀገርን እንደ ሀገር ሀዘን ውስጥ የሚከቱ ክስተቶች ይፈጠራሉ። የሚነጫንጩ፣ እንደ ሕዝብ ትዕግስትን የሚፈታተኑ እውነታዎች ይከሰታሉ። ለዚህ ሁሉ ያለው አማራጭ ከችግሮቹ በላይ የሚያደርግ የስነ ልቦና ጥንካሬ መፍጠር ብቻ ነው። ለዚህ ደግሞ ራስን ማዘጋጀት ተገቢ ነው!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።**

## የሐምሌን ዝናብ ከነዳጅ ጋር ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ሰሞኑን በየመንገዱ ዳርቻ የእግረኞችና የመኪኖች ሰልፍ በርክቷል። በተለይ ደግሞ መኪኖቹ በሰልፍ ውለው በማደር ቀናትን እያስቆጠሩ ነው። ተሽከርካሪዎቹ ባልተለመደ ሁኔታ መንገዱን ማጨናነቃቸው ያለምክንያት አልሆነም። እረፍት አልባው የነዳጅ ወረፋ በሰውሰራሽ ችግር ተተብትቦ ጊዜን በመቁጠሩ እንጂ።

ዛሬም ግን የራስ ወዳዶቹ እጆች አልተሰበሰቡም። አሁንም በየጥጋጥጉ፣ በየጥሻው ነዳጅን ያህል ጉዳይ በችርቻሮ በመሸቀጥ ራስን ከማክበር ማማ ለማድረስ በጥድፊያ ላይ ናቸው። የሀምሌ ወር መግባትን ተከትሎ ይጨምራል የተባለው የነዳጅ ዋጋ ስጋት የሆነባቸው አንዳንዶች ዕንቅልፍ ካጡ ሰንብተዋል። ብዙሀን በማንኪያ ይቀምሱት በቸገራቸው አጋጣሚ እነሱ በአካፋ ዝቀነው እንሙት ማለታቸው እያስገረመን ነው።

በዓለማችን በየዕለቱ የምንሰማቸው ኢኮኖሚያዊ ጫናዎች የእኛን መሰል አገራት አቅም መፈታተናቸው አይቀሬ ሆኗል። ሁሌም እንደሚስተዋለው በልጽገናል የሚሉት አገራት ለሚገጥማቸው ወቅታዊ የዋጋ ግሽበት እምብዛም ሲንገዳገዱ አይስተዋልም። አስቀድመው ራሳቸውን በኢኮኖሚው አሳድገዋልና መላና መፍትሄው በእጃቸው ነው።

ይህ አይነቱ የኢኮኖሚ ተጽዕኖ በተለይ ወደ አፍሪካውያን ባነጣጠረ ጊዜ ጫናውን ከበድ ያደርገዋል። በተለይ የሰማይ ደመናን ተስፋ አድርጎ ለሚያድርና ያደጉ አገራትን ምንዳ ለሚናፍቅ ህዝብ ደግሞ አጋጣሚው በርካታ ችግሮችን ይመዛል። ኢኮኖሚው በድንገት ሽብረክ ባለ ጊዜ ህይወት ትርጉም ታጣለች። ችግር ፣ርሀብ ስደትና መፈናቀል ይበዛል። እንዲህ መሆኑም ችግሩን በተናጠል ብቻ አይወስነውም። በሀገርና ህዝብ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ የከፋ ያደርገዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከሰተው ኢኮኖሚያዊ ጫና ሁሌም ህይወቱን ከእጅ ወደአፍ ላደረገው ለፍቶ አዳሪ ፈተና እንደሆነ ነው። ይህ ብቻ አይደለም። አጋጣሚውን ተከትሎ በሚኖረው ሰውሰራሽና የኢኮኖሚ አሻጥር የመጀመሪያው ተጠቂ ሰፊው የህብረተሰብ ክፍል ይሆናል።

ሁሌም የዋጋ ጭማሪ ወሬ ሽው ባለ ቁጥር ለትርፍ ብቻ የሚቆሙ ስግብግቦች የመጋዘኖቻቸውን ሆድ ባሻቸው ሞልተው «ጆሮ ዳባ ልበስ» ማለታቸው ተለምዷል። እነዚህ ራስ ወዳዶች ገንዘብ ይሉትን ጥቅም አስካዩ ድረስ የሌላው መቆምና መውደቅ ችግራቸው ሆኖ አያውቅም። ባላቸው ላይ እየከዘኑ፣በደበቁት ቁልል እየጨመሩ በር ዘግተው ይስቃሉ።

ሁሌም ገበያውን በትርፍ ለመቆጣጠር የሚተጉ ወቅታዊ ስግብግቦች ቀን ጠብቀው የደበቁትን ይመዛሉ። እነሱ በወሰኑት ዋጋ ገበያውን ተቆጣጥርውም ተፈላጊነታቸውን ያበዛሉ። ይህ አይነቱ እውነት የከፋ በትሩን የሚያሳርፈው አሁንም ኑሮውን ሊሞላ በሚሮጠው ህብረተሰብ ትከሻ ላይ ይሆናል።

አብዛኛው ተጠቃሚ የሚፈልገውን ጠይቆ «የለም» በተባለ ቁጥር የእጁን አራግፎ ከአትራፊዎች መደርደሪያ መቃረሙ የተለመደ ነው። እነሱ በየአጋጣሚው አንዳሻቸው የሚያዙበትን ሸማች ጊዜና ወቅት እየጠበቁ ሲበዘብዙት ኖረዋል። ፡ድርጊታቸውን ተከትሎ የሚወሰደው እርምጃ ጠንካራና አስተማሪ ያለመሆኑም ችግሩ ስር እንዲሰድና እንዲስፋፋ ሲያመቻች ቆይቷል።

ወደቀደመው ጉዳዩ ልመለስ፡፤ወደሰሞኑ የነዳጅ ገበያ ሁኔታ። የዘንድሮ የሀምሌ ወር አመጣጥ ያላማራቸው አንዳንድ ህገወጦች ወሩን በክረምትነቱ ብቻ የተቀበሉት አይመስልም። በዚህ ወር መግቢያ ላይ ይተገበራል የተባለውን የነዳጅ ዋጋ ማስተካከያና ድጎማ ተከትሎ ገበያውን ለመቆጣጠር ዓይን ያወጣ ድርጊት መፈጸም ጀምረዋል።

ያለአግባብ የሚገኝ ትርፍን ለማግበስበስ ያሰቡ አንዳድ ህገወጦች በአደራ የተቀበሉትን የነዳጅ ሀብት በየጫካው ደብቀው ለሽያጭ ጭምር እያዋሉት መሆኑ ተደርሶባቸዋል። መንግስት እስከዛሬ ከነበረው ያነሰ የነዳጅ አቅርቦት አለመኖሩን ቢያረጋግጥም ድርጊቱ ግን ቀደም ሲል ይገባ የነበረው ምርት እንዲቀንስና ከፍተኛ የነዳጅ እጥረት እንዲከሰት ምክንያት ሆኗል፤

ከሰሞኑ የነዳጅና ኢነርጂ ሚኒስቴር እንዳስታወቀው መነሻቸውን ከጂቡቲ ያደረጉና አዲስ አበባ መድረስ የነበረባቸው 200 ነዳጅ ጫኝ ቦቴዎች በተለያዩ ጫካና መንደሮች ተደብቀው ተገኝተዋል። ይህን አግባብ ያልሆነ ድርጊት ሲፈጽሙ ከተገኙት መሀልም እስካሁን ስምንት የነዳጅ የጫኑ ቦቴዎች ለመንግስት ገቢ እንዲሆኑ ተደርጓል።

ከአዋሽ እስከሞጆ ባሉ መስመሮች በየጥሻው ተደብቀው የሚገኙትን የነዳጅ ቦቴዎች ለመቆጣጠርም አሳሽ ግብረሀይል ተደራጅቷል። ነዳጅ ማራገፊያ ቀናቸውን የተላለፉትን በመለየትም እርምጃ የመውሰዱ ሂደት ተጠናክሯል። ችግሩ ግን በዚህ ብቻ የሚቆም አይመስልም። በአሁኑ ጊዜ ወደሰሜን ኢትዮጵያ በተለይም ወደ ወልዲያና ቆቦ አካባቢዎች በህገወጥ መልኩ ነዳጅ እየተዘዋወረ ይገኛል።

ህገወጥ ድርጊቱን ተከትሎ ወልዲያ ከተማ ላይ ነዳጁን የሚያጓጉዙ ግለሰቦች ተይዘዋል። በአፋር ክልል በኩልም ወደትግራይ ሊገባ የነበረ ከአምስትሺህ ሊትር በላይ ነዳጅ በቁጥጥር ስር ውሏል። በዚህ ብቻ ያልተቋጨው ህገወጥነት ግን በዋግህምራና ሰሜን ጎንደር አካባቢዎች ተዛምቶ ቆይቷል።

ነዳጁ ለሽያጭ የሚውለው በበርሜሎች እየተቀዳና እየታሸገ ሲሆን የንግድ ሂደቱም በከፍተኛ ደረጃ እንደሚከናወን ታውቋል። አሁን የትራንስፖርትና ሎጅስቲክ ሚኒስቴር በነዳጅ አመላላሽ ተሽከርካሪዎች ላይ የእንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ /ጂፒኤስ/ ለመግጠም ዝግጅት በማድረግ ላይ መሆኑን እያስታወቀ ነው። ይህ አስገዳጅ የሆነ አሰራር አስኪተገበር ግን አስቸኳይና የማያዳግም እርምጃ ሊኖር ይገባል።

ሰሞነኛውን የነዳጅ እጥረት ተከትሎ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የነዳጅ ማደያዎች በሙሉ አቅማቸው እየሰሩ አይደለም። ይህን ችግር ከስሩ ለማጥራትም የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል። ዕለታዊ መረጃዎች እንደሚጠቆሙት ነዳጅ አራግፈው የቆሙ ቦቴዎች ተመልሰው ወደጅቡቲ የመሄድ ፍላጎት እየታየባቸው አይደለም።

ከጅቡቲ ወደ አዲስ አበባ መግባት የሚገባቸው አንዳንድ ቦቴዎችም ነዳጁን በመዳረሻ ከተሞች እያረገፉት ይገኛል። ይህ ከመወረስና ከተጠያቂነት ለመዳን የሚደረግ ሽሽትም ለችግሩ ስፋት አስተዋጽኦ እያበረከተ ነው።

በመንግስት በኩል ተደጋግሞ እንደሚነገረው በሀገሪቱ የነዳጅ አቅርቦት ይሉት ችግር የለም። እንዲህ በመሆኑም ተጨማሪ ነዳጅ ማስገባቱ አስፈላጊ አልሆነም። አሁንም ግን ከጅቡቲ አዲስ አበባ መድረስ የሚገባው የነዳጅ ሀብት በአግባቡ እየተጓጓዘ አይደለም።

ነዳጅ ለአንድ አገር የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከፍተኛውን ድርሻ የሚሸፍን አንቀሳቃሽ ሞተር መሆኑ ይታወቃል። በነዳጅ አምራችነታቸው የሚታወቁ አገራትም ከራሳቸው አልፎ በመላው ዓለም በሚያውሉት ሽያጭ በእጅጉ ሀብታምና ተጠቃሚ መሆን ችለዋል።

በሀገራችንም መንግስት ለነዳጅ ገበያ በዓመት እስከ ሶስት ቢሊየን ዶላር ወጪ ያደርጋል። በየቀኑም ከሁለት ነጥብ ሰባት እስከ ሶስት ሚሊየን ሊትር ነዳጅን ያሰራጫል። ከተለያዩ ኩባንያዎች ጋር በሚደረግ የውል ስምምነት ምርቱ በተገቢው መስመር ተደራሽ የሚሆንበት አሰራር ሲተገበር ቆይቷል።

የሰሞኑ የነዳጅ እጥረት የመስሪያቤቶችን አቅም በእጅጉ ተፈታትኗል። መስራት የሚገባው ሀይል ሰአታትን ለወረፋ በመስጠት ለኪሳራ እየተዳረገ ነው። ሰራተኛው በሰአቱ ፤ለስራው እየደረሰ አይደለም። በሀገሪቱ የትራንስፖርት ዝውውር ላይ ተጽዕኖው አጥልቷል።

ይህ ብቻ አይደለም። የሐምሌ ወርን ከነዳጅ ትርፍ ጋር ሊቀበሉት የቋመጡ ስግብግቦች የፈጠሩት ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ጫና ከኑሮ ውድነቱ ተዳምሮ ችግሩን አጉልቶታል። የህብረተሰቡን ጓዳ በማራቆት አቅምን ለመፈተን የሚኖረው ድርሻም ቀላል ሚዛን ላይ የሚቀመጥ አይሆንም።

ለዚህ አይነቱ ኤኮኖሚያዊ ራስ ምታት አስቸኳይ መፍትሄ በማበጀት የወረቀት ላይ ህጎች በተግባር ሊተረጉሙ፤ በጥቂት ግለሰቦች ፍላጎትና ቅጥ ያጣ ስግብግብነት የተፈጠረው ችግርም በ«ነበር» ሊታለፍ፣ በ«ይቅርታ» ሊረሳ አይገባም።

# ነፃ ሃሳብ



በሙዐዘ ጥበባት ዳንኤል ክብረት

# ሰኔ፣ ግብጽ፣ ዓባይና ኢትዮጵያ

የጥንት ግብጻውያን የዘመን መቁጠሪያ፣ ፀሐይን መሠረት ያደረገ ነበር። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ‹ዖን› የተባለችውን የፀሐይ አምላክ ያመልኩ ስለነበር ነው። የዚህች አምላክ ቤተ መቅደስ በሄልዮፖሊስ ይገኝ የነበረ መቅደስ ነው። በመጽሐፈ ፊሳልጎስ የሄልዮፖሊስ ቤተ መቅደስና የካህናቱ ሁኔታ ተገልጧል። ዖን ማለት ፀሐይ ማለት ነው። በአቡሻህር ሊቃውንት የሚታወቀውና ‹ጥንተ ዖን›(ቅድመ ፀሐይ፣ ቅድመ ብርሃን) የሚለው ቀመር ከዚሁ የተገኘ ነው።

ግብጻውያን አዲሱን ዓመታቸው የሚጀምሩት በመስከረም ነበር። ስሙንም ‹አኬት› ይሉታል ‹የዓባይ ውኃ የመድረሻ ወር› ማለት ነው። የኢትዮጵያ ክረምት የሚጀምረው በሰኔ ወር ነው። ለግብጽ ደግሞ ሰኔ ዝቅተኛው የዓባይ ውኃ የሚደርስበት ነው። ዓባይ የመጀመሪያውን አፈር ጭኖ ግብጽ የሚያደርሰው ለሦስት ወራት ተጉዞ በመስከረም ነው። በዚያ ጊዜ የኢትዮጵያን ጥቁር አፈር ተሸክሞ ስለሚደርስ፣ ስሙን ‹አውር› ይሉታል። ጥቁር ማለት ነው።

ከመስከረም እስከ ኅዳር በዓባይ ተጭኖ የመጣው የኢትዮጵያ አፈር፣ በዓባይ ዳርና ዳር የሚጠራቀምበት ጊዜ ነው። የግብጽ ገበሬዎች ዋናው ሥራቸው እርሱን ወደ ዳር እየወሰዱ መከመር ነው። ከታኅሣሥ ወር ጀምሮ ዋናው የሰብል ወቅታቸው ይሆናል። ኢትዮጵያ ውስጥ ደኅና ክረምት መኖሩን ግብጻውያን የሚያውቁት የዓባይ ወንዝ በአፈር ተሞልቶ እየተገማሸረ እስክንድርያ ከደረሰ ነው። ወደ ሰሜን ግብጽ ደርሶ ዓባይ በወፍ እግር መልክ(ዴልታ) ግራና ቀኝ አፈሩን ሲደፋው የግብጻውያን ደስታ ያን ጊዜ ይጀምራል።

ግብጻውያን ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያን ሁኔታ መከታተል የሚጀምሩት ከሰኔ ወር አንሥቶ ነው። የበልጉ ዝናብ ምልክቱን የሚሰጣቸው በሰኔ ስለሆነ። ከሰኔ በፊት ያለውን ወቅት ‹ሻሙ - ውኃ የሚንጠፋጠፍበት ወቅት› ይሉታል። በሰኔ ወር የኢትዮጵያ የአየር ሁኔታ መልካም ከሆነ የግብጻውያን መስከረም የተሳካ ይሆናል። በሰኔ ወር የኢትዮጵያ አየር ከተዛባ የግብጻውያን መስከረም ፈታኝ ይሆናል።

ይሄንን ሁኔታ ግብጻውያን ከዛሬ 5000 ዓመታት በፊት ጀምረው በየሄሮግላፊክሶቻቸው መዝግበውታል። ግብጽን በዝናብ የሚመግበው የግብጽ ‹አምላክ› በአፈ ታሪክ ‹ሃፒ› ይባል ነበር። የሚኖረው በተራሮች ነው(ምናልባትም ኢትዮጵያ ማለታቸው ይሆናል)። ሃፒ ከተቆጣ ዝናብ አይኖርም። ሃፒ ከተደሰተ ደግሞ ከሰኔ እስከ መስከረም አፈር የሞላው ውኃ ይወርዳል።

የዓባይ ግድብ እየተጠናከረ ከመጣበት ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ ሰኔ ለኢትዮጵያውያን የመከራ ወቅት ሆኗል። ሰኔ ወር ላይ ሀገራችን አስከፊ ግድያዎችን፣ ጭፍጨፋዎችንና መከራዎችን አሳልፋለች። በሰኔ ወር ታቅደው የከሸፉት የሽብርና የሳይበር ጥቃቶች ደግሞ የትየለሌ ናቸው። የግድቡን ሂደት ለማስተጓጎል ተሞክሮ የነበረውንና ኢንሳና ሌሎች የጸጥታ ተቋማት ተባብረው ያከሸፉትን የቢልዮኖች የሳይበር ጥቃት ማስታወሱ ጠቃሚ ነው።

### ስምን ሰኔ?

ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ ሰኔ ለግብጽ መንግሥትና ፖለቲከኞች የራስ ምታት ወር ሆኗል። በሀገራችን ‹በመስከረም የሚቆስል እግር፣ በሰኔ ዝንብ ይወረዋል› ይባላል። ኢትዮጵያ ሁለት ታሪክ ቀያሪ ተግባራትን በሰኔ ወር ታከናውናለች። በዚህ ዓመት ደግሞ በቢጋ ስንዴ ኢትዮጵያ ያገኘችው ውጤት በዓለም የናኘው በሰኔ ወር መሆኑ ሦስተኛ ራስ ምታት ሆኗል። የመጀመሪያው አረንጓዴ ዐሻራ ነው። ሁለተኛው ደግሞ የግድቡ ሙሌት።

አረንጓዴ ዐሻራ ኢትዮጵያ ለዘመናት ያጣችውን ሀብት የመጠበቂያና ለትውልድ የምትገነባውን የሕዳሴ ግድብ እድሜ ማራዘሚያ ነው። ግብጽ ለዘመናት ከኢትዮጵያ የዓባይን ውኃ ብቻ አይደለም ያገኘችው። ዓባይ ይዞት የማይሄደው ነገር አልነበረም።

ዕጽዋቱንና እንስሳቱን እየጫነ ይወስዳል። ታላላቅ ግንዶችን ጭኖ ይሄዳል። ‹ዓባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል› የተባለውም ለዚህ ነው። ግብጻውያን ለጽሕፈት የተጠቀሙበት ፓፒረስ ከደንገል ዛፍ የተገኘ ነው። የደንገል ዛፍ መነሻው ደግሞ የጣና ሐይቅ ነው። የዓባይ ውኃ የደንገልን ዛፍ ፍሬ ተሸክሞ ወስዶ በግብጽ ሰሜን በዴልታው ግራና ቀኝ ዘርቶታል።

ዓባይ ከመሬት ወለል ተነሥቶ የገባበትን ሸለቆ ለሚመለከት፣ በዘመናት ውስጥ ታጥቦ የሄደውን የኢትዮጵያ አፈር መገመት ይችላል። ከእንጦጦ ተራራ ጀምሮ በሚገኘው የዓባይ ቆሬ ውስጥ ያለው አፈር ሲጠረግ ነው የኖረው። በየዓመቱ ከ4 ቢልዮን ቶን በላይ ለም አፈር ይዞ ዓባይ ወደ ሱዳንና ግብጽ ይጓዛል። ይሄንን እንግዲህ ዓለም ከተፈጠረበት ዘመን ጀምሮ ባሉት ዓመታት ማባዛት ነው። ለዚህ ደግሞ በኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታዎች የሚዘንበው ዝናብና በየጊዜው እየተመናመነ የሄደው የደን ሀብት አስተዋጽዖ አድርገዋል።

ዓባይ መፍሰስ ተፈጥሮው ነው። የኢትዮጵያን ሀብት ይዞ መሄድ ግን አልነበረበትም። የፈሰሰው በተፈጥሮው፣ ሀብት ይዞ የሄደው ግን በስንፍናችን ነው። የግብጽ ገበሬዎች የኢትዮጵያን አፈር ከዓባይ ግራና ቀኝ እያወጡ ነው በስንዴ ምርታቸው ታዋቂ ለመሆን የበቁት። አረንጓዴ ዐሻራ ሲጀመር ይህ የሺ ዘመናት ታሪክ ነው የተቀየረው። በየዓመቱ ቢልዮን ችግኞች መተከላቸው ለግብጽ ፖለቲከኞች ሰኔን በመልካም እንዳያዩት አድርጓቸዋል። የአረንጓዴ ዐሻራ መስፋፋት በአንድ በኩል የተመናመነውን የኢትዮጵያን የተራራ ደን ይመልሰዋል።

ይህ ደግሞ ወደ ግብጽ እየታጠበ የሚወርደውን አፈር እየቀነሰው መሄዱ የማይቀር ነው። የደን ሽፋኑ ወዲያው ተጽዕኖ ባይኖረውም እንኳን ‹ኢትዮጵያ የአፈር ሀብቷን ለመጠበቅ ቢልዮን ዛፎችን ተከለች› የሚለው ዜና ግን ለግብጽ ፖለቲከኞች የሚመች አይደለም።

ይህ የአረንጓዴ ዐሻራ ጉዳይ የአፈር ሀብትን ከመጠበቅ ባለፈም የሕዳሴ ግድብ እድሜ እንዲራዘም የሚያደርግ ነው። የግድቦቻችን አንዱ ፈተና በደለል መሞላት ነው። የቆቃ ግድብ የገጠመው አንዱ ፈተና በደለል መሞላቱ ነበር።

የሐይቁ ጥልቀት ከ10 ሜትር ወደ 1 ሜትር መቀነሱን ባለሞያዎቹ ገልጠዋል። በዚህ የተነሣ ከሦስቱ ተርባይኖች አንዱ ሥራ እስከ ማቆም ደርሷል። የሚያመነጨው ኃይልም ከ42 ሜጋ ዋት ወደ 10 ሜጋ ዋት ቀንሶ ነበር። የቆቃ ግድብ የሚመጣበትን ደለል ለማስወገድ የተጠቀመው ዘዴ ደለልን ከሐይቁ ማስወገድ ነበር። ይህ ደግሞ ለሃያ ዓመታት ያህል በመቋረጡ ከፍተኛ ኪሣራ ውስጥ ገብቷል። አረንጓዴ ዐሻራ ባህል እየሆነ ካልመጣ የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ዕጣ ፈንታም ይሄ ይሆናል። ለዚህ ነው የግብጽ ፖለቲከኞች አረንጓዴ ዐሻራን በፖለቲካ ጉሮሯቸው ላይ የቆመ አምስት ቁጥር አድርገው የቆጠሩት።

የግብጽ የማኅበራዊ ሚዲያ አቀንቃኞች መነሻቸውን ከሜዲትራንያን ደሴቶች ባደረጉ ዘመቻዎች አረንጓዴ ዐሻራን የሚቃወሙ ቅስቀሳዎችን የጀመሩት በግንቦት ወር አጋማሽ ነው። በሰኔ ወር ግን በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመሩ መምጣታቸውን የሳይበር ደኅንነት መረጃዎች ያሳያሉ።

የኢትዮጵያን የሳይበር ደኅንነት የሚያስከብሩ ተቋማት መረጃዎች እንደሚያሳዩት ‹ቀይ ዐሻራ› የሚለውና አረንጓዴ ዐሻራን ለመቃወም የተጀመረው ዘመቻ የተፈጠረውም የሚመራውም በሜዲትራንያን ከምትገኝ አንዲት ደሴት ነው።

የሚያስተጋቡትም የግብጽ የማኅበራዊ ሚዲያ አካላት ናቸው። በርግጥ ሰሞኑን የግብጽ የማኅበራዊ ሚዲያ መሪዎች ካይሮ ላይ ባደረጉት ስብሰባ ይሄና ሌሎችም ፀረ ኢትዮጵያ የማኅበራዊ ሚዲያ ዘመቻዎቻቸው የሚጠበቀውን ያህል ውጤት እንዳላመጡ ገምግመዋል።

የኢትዮጵያ ከፍተኛ ተራሮች የክረምት ዝናብ የሚያገኙት ከሰኔ ወር ጀምሮ ነው። ‹ሰኔ ግም አለ› ይባላል። ተራሮች ልምላሜ የሚጀምሩበት ወቅት በመሆኑ የወሩ ስም ‹ሠነየ - አማረ› ሊባል ችሏል። ሰኔ ማለትም ያማረ፣ የለመለመ ማለት ነው።

ከሰኔ ወር ጀምሮ የኢትዮጵያ ዝናብ በመካከልና በሰሜን ተራሮች ላይ መዝነብ ሲጀምር ከሐምሌ ወር ጀምሮ ደግሞ ታችኛው የዓባይ ክፍል ማለትም በምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በተለይ በቤኒሻንጉል ጉምዝ የሚገኘው ታኅታዩ የወንዙ ክፍል በውኃ መጥለቅለቅ ይጀምራል። ኢትዮጵያ የዓባይ ግድብ የሙሌት ዝግጅቷን የምትጀምረው በሰኔ ወር ነው ብለው የግብጽ ፖለቲከኞች ያምናሉ። ስለዚህም ፖለቲካዊ ጭንቀት ውስጥ ይወድቃሉ።

ካለፉት አራት ዓመታት ጀምሮ የግብጽ ሚዲያዎችና ግብጻውያን የሰኔ ወር የኢትዮጵያን የሕዳሴ ሙሊቶች መከታተል የሚጀምሩበት ወር ነው። የግብጽ የመማሪያ መጻሕፍት ዓባይ የሚመነጨው ከደቡብ ግብጽ ነው ሲሉ ነው የኖሩት። ግብጽ የዲፕሎማሲ ግንኙነቷን ከሰሜኑ ንፈቀ ክበብ እንጂ ከደቡቡ ንፍቀ ክበብ ጋር አጠናክራ አታውቅም።

የታችኞቹ ተፋሰስ ሀገሮች በዓባይ ውኃ ላይ ተጽዕኖ ያመጣሉ ብላ አስባ አታውቅም። ግብጽ ከአፍሪካ ሀገሮች ጋር ለዲፕሎማሲ ግንኙነት መሯሯጥ የጀመረችው ከሕዳሴ ግድብ በኋላ ነው። በ2009 ዓም ካይሮ ላይ ተደርጎ በነበረው የሕዝብ ውይይት ‹የአፍሪካ ሀገሮች በዓባይ ላይ ይሄንን ያህል ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ከሆነ እስከ ዛሬ ድረስ የተጠናከረ ዲፕሎማሲ ለምን አልመሠረትንም› ሲሉ የግብጽ ታላላቆች ጠይቀው ነበር።

ሰኔ የግብጽ ፖለቲካ የመበጥበጫ ወር ነው። የግብጽ የደኅንነት ሰዎች ከኢትዮጵያ ባንዳዎች ጋር በመሆን በከፍተኛ ሁኔታ ሀገሪቱን ለማመስ የሚነሡት በሰኔ ወር ነው። የእሥራኤሉ መስፍን ሳምሶን ‹በጥጃዬ ባላረሳችሁ፣ የዕንቆቅልሼን ትርጓሜ ባላወቃችሁ› እንዳለው፣ የውጭ ኃይሎች ኢትዮጵያን እንዲያጠቁ የመረጃና የሎጂስቲክስ ድጋፍ የሚሰጧቸው፣ በመዋቅርም ከመዋቅርም ውጭ ያሉት የውስጥ ባንዳዎቹ ናቸው። የውጭ ጠላቶችና የውስጥ ባንዳዎች ተደምረው በተለይም ከሰኔ ወር ጀምረው ጆሮ ጭው የሚያደርጉ ሤራዎችን ያውጠነጥናሉ። የከሸፈው ይከሽፋል፤ ያመለጠው ደግሞ የሕዝቡን ልብ ይሰብራል።

ሰኔ 16 ቀን 2010 ዓም (በመስቀል አደባባይ)፣ ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓም (በባሕርዳር ከተማና በአዲስ አበባ)፣ ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓም የሐጫሉ ግድያና በብዙ ከተሞች የተፈጠረው ግድያና የንብረት ውድመት)፣ ሰኔ 2013 (የሕወሐት ዳግም ወረራ)፣ ሰኔ 11 2014 ዓም (በምዕራብ ወለጋ ጊምቢ እና ቄለም የተከሠተው ጭፍጨፋ)። እነዚህ ሁሉ ‹ሰኔና ሰኞ› ገጥመው የተፈጠሩ አይደሉም።

ዓባይ፣ ግብጽና ሰኔ የሚገጥሙበት ወቅት ሆኖ እንጂ። ከሰሞኑም በዚሁ በሰኔ ወር በእስልምናም በኦርቶዶክስም ቤቶች ጫና የሚፈጥሩ ነገሮች እየታዩ ነው። ከሱዳን በኩል በድንበር በኩል በዚሁ በሰኔ ወር የተፈጠረው ነገርም ተጨማሪ ጫና ለመፍጠር የተፈለገ ነበር።

የግብጽ ሚዲያዎችም የሕዳሴውን ግድብ ዜና ትተው በኢትዮጵያ ውስጥ ስለደረሰው እልቂት፣ ግድያ፣ ጭፍጨፋ ማውራት ያበዛሉ። ከሰሞኑ በወለጋ የደረሱትን እልቂቶችና በሱዳን ድንበር የተከሠተውን ነገር፣ የግብጽ ሚዲያዎች እንዴት ተሯሩጠው እንደዘገቡት ማስታወስ ጥሩ ነው።

በአንድ በኩል ኢትዮጵያን በማዳከም ወደፊት እንዳትቀጥል ለማድረግ፤ በሌላ በኩል የግብጽን ሕዝብ በሌላ አጀንዳ ለመያዝ ይጠቀሙበታል። በማኅበራዊ ሚዲያ አዝማቾቻቸውና ዘማቾቻቸው በኩልም በኢትዮጵያ ላይ ጫና ማሳደር ይጀምራሉ። በተደጋጋሚ ባለፉት ሁለት ዓመታት የጸጥታው ምክር ቤት የሕዳሴው ግድብ በተመለከተ በሰኔ ወር እንዲጠራ ተደርጓል።

ነገሩ ሁሉ ያማል፤ ያቆስላል፤ ልብ ያደማል፤ ግን መፍትሔው ከስሜታችን በላይ ከማሰብ የሚገኝ ነው። ሰው ችግሩን ከዐቅሙ በላይ አግዝፎ ካየው ከመፍትሔ ይልቅ ራሱን ወደ ማጥፋት ያዘነብላል። ራሳቸውን የሚያጠፉ ሰዎች ብዙ ጊዜ ችግራቸውን ከመፍትሔ በላይ አድርገው የሚያስቡ ናቸው። ማኅበረሰብም ይህ ራስን የማጥፋት የሥነ ልቡና ቀውስ ሊገጥመው ይችላል።

የጸጥታ አካላትን ይበልጥ ማጠናከርና አብረናቸው መቆም አለብን። ድካማቸውን እያገዝን፣ ፈተናቸው እየተረዳን፤ አብረናቸው መጓዝ አለብን። በየአካባቢው ሕዝብ ተደራጅቶ ሀገሩንና አካባቢውን ከጸጥታ ኃይሎች ጋር እንዲጠብቅ ማድረግ ይገባናል። በሕዝብ ውስጥ አጥፊ ሰዎች አሉ እንጂ፣ አጥፊ ሕዝብ የለም። ሕዝብ የግለሰቦችንና የቡድኖችን ዕዳ እንዲሸከም ማድረግ የለብንም። ይህ ጠላትን እንጂ ሕዝብን አይጠቅምምና።

ጥርሳችንን ነክሰን የሕዳሴው ግድብ ግንባታ አጠናቅቀን፣ ተፈላጊውን ሙሌት ጨርሰን፣ አረንጓዴ ዐሻራን ባህል አድርገን፣ በብሔራዊ ምክክሩ አማካኝነት ልዩነቶቻችንን አጥብበን፣ ከብሔራዊ ምክክሩ በኋላ የሀገሪቱን ሕጎች ፈትሸን፣ አሻሽለን፤ ኅብረ ብሔራዊ አንድነቷን የጠበቀች ጠንካራ ኢትዮጵያን በጋራ እስካልገነባን ድረስ መፈተናችን አይቀሬ ነው። በተለይም ከሰኔ እስከ ነሐሴ ያሉት ሦስት ወራት ወሳኝ ጊዜያት ናቸው።

አናጺ ሚስማሩን በመዶሻው የሚመታው ከመዶሻው በላይ ሚስማሩን ጠልቶት ወይም ከሚስማሩ በላይ መዶሻውን ወድዶት አይደለም። ለእርሱ ዋናው ጉዳይ ጥቅሙ ነው። መዶሻው ከድንጋይ የተሻለ መምቻ ሆኖ ስላገኘው ብቻ ይጠቀምበታል። የተሻለ መምቻ ካገኘ መዶሻውን ይወረውረዋል። የተሻለ ማጣበቂያ ካገኘም ሚስማሩንም ይወረውረዋል። መዶሻውም አገልግሎቱን ከጨረሰ፣ በእሳት ቀልጦ ለሌላ ነገር እንዲውል እርሱን ለአንጥረኛ ይሰጠዋል። እርሱ መዶሻ በነበረ ጊዜ ሌላውን ሲቀጠቅጥ እንደነበረው ሁሉ፣ እርሱም በተራው በሌላ መዶሻ ይቀጠቀጣል።

ጠላት አንዳችንን የሌላችን መምቻና መግደያ፣ አንዳችንን የሌላችን ማጥፊያና ማስለቀሻ ሲያደርግ ከሟቹ ይልቅ መግደያውን፣ ከአልቃሹ ይልቅ ማስለቀሻውን የበለጠ ወድዶትና አክብሮት አይደለም። ለጠላት የተመቸ መሣሪያ ሆኖ አግኝቶት ነው። ነገ በተራው ሌላ የተሻለ መሣሪያ ሲያገኝ እርሱንም አልቃሽና ሟች ማድረጉ አይቀሬ ነው።

ለዚህ ሁነኛው መፍትሔ ሁላችንም ለሁላችንም ዘብ መቆም ነው። ጠላቶቻችን ምንም ያህል ግዙፍና አስቸጋሪ ቢሆኑም፣ የመፍትሔውን መንገድ ካወቅነው፣ ቀድመናቸው መሮጥ እንችላለን። ‹መንገድ የምታውቅ አይጥ ከፈረስ በላይ ትሮጣለች› እንደሚባለው።

# «ሕወሓት በፈጠረው ችግር የትግራይ ሕዝብ መበደልም ሆነ መጎዳት የለበትም ፤ የትኛውም ማህበረሰብ ሰላሙ ሊከበርለት እና ሊጠበቅለት ይገባል»

*- ዶክተር መብራቱ ዓለሙ*
*የፖለቲካ ፓርቲዎች ማህበር ፕሬዚዳንት*

**ምሕረት ሞገስ**

የለውጡ መንግሥት ወደ መሪነት ከመጣ በኋላ በአገሪቱ የሥልጣን መንበር ላይ ቁንጮ የነበረው ሕወሓት ከፌዴራል መንግሥቱ ጋር የነበረው ግንኙነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሻከረ ሄዶ ጦርነት እስከ መክፈት ደርሷል። ቀድሞም ሕወሓት እየሄደበት ያለው መንገድ ትክክል አለመሆኑን ለማሳወቅ እና ደም አፋሳሽ ጦርነት ለማንም እንደማይበጅ ለመጠቆም ለአገር የሚበጀውን በመምረጥ የፌዴራል መንግሥት ተደጋጋሚ የሠላም ጥሪዎችን ሲያቀርብ ቆይቷል።

ከ11 ጊዜ ያላነሰ የሰላም ጥሪ የተደረገለት ሕወሓት የሃይማኖት አባቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ ታዋቂ ሰዎች እና የእናቶችን ጥሪ አሻፈረኝ በማለት በእምቢተኛነቱን ቆይቷል። ከዚያም አለፍ ብሎ በትግራይ የተናጠል ምርጫ ማካሄድን ጨምሮ ከፌዴራል መንግሥቱ ጋር ያለውን ግንኙነት ይበልጥ ማደፍረሱን ተያያዘው። የየዕለቱን ውጥረት ከማባባስ አልፎም በጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ትግራይ ክልል ውስጥ አብሮት ከ20 ዓመታት በላይ በኖረው፣ በማህበራዊ ጉዳይና በበጎ አድራጎት ሥራ ከጎኑ ሆኖ ሲያገለግለው የኖረውን የሰሜን ዕዝ የመከላከያ ሠራዊት ላይ ጥቃት ፈፀመ። ድርጊቱ ቅጽበታዊና አስደንጋጭ፤ መንግሥትም በዚያው ልክ ዝግጅት ያላደረገበት ቢሆንም ግን ከሦስት ሳምንታት በላይ ባልቆየ ሕግ የማስከበር እርምጃ ሕወሓትን መቆጣጠር ተችሏል።

የፌዴራል ሠራዊት በሕወሓት የሽብር ቡድን ላይ የበላይነትን ተቀናጅቶ መቀሌን ከተቆጣጠረ በኋላ፤ ጊዜያዊ አስተዳደር ቢቋቋምም ክልሉ መረጋጋት አልቻለም። የሽምቅ ጥቃት መቀጠሉን ተከትሎ የክልሉ ሕዝብም እንዳይጎዳ በማሰብ ለሰላም ሲል መንግሥት የተናጠል ተኩስ አቁም አውጆ ሠራዊቱን ከትግራይ ክልል አስወጥቶም ነበር።

ነገር ግን መንግሥት ለትግራይ ሕዝብ በማሰብ የማሰላሰያ ጊዜም እንዲሁን የሰጠውን የሰላም መንገድ ጥሶ ሽብር ቡድኑ በአገሪቱ ሰላም እንዳይሰፍን በየአቅጣጫው ትንኮሳውን ተያያዘው። የትግራይ አዋሳኝ የሆኑት የአፋርና የአማራ አካባቢዎች በመውረር ጦርነቱን አስቀጠለ። በዚህም በሁሉም ቦታ የብዙዎች ሕይወት ተቀጠፈ። በሕወሓት የጥፋት ቡድን ከፍተኛ ቁሳዊ ውድመት ደረሰ። የደሴና የኮምቦልቻ ከተሞችን በመቆጣጠር ከሸኔ ጋር በመተባበር ወደ መሃል አገር ለመግባት በተለይ በአፋር በኩል ቁልፍ ከተማ የሆነችውን ጭፍራን ይዘው አዲስ አበባን ከጂቡቲ ጋር የሚያገናኘውን መንገድ ለመቆጣጠር ቢዋጉም አልተሳካላቸውም። በተቃራኒው የፌዴራል መንግሥቱ ጠንካራ እርምጃ መውሰድ በመጀመሩ በመጡበት እግራቸው መልሰው ወደ ኋላ ፈረጠጡ። የአፋር እና የአማራ ክልልን መልቀቅ ግዴታ ሆነባቸው። ነገር ግን አሁንም ድረስ የችግሩ ሰንኮፍ አልተነቀለም። የትግራይ ሕዝብም ከስቃይና ረሀብ ተላቆ የሰላም እንቅልፍ አላገኘም።

ይሁን እንጂ ሕወሓት በሌላ በኩል ደግሞ ሸኔን በደንብ በማገዝ እና በማደራጀት የኦሮሚያ ክልልን ማመስ ሥራዬ ብሎ ተያያዘው። በኦሮሚያ ክልሉ የተለያዩ ዞኖች አርሶ አደሮችንና ሌሎች ሰላማዊ ወገኖችን ጭምር መግደል፣ መዝረፍና ማገት እንዲሁም የከፋ ችግር ማድረስ የየዕለት ዜና ሆነ። በክልሉ በሚኖሩ ሕዝቦች አሰቃቂ ግድያና ዘረፋ ሲያካሂድ በአሸባሪው ሸኔ የጥፋት ቡድን በርካታ ዜጎችን መግደል እና ማቁሰልን፤ ወንድ ሴት ሕፃን ሳይል በአሰቃቂ ሁኔታ የዜጎችን ሕይወት ማጥፋት አንዳንዴም የዘር ፍጅት እንዲነሳ በሚቀሰቅስ መልኩ ግድያን መፈፀም ተዘወተረ።

‹‹ኢትዮጵያውያን ወገኖችም የራሳቸውን ችግር ለመፍታት እስከፈቀዱና ለመተባበር እስከቆረጡ ድረስ የሰላም ጉዞው የቱንም ያህል ዋጋ ቢጠይቅ ለስኬት እንደምንበቃ ጥርጥር የለንም። ›› ያለው መንግሥት ለሰላም ሲል ዝምታን ቢመርጥም በተቃራኒው ለጥፋት አላማ የቆመው አካል ፈቃደኛ ባለመሆኑ አሁን ደግሞ በርካታ ንጹሀን ዜጎች በሸኔ የሽብር ቡድን ሕይወታቸው እያለፈ ይገኛል።

መንግሥት ተደጋጋሚ የሠላም ጥሪዎችን ያቀርባል፤ በሰሜን በኩል ብቻ ሳይሆን በሌሎችም፣ በደቡብም ሆነ በምዕራብ ኦሮሚያ፣ በጋምቤላም ሆነ በሌላ አካባቢ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ ሰላም ይሻላል በሚል በሆደ ሰፊነት ነገሮችን በትዕግስት ለማለፍ ሞክሯል። ሆኖም ለሰላም ብቻ ቅድሚያ መስጠቱ ወንጀለኞች እና ክፉ ድርጊት ፈፃሚዎች ከሰላም ይልቅ ጥፋት ብቻ የሚታያቸው አሸባሪዎች የልብ ልብ እየተሰማቸው የበለጠ ወንጀል እየፈፀሙና ሕዝብ እየተጎዳ፤ የሰዎች ሕይወት እየጠፋ መሆኑን በመጥቀስ መንግሥት እርምጃዎች ላይ መጠንከር አለበት በማለት የሚሰጠውን አስተያየት በሚመለከት እና በዚህ ቀውስ ላይ የጥላቻ ንግግር እና ሐሰተኛ መረጃ ከታከለ ምን ያህል ጥፋት ሊያስከትሉ ይችላል? እንዲሁም በዋናነት መፍትሔው ምን መሆን አለበት ስንል ከፖለቲካ ፓርቲዎች ማህበር ፕሬዚዳንት ዶክተር መብራቱ ዓለሙ ጋር የነበረንን ቆይታ እንሆ ብለናል።



ፎቶ፡ ገብሩ ገብሬ

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ መንግሥት ለሰላም የሰጠውን ትኩረት አሁንም ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት እያደረገ ያለውን የሰላም ሂደት እንዴት አገኙት?**

**ዶክተር መብራቱ፡-** እንግዲህ የኢትዮጵያ መንግሥት ሰላም ላይ እየሠራሁ ነው ይላል። በደንብ ትኩረት መስጠቱን ለማሳወቅ የሰላም ሚኒስቴር አቋቁሟል። ነገር ግን መንግሥት ሠርቻለሁ እያለ ባለው ልክ ሰላም መጥቷል ወይ ? የሚል ጥያቄ ከተነሳ መልሱን የትኛውም ኢትዮጵያዊ ሊመልሰው ይችላል። ብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ ከሃይማኖት አባቶች እና የአገር ሽማግሌዎች ጋር ተደጋጋሚ ውይይት ይደረጋል። ከልሒቃን ጋርም ተደጋጋሚ ውይይቶች እየተደረጉ ናቸው። ነገር ግን ተጨባጭ ሰላም ማምጣት ላይ ግን ብዙ የተሔደበት አይመስልም። በዚህ የተነሳ አሁንም ድረስ የዜጎች ሞት እና መፈናቀል መቆም አልቻለም።

**አዲስ ዘመን፡- ትክክል ነዎት! አሁንም የዜጎች ሞት እና መፈና ቀል አላቆመም። ነገር ግን መንግሥት ተደጋጋሚ የሠላም ጥሪዎችን ከማቅረብ አልተቆጠበም። ለምሳሌ ለሕወሓት የሽብር ቡድን ከ10 ጊዜ በላይ የሃይማኖት አባቶችን፣ ሽማግሌዎችን፣ ታዋቂ ሰዎችን እና እናቶችን… በመላክ ከጦርነት ይልቅ ሁሉም ነገር በሠላም እንዲያልቅ ተደጋጋሚ ጥያቄ አቅርቧል። አልፎ ተርፎ ለሰላም ባለው ፍላጎት የታሰሩ የሕወሓት ከፍተኛ አመራሮችን ጭምር ፈትቷል። ጦርነቱ ከተጀመረ በኋላም በተደጋጋሚ ሰዎች ከሚያልቁ በሠላም እንጨርስ በማለት ተደጋጋሚ ዕድል ከፍቷል። ከእዛኛው ወገን ያለው ምላሽ ግን ሁሉም እንደሚያየውና እንደሚሰማው ነው። አሁንስ ምን ሲሆን ይችላል ብለው ይገምታሉ?**

**ዶክተር መብራቱ፡-** እውነት ነው። የአንድ ወገን ሰላም መፈለግ ብቻ አዋጪ አይሆንም። የሌላኛውን ፍላጎት በደንብ መረዳት እና ማየት ተገቢ ነው። ሁለተኛ የሰሜኑ ጦርነትን በተመለከተ መንግሥት የወሰደው እርምጃ ትክክል ነው። ጥቃት ሲፈፀም ቢያንስ የአፀፋ መልስ መስጠት የአንድ መንግሥት ግዴታ ነው። ነገር ግን ከዛ ጋር ተያይዞ ማህበረሰቡ ጋር የተፈጠሩ ችግሮችን ቶሎ መፍታት ተገቢ ነው የሚል እምነት አለኝ።

በመንግሥታት ወይንም በፖለቲካ ልሒቃን መካከል በሚፈጠር ግጭት ብዙ ሕዝብ እና ማህበረሰብ መጎዳት የለበትም። አሁን እንደሚታወቀው የትግራይ ሕዝብ መብራት፣ ስልክም ሆነ ውሃ ምንም የለውም። ምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ እንኳ የሚታወቅ ነገር የለም። ሕወሓት በፈጠረው ችግር የትግራይ ሕዝብ መበደልም ሆነ መጎዳት የለበትም። የትኛውም ማህበረሰብ ሰላሙ ሊከበርለት እና ሊጠበቅለት ይገባል። ከዚያ አንፃር አሁንም ብዙ ምስቅልቅል ያለባቸው ነገሮች ከፊታችን ያሉ ይመስለኛል። ስለዚህ እንደተባለው በትክክል ሰላም ማስፈን የሚቻለው በአንድ ወገን ብቻ አይደለም። በሁለቱም ወገን የሰላም ፍላጎት መምጣት አለበት። ይህ ደግሞ ሊመጣ የሚችለው በድርድር፣ በሽምግልና ወይም ወደፊት ይመጣል ተብሎ በሚታሰበው አገራዊ ምክክር በመግባባት ችግሮች ይፈታሉ፤ ወይም ይቀረፋሉ ተብሎ ይጠበቃል።

**አዲስ ዘመን፡- መንግሥት በደቡብም ሆነ በኦሮሚያ፣ በጋምቤላም ሆነ በሌላው አካባቢ በሚከሰቱ የሰላም መደፍረሶች የሚወስደው እርምጃ በቂ ነው ይላሉ? በተለይ የሰዎችን በሕይወት የመኖር መብት ከማስጠበቅ አንጻር እንዴት ያዩታል?**

**ዶክተር መብራቱ፡-** መንግሥት የመጀመሪያ ተልዕኮ መሆን ያለበት የዜጎች በሰላም ወጥቶ መግባት፣ ዜጎችን ማረጋጋት እና የመኖር ዋስትናን ማረጋገጥ ነው። በዚህ ረገድ ሥራ አልተሠራም ማለት አይቻልም። ነገር ግን የምናየው ደም መፋሰስ እና የሰዎች እልቂት አሁንም ድረስ አላቆመም። ይሔ ደግሞ የሚያሳየን መንግሥት መሥራት ያለበትን ያክል ወርዶ አለመሥራቱን ነው። ለምሳሌ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል አካባቢ ጅምላ ጭፍጨፋዎች እና የሰዎች ሞት እንዲያውም ጅምላ ቀብር ሁሉ ነበር። በክልሉ ኮማንድ ፖስት ተቋቁሞ ነበር። የተቋቋመው ኮማንድ ፖስት ሦስት ዓመት ቢሞላውም አሁንም የዜጎች ሞት መቆም አልቻለም። መፈናቀልም አልቆመም።

መሻሻሎች ቢኖሩም ችግሩ አሁንም አልተቀረፈም። የፀጥታ ኃይሎችም እየተጎዱ እና እየሞቱ ነው። ስለዚህ በፍጥነት ወደ አገራዊ ምክክር ተገብቶ ተፋላሚ ኃይሎችም ወደ ጠረጴዛ ዙሪያ መጥተው ሰላም እና እርቅ ይፈፀማል የሚል እምነት ነበረኝ። ነገር ግን ብሔራዊ ምክክሩም ወደ ኋላ እየተጎተተ ነው። ስለዚህ መንግሥት እየወሰደ ያለው እርምጃ ችግር ሲከሰት ችግሩ እንዴት

# ወቅታዊ



ላስቁመው እያለ ነው። አስቀድሞ ለመከላከል ብዙ ትኩረት እየተሰጠ አይደለም። ችግሩ ሲከሰት ሔዶ ማዳፈን እና ማፈን፤ እዚያ አካባቢ ያለውን መረጃ መደበቅ ትክክል አይደለም። ይህ ከአሁኑ ማስተካከያ ካልተደረገለት የእዚህች አገር ዕጣ ፈንታ ወደ ቀውስ ያመራል። ስለዚህ መንግሥት ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ባለድርሻ አካላት ማለትም የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ተቋማት፣ መገናኛ ብዙኃን እና በአጠቃላይ ሁሉም ተረባርቦ ካልሠራ የወደፊት እንቅስቃሴያችን ውጤት ካለማምጣት ባሻገር ሁኔታው በዚሁ ከቀጠለ ትንሽ የሚያሰጋ ይመስለኛል።

**አዲስ ዘመን፡- ቀድሞ መከላከልን በተመለከተ ሁለት ሃሳቦች ይሰጣሉ። አንደኛው መንግሥት ከእርምጃ ይልቅ ሰላም ላይ ትኩረት ማድረጉ ችግሩ የበለጠ እንዳይባባስ ረድቷል የሚሉ ቢኖሩም በተቃራኒው ለሰላም ቅድሚያ መስጠት በሚል ሰበብ መንግሥት ፈጠን ብሎ እርምጃ አለመውሰዱ እንዲያውም ድርጊቱን ፈፃሚዎች የልብ ልብ እየተሰማቸው የበለጠ ወንጀል እንዲፈፅሙ ሕዝብ እንዲጎዳ እና የሰዎች ሕይወት እንዲጠፋ እያደረገ ነው የሚሉ ወገኖችም አሉ። እርሶ ቀድሞ መከላከል ሲሉ ምን ማለትዎ ነው? በደንብ ያብራሩልኝ።**

**ዶክተር መብራቱ፡-** ቀድሞ መከላከል ማለት የትኛዎቹም ታጣቂ ኃይሎች ከመንግሥት ጋር ጥላቻ ያላቸው የተደራጁ ኃይሎች ሊሆኑ ይችላሉ ወይንም የውጭ ኃይሎችም ሊሆኑ ይችላሉ እነዚህ አንድ ማህበረሰብ ውስጥ ገብተው የሆነ ጉዳት እና ጥቃት እስኪፈፅሙ ድረስ የእኛ የፀጥታ መዋቅር ምን ላይ ነው? የክልሉ ፖሊስ አለ፤ ፌዴራል ፖሊስ አለ፤ ልዩ ኃይል አለ፤ መከላከያ አለ፤ ኮማንዶ አለ። ይህ ሁሉ ባለበት አገር አንድ ሰፈር ተገብቶ ብዙ ሰዎች ላይ እርምጃ ተወስዷል። ነገር ግን ይሔ አሰቃቂ ተግባር ተከሰተ ተብሎ ዜና ከመሠራቱ በፊት የደህንነት ተቋሙ ምን ይሠራል የሚል ጥያቄ ማንሳት ይቻላል። ሁለተኛም ለማህበረሰቡ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ በደንብ ተከናውኗል? ብዬ አላምንም የተለያዩ የማህበረሰቡ ጥያቄዎች አሉ።

ከሕዝቡ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች ይኖራሉ። መንግሥት እነዚህን ጥያቄዎች እስከታች ድረስ ወርዶ መመለስ ካልቻለ ማህበረሰቡ የሽፍታ መደበቂያ ዋሻ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ማህበረሰቡ የሚፈልገው ለውጥ መጥቶለታል? የተባለው ለውጥስ በእርግጥ ማህበረሰቡ ላይ ለውጥ አሳይቷል ወይ? በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካው በትክክል በንቃት ኅብረተሰቡ እየተሳተፈ ነው? ወይንስ ምንድን ነው? የወጣቱ ፍላጎትስ እንዴት ይታያል? የወጣቱ ቁጥር እየጨመረ እና ሥራ አጥ እየተበራከተ ነው። በሌላ በኩል የኑሮ ውድነት አለ። ይሄ በሙሉ ማህበረሰቡን እያንገሸገሸው ነው። እነዚህ ሁኔታዎች በሙሉ ችግሮችን ሊያባብሱ ይችላሉ። ስለዚህ እነዚህን ሁሉ ነገሮች አስቦ በማስተዋል ምንድን ነው? ብሎ ተቀምጦ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምን ሊያግዙን ይችላሉ? ሲቪክ ማህበረሰቡ ምን ሊያግዘን ይችላል? ዓለም አቀፍ ተቋማት ምን ሊያግዙን ይችላሉ? ብሎ አቅዶ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል።

አሁን ግን ከታች ሲነድ እሳቱን የማዳፈን እና የማጥፋት እንቅስቃሴዎች እየታዩ ናቸው። ስለዚህ መንግሥት ይህንን ትኩረት ሰጥቶ መሥራት አለበት። እኛም የፖለቲካ ፓርቲዎች መንግሥትም ላይ ጫና ፈጥረን፤ ማህበረሰቡ ንቁ እንዲሆን ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኝ ብንሠራ ምናልባት የችግሩ ስፋት እና ጥልቀት እየቀነሰ ይሔዳል የሚል እምነት አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- በጋምቤላም ሆነ በኦሮሚያ ወለጋ ሳይም ሆነ በሌሎች አካባቢዎች እየታየ እና እየተፈፀመ ያለው ድርጊት ብዙ ኢትዮጵያውያንን ስጋት ውስጥ መጨመሩ አይታበልም። በዚህ ላይ ሀሰተኛ መረጃና የጥላቻ ንግግር ከተባባሰ እና ከቀጠለ አደጋው እስከምን ደረጃ ሊደርስ ይችላል ይላሉ?**

**ዶክተር መብራቱ፡-** እኔን የሚያስጨንቀኝ የጥላቻ ንግግሩ አይደለም። የጥላቻ ንግግሩን ያመጣው ምንድን ነው? የሚለው ነው። የጥላቻ ንግግርን ያመጣው የጥላቻ ፖለቲካ ነው። ሌላው በሕዝብ እና በመንግሥት መካከል እምነት ከሌለ የጥላቻ ንግግሮች እጅግ በጣም እየሰፉ ይሔዳሉ። የጥላቻ ንግግር እና የሃሰተኛ መረጃ ስርጭት ላይ የወጡ ሕጎች እንደሚታዩት ገና በደንብ ተግባራዊ ሆነው እርምጃ እየተወሰደ አይደለም። ስለዚህ የጥላቻ ንግግሮች ለምን ይፈጠራሉ? የሚፈጥራቸውስ ማን ነው? ኅብረተሰቡስ ለምን ይቀበላቸዋል? እነዚህ የሀሰት መረጃዎች እና የጥላቻ ንግግሮችስ ለምን ይሰራጫሉ የሚለው ላይ በደንብ መታሰብ አለበት። ይህ ደግሞ የመጣው ትክክለኛ መረጃ ለኅብረተሰቡ መገናኛ ብዙኃኑ እያቀረቡ ስላልሆነ ነው።

መንግሥት ለምን ይፈራል? ምዕራብ ወለጋ እና ጋምቤላ ላይ የተፈፀመው ነገር መገናኛ ብዙኃኑ እዚያው ቦታው ላይ ሆነው ያለውን እውነታ ቢገልፁ ችግሩ ምንድን ነው? ሕዝቡ የሚፈልገው እውነታውን ነው። ተቸገርኩ እርዱኝ ቢባል የእኛ ሕዝብ ይረዳል፤ ያግዛል። የእኛ ሕዝብ ለአገሩ እና ለሃቅ ሟች ነው። ከዚያ አንፃር እኔ አውቅልሃለሁ ፖለቲካን ማስቆም ካልቻልን ፊታችን ላይ ብዙ ተስፋ አይታየኝም። ስለዚህ የጥላቻ ንግግር እንዳይበራከት መንግሥት የጥላቻ ፖለቲካን በማጥፋት እና መረጃዎች በትክክል ሕዝቡ ጋር በማድረስ በኩል መሥራት አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- የተጠያቂነት ሁኔታን በሚመለከት ከላይ የደህንነት መዋቅሩ ምን ይሠራል? ብለው ነበር። በአጠቃላይ በአካባቢው የነበረው የፀጥታ ኃይልም ሆነ አጠቃላይ አደረጃጀቱ ተጠያቂ መሆን አለበት። ያለበለዚያ የጥፋት ድርጊቱ ይቀጥላል የሚሉ ወገኖች አሉ። እዚህ ላይ ምን አስተያየት አለዎት?**

**ዶክተር መብራቱ፡-** ማንኛውም ሰው ከሕግ በታች ነው። ሁላችንንም የሚገዛን አገራዊ ሕግ አለ። ስለዚህ በፈፀሙት ልክ ተጠያቂ መሆን አለባቸው። ተጠያቂ የሚሆን አካል እያየን አይደለም። ተጠያቂዎች እየመጡም አይደለም። ስለዚህ ተጠያቂነትን ማስፈን ላይ መንግሥት በጣም ሊገፋበት ይገባል። እኛም እየታገልን ያለነው የአካባቢያቸውን ፀጥታ ፣ ሰላም እና ደህንነት ማስጠበቅ ያልቻሉትን መንግሥት ራሱ ተጠያቂ ያድርጋቸው እያልን ነው።

መንግሥት ሕዝብን ሊያወያይ ይገባል። ሕዝብ ተጠያቂውን ያውቃል። ማን ተጠያቂ ነው? ቢባል ሕዝቡ ቁልጭ አድርጎ ያስቀምጠዋል። እንደአገር እንደመንግሥት ተጠያቂነትን ለማስፈን ምን እንደቸገረን እኔም ብዙ አላወቅኩም። ምክንያቱም ብዙ ሀብት እና የተማረ የሰው ኃይል አለን። ጥሩ ጅማሮ ላይ ነበርን። አሁን ተመልሰን ለምን ወደ ቀውስ እንደገባን አላወቅንም። እርሱ በደንብ መታየት አለበት ባይ ነኝ።

**አዲስ ዘመን፡- በእርግጥም ጥፋቱ ቆመ ሲባል መልሶ ይቀጥላል። እስኪ በዋናነት መፍትሔ ይሆናል የሚሉት ምንድን ነው?**

**ዶክተር መብራቱ፡-** አሁን ላለው የሰላም መደፍረስ መፍትሔው አገራዊ ምክክሩን ቶሎ መጀመር ነው። ጊዜ ሳይባክን አገራዊ ምክክሩን ለማካሔድ በአስቸኳይ ወደ ሥራ መገባት አለበት። ተፋላሚ ኃይሎች በጠረጴዛ ዙሪያ እንዲመጡ መደረግ አለበት። ምንም ዓይነት ነገር ተደባብቀን እና ተሸፋፍነን ሳይሆን የየራሳችንን ፍላጎት የሆነ ቦታ ቁጭ አድርገን ይህችን አገር እንዴት ወደ ፊት እናሻግራት ብለን መነጋገር አለብን። በብዙ ነገሮች ላይ ልዩነቶች አሉ። በታሪክ ትርክት ላይ፤ በባንዲራ ላይ፣ በአገር ግንባታ ላይ፣ በፌዴራሊዝሙ ላይ ፣ በሕገመንግሥቱ ላይ በአብዛኛው መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ልዩነቶች አሉ። እነዚህን ልዩነቶች ማጥበብ እና ወደ አንድነት ማምጣት የምንችለው በአስቸኳይ ወደ ብሔራዊ ምክክሩ ስንገባ ነው። ለእኔ ዋነኛ መፍትሔ የምለው ይሔንን ነው።

ሌላው መንግሥት ከተፋላሚ ኃይሎች ጋር መነጋገር፣ መደራደር እና ወደ ሽምግልና መግባቱ ትክክል ነው። እንዲያውም ቶሎ መጀመር አለበት። የታጠቁ ኃይሎችም ውጊያቸውን አቁመው በጠረጴዛ ዙሪያ ጥያቄያቸውን ማቅረብ አለባቸው። በተከታዮቻቸውም በኩል ቢሆን ጥያቄያቸውን ማቅረብ አለባቸው። ይህ ከሆነ መፍትሔ ሊመጣ ይችላል። በዚህ አሁን ያለውን ቀውስ መቀነስ ወይም አስቀድመን መከላከል እንችላለን። ለፖለቲካ ለውጡም ሽግግር ይሆናል። ዋናው መፍትሔ ብሔራዊ ምክክር ነው። ሽምግልናው እንደ ግብአት ሊሆን ይችላል።

**አሁን ላለው የሰላም መደፍረስ መፍትሔው አገራዊ ምክክሩን ቶሎ መጀመር ነው። ተፋላሚ ኃይሎች በጠረጴዛ ዙሪያ እንዲመጡ መደረግ አለበት። ምንም ዓይነት ነገር ተደባብቀን እና ተሸፋፍነን ሳይሆን የየራሳችንን ፍላጎት የሆነ ቦታ ቁጭ አድርገን ይህችን አገር እንዴት ወደ ፊት እናሻግራት ብለን መነጋገር አለብን**

**አዲስ ዘመን፡- ከላይ እርሶ እንደገለፁት በፍጥነት አገራዊ ምክክሩ ካልተጀመረ፤ ተጠያቂነት ካልሰፈነ እና አሁን የሚታየው በዚሁ ከቀጠለ መጨረሻችን ምን ይሆናል?**

**ዶክተር መብራቱ፡-** ሥርዓት አልበኝነት ይነግሳል። የብሔር ግጭት ውስጥ ልንገባ እንችላለን። በኋላ ወደማያባራ እልቂት እናመራለን። ሩዋንዳም ቢሆን የተጀመረው በዚሁ መልኩ፤ ቀስ በቀስ በጥላቻ ንግግር ነው። ስለዚህ ወደማያባራ ችግር ከማምራታችን በፊት ከወዲሁ መፍትሔ ማበጀት የተሻለ ነው። ያለበለዚያ ሕዝቡ በብሔር ተከፋፍሎ ወደ ግጭት ያመራል። በዚህ ጊዜ ደግሞ አገር ቀውስ ውስጥ ትገባለች። ማንም የጎበዝ አለቃ እየተነሳ ዘራፊ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ከምንገባ ከአሁኑ አካሔዳችንን ማስተካከል አለብን ባይ ነኝ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።**

**ዶክተር መብራቱ፡-** እኔም ስለተሰጠኝ ዕድል አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

# ከሀብቱ ተጠቃሚ ለመሆን ብዙ ስራዎች የሚጠብቁት ባለፀጋ ክልል

አንተነህ ቸሬ

በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ስር የነበሩትን የምዕራብ ኦሞ፣ የቤንች ሸኮ፣ የካፋ፣ የዳውሮና የሸካ ዞኖች እና የኮንታ ልዩ ወረዳን በአንድነት በመያዝ በኅዳር ወር 2014 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲዊ ሪፐብሊክ 11ኛው ክልላዊ መንግሥት ሆኖ የተዋቀረው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል፤ ለኢንቨስትመንት የሚሆን ከፍተኛ አቅም ያለው በተፈጥሮ ሀብት የታደለ አካባቢ ነው። በተለይም ክልሉ ያለው የቡና፣ የሻይ ቅጠል፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የማዕድናት ሀብት ሀገርን የሚያኮራ፣ ባለሀብቶችን በኢንቨስትመንት ለመሰማራት የሚያነሳሳ እና የሕዝብን የልማት ጥያቄ ለመመለስ ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ የፀጋዎች ባለቤት ነው።

የክልሉ ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ኤጀንሲ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ ክልሉ ወርቅን ጨምሮ የተለያዩ ማዕድናት ባለፀጋ ነው። ከወርቅ ማዕድን በተጨማሪ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውል የድንጋይ ከሰል በክልሉ በዳውሮ እና በኮንታ አካባቢዎች በስፋት ይገኛል። ለኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆን የብረትና የድንጋይ ከሰል ማዕድናትም ሌላው በክልሉ የሚገኙ ሀብቶች ናቸው።

በአስር ዓመቱ ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች መካከል የማዕድን ዘርፍ አንዱ መሆኑ ይታወቃል። የዘርፉ እምቅ የማእድን ሀብት በዚህ በኩል ጉልህ ስፍራ ይኖረዋል። ዘርፉ በሀገራዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ጉልህ ድርሻ እንዲኖረው በክልሉ ያለውን እምቅ ሀብት ጥቅም ላይ ለማዋል ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

ክልሉ ወርቅን ጨምሮ የተለያዩ ማዕድናት ባለፀጋ ቢሆንም ልማቱ እየተከናወነ ያለው በባህላዊ መንገድ በመሆኑና ቀደም ሲል ጀምሮ ለዘርፉ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶ፣ ሀብቱ ከባህላዊ አሰራር ወጥቶ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል የሚፈለገውን ያህል ጥረት ባለመደረጉ ተገቢውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አላስገኘም። ለአብነት ያህል እስካሁን ባለው ሂደት ወርቅ የማምረት ሥራው በባህላዊ መንገድ፣ በአካፋና በዶማ በመቆፈር፣ የሚከናወን ነው። ስራውን የሚያከናውኑት በማሕበር የተደራጁ የአካባቢው ነዋሪዎች በመሆናቸው የማዕድን ሀብቱን በዘመናዊ አሰራር ለማልማት ብዙ ሥራዎች ይጠበቃሉ። ስለሆነም የማዕድን ሀብቶችን ለይቶና አደራጅቶ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ የክልሉ ቀጣይ የቤት ሥራ እንደሆነ ግንዛቤ ተይዞ ከወዲሁ እየተሰራ እንደሆነም የኤጀንሲው መረጃዎች ያሳያሉ። በተለይም ለውጭ ገበያ ቀርቦ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት ረገድ ትልቅ ድርሻ ባለው በወርቅ ማዕድን ልማት ላይ በስፋት እንዲሰራና በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከውጭ በግዥ ጥቅም ላይ እየዋለ ያለውን የድንጋይ ከሰል በአገር ውስጥ መተካት እንዲቻል ትኩረት ተሰጥቷል።

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት የሀገር ኢኮኖሚን በብርቱ የሚደግፉ ምርቶች መገኛ ነው። ከፍተኛ የቡናና የማዕድን ሀብቶችን የያዘው ይህ ክልል፤ ሀብቱ ከክልሉ አልፎ ለሀገርም የሚተርፍ ፀጋ ነው። ክልሉ አስደናቂ የሆነ መልከዓምድራዊ አቀማመጥ፣ ልምላሜና የተፈጥሮ ሀብት ያለው በመሆኑ የባለሀብቶችን ትኩረት እንደሚስብ ይጠበቃል። በዚህ ረገድ ስለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የኢንቨስትመንት ሀብትና የዘርፉ የሥራ እንቅስቃሴዎች የክልሉ ንግድና ኢንቨስትመንት ቢሮ፣ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ዳይሬክተር አቶ ይደነቅ ወልደሰንበት በተለይ ለ‹‹አዲስ ዘመን›› ጋዜጣ የሰጡትን ማብራሪያ እንደሚከተለይ አቅርበነዋል።

## የክልሉ የኢንቨስትመንት አቅም

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በተለያዩ ዘርፎች እምቅ የኢንቨስትመንት አቅም አለው። ዓመታዊ ሰብል፣ ቡናና ቅመማ ቅመም፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ኢንዱስትሪ እና አገልግሎት ዘርፎች በክልሉ በኢንቨስትመንት ለመሰማራት የሚያስችሉ የምጣኔ ሀብት መስኮች ናቸው።

በማዕድን ዘርፍም ሰፊ አቅም እንዳለ አመላካች ነገሮች




አሉ። ክልሉ በአዲስ መልክ የተደራጀ በመሆኑ ያሉትን የማዕድን ሀብቶች ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በስፋት በማጥናት ለኢንቨስትመንት ዝግጁ የሚያደርግ ይሆናል። የክልሉን ሀብቶች ለመለየት የሚደረጉ ተጨማሪ ጥናቶች እንደተጠበቁ ሆነው፤ እስካሁን በተካሄደ ጥናት 88ሺ 786 ሄክታር ለዓመታዊ ሰብሎች፣ አራት ሺ 875 ሄክታር ለቡናና ቅመማ ቅመም እና 20ሺ 565 ሄክታር ለአትክልትና ፍራፍሬ፤ በአጠቃላይ 134ሺ 126 ሄክታር መሬት ለግብርና ዘርፍ ምቹ እንደሆነ ታውቋል።

በአገልግሎትና በኢንዱስትሪ ዘርፎችም ክልሉ የኢንቨስትመንት መዳረሻና አማራጭ መሆን የሚችል አካባቢ ነው። በክልሉ ዞኖችና ከተሞች 69 ነጥብ ሰባት ሄክታር መሬት በአገልግሎት ዘርፍ እንዲሁም 64 ነጥብ ስድስት ሄክታር ደግሞ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ተለይቷል።

## ባለሀብቶችን የመሳብ ጥረት

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ባለሀብቶችን ወደ ክልሉ በመሳብ ክልሉና ሕዝቡ ከሀብቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የተለያዩ ተግባራት አከናውኗል፤እያከናወነም ይገኛል። ለባለሀብቶች ጥሪ ተደርጓል፤ባለሀብቶችን ለመቀበል በዞን የአስተዳደር መዋቅሮች አማካኝነት ግንዛቤ እንዲፈጠር ተደርጓል። ባለሀብቶች ወደ ክልሉ ሲመጡ ያለምንም መስተጓጎል ወደ ስራ እንዲገቡ በየጊዜው ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ተሰርተዋል። የባለሀብቶች ጥያቄዎች ከአንድ ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ምላሽ እንዲያገኙ ይደረጋል። ባለሀብቶች ምንም ዓይነት የቢሮክራሲ ችግር ሳይገጥማቸው ወደ ስራ እንዲገቡ ጥረት እየተደረገ ነው።

## የባለሀብቶች ፍላጎትና ተሳትፎ

ክልሉ ከተደራጀ ወዲህ ባለሀብቶች በክልሉ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለመሰማራት ፍላጎት አሳይተዋል። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በተሰሩ የንቅናቄ ተግባራት አማካኝነት ብዙ ባለሀብቶች በክልሉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሰማራት ፍላጎት እንዳላቸው ማወቅ ተችሏል። በቅርቡ በግብርና፣ በአገልግሎትና በኢንዱስትሪ ዘርፎች ከአንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ያስመዘገቡ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶቻቸውን አቅርበው ፕሮጀክቶቹ ተገምግመውና በሚያስፈልገው መስፈርት መሰረት ተመዝነው በአስፈፃሚው አካል ውሳኔ አግኝተዋል። ፕሮጀክቶቹ አቅማቸው ታይቶና በቴክኒክ ኮሚቴ ተገምግሞ አስፈፃሚው አካል ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ወደ ስራ እንዲገቡ እየተደረገ ነው።

**ክልሉ ከተደራጀ ወዲህ ባለሀብቶች በክልሉ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለመሰማራት ፍላጎት አሳይተዋል። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በተሰሩ የንቅናቄ ተግባራት አማካኝነት ብዙ ባለሀብቶች በክልሉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሰማራት ፍላጎት እንዳላቸው ማወቅ ተችሏል። በቅርቡ በግብርና፣ በአገልግሎትና በኢንዱስትሪ ዘርፎች ከአንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ያስመዘገቡ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶቻቸውን አቅርበው ፕሮጀክቶቹ ተገምግመውና በሚያስፈልገው መስፈርት መሰረት ተመዝነው በአስፈፃሚው አካል ውሳኔ አግኝተዋል**

ባለሀብቶቹ ለመሰማራት ጥያቄ ያቀረቡባቸው ዘርፎች ግብርና (ዓመታዊ ሰብሎች፣ ቡና፣ ሻይ ቅጠል፣ ቅመማ ቅመም፣ አትክልትና ፍራፍሬ)፣ አገልግሎት (ሆቴልና ቱሪዝም) እና ኢንዱስትሪ ዘርፎች ናቸው። ባለሀብቶቹ ፈቃድ ወስደው ስራ የጀመሩባቸው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ለሁለት ሺ 457 ዜጎች ቋሚ እንዲሁም ለ21ሺ.939 ዜጎች ደግሞ ጊዜያዊ የሥራ እድሎችን መፍጠር ችለዋል።

## የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች

ክልሉ የባለሀብቶችን ፍሰት ለመጨመር የሚያደርጋቸው ማበረታቻዎች በአዋጅና በመመሪያ በተደነገጉ የማበረታቻዎች (lncentives) አሰጣጥ መሰረት የሚፈፀሙ ይሆናል። ቦታዎችን አዘጋጅቶ ለባለሀብቶች ማቅረብን ጨምሮ ክትትልና ድጋፍ የማድረግ ተግባራትን ያከናውናል። ባለሀብቶች በፍጥነት ወደ ስራ እንዲገቡ ቅድመ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

## ተግማች መሰናክሎች

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በክልልነት ከተደራጀ ገና ጥቂት ወራት የተቆጠሩ በመሆኑ ባለሀብቶችን ወደ ክልሉ ለመሳብ በሚደረገው ጥረት ላይ መሰናክል ይፈጥራሉ ተብሎ የሚገመቱ ችግሮች ይኖራሉ።

በክልሉ ገና በጥናት ያልተለዩ ብዙ ሀብቶች አሉ። ወርቅ፣ ኦፓልና ሌሎች ማዕድናት በክልሉ ይገኛሉ ተብሎ ይገመታል። እነዚህ ሀብቶች በትክክል ተጠንተው ወደ ስራ አለመግባቱ ባለሀብቶችን በብዛትና በፍጥነት ወደ ክልሉ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለማስገባት ችግር መፍጠሩ አይቀርም። ከዚህ አንፃር ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የክልሉን ሀብቶች በጥናት በመለየት ለኢንቨስትመንት ክፍት ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ክልሉ አዲስ በመሆኑ የኢንቨስትመንት ዘርፉን ተግባራት ለማቀላጠፍ በሚያስችል የሰው ኃይልና ሌሎች ግብዓቶች ማጠናከር ያስፈልጋል። የኢንቨስትመንት ስራዎች ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆኑ ብቁ የሰው ኃይል አስፈላጊ በመሆኑ አደረጃጀቶችን የማጠናከርና ግብዓት የማሟላቱን ስራ እስከታችኛው መዋቅር ድረስ መስራት ይገባል።

የመሰረተ ልማት ችግሮችም በክልሉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ላይ ችግር ይፈጥራሉ። አርብቶ አደሮችና አርሶ አደሮች የሚኖሩባቸው የክልሉ አካባቢዎች የመሰረተ ልማት ተደራሽ ካልሆኑ ባለሀብቶች ወደ አካባቢዎቹ ገብተው በኢንቨስትመንት ላይ ለመሰማራት ይቸገራሉ። ስለሆነም የኢንቨስትመንት ፍሰቱን ለማጠናከር የመሰረተ ልማት አቅርቦቶችን ማሟላት ይገባል።

## ሰላምና ፀጥታ እና ኢንቨስትመንት

ሰላምና ፀጥታን ማስጠበቅ ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታዎችን ከሚፈጥሩ ግብዓቶች ዋነኛው እንደሆነ ይታወቃል። የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ከተመሰረተ በኋላ በሰላም እጦት የሚታወቁ አካባቢዎች ሰላም ሰፍኖባቸዋል። ለአብነት ያህል የፀጥታ ችግሮች የነበሩባቸው የአርብቶ አደር አካባቢዎች እየተረጋጉ ይገኛሉ። የክልሉ የፀጥታ መዋቅርም የተጠናከረና ችግሮችን መፍታት የሚችልበት ቁመና ላይ ይገኛል። በመሆኑም ከዚህ ቀደም ተደራሽ ያልነበሩ አካባቢዎች ጭምር የኢንቨስትመንት ፍላጎት እየታየባቸው ነው። በአጠቃላይ የክልሉ መንግሥት ሰላምና ፀጥታን ከማስፈን አንፃር የተሻለ ስራ እየሰራ ይገኛል።

## እቅዶች

ክልሉ አስደናቂ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ልምላሜና ሀብት ያለው በመሆኑ ይህን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ እቅድ ተግባራዊ ይደረጋል። በግብርና፣ በቱሪዝምና በኢንዱስትሪ ዘርፎች በስፋት ለመስራት የተዘጋጁ እቅዶች አሉ። የክልሉን የማዕድን ሀብቶች በጥናት በመለየት ለኢንቨስትመንት ምቹ ማድረግም ሌላው የትኩረት አቅጣጫ ይሆናል።

አቶ ይደነቅ ወልደሰንበት እንደሚናገሩት፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ሰፊ የኢንቨስትመንት አማራጮች አሉት። አካባቢው ገና ያልተነኩ ብዙ ሀብቶች አሉት። ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለሌላው አካባቢ የሚበቃ የተትረፈረፈ ሀብት ያለው አካባቢ ነው። የሀገር ውስጥም ሆኑ የውጭ ባለሀብቶች ወደ ክልሉ በመምጣት በኢንቨስትመንት ስራዎች ላይ ቢሰማሩ ጥሩ ውጤቶችን ያገኛሉ፤ራሳቸውንም ሀገርንም መጥቀም ይችላሉ።

በክልሉ በኢንቨስትመንት ዘርፎች ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ወደ ክልሉ ቢመጡ ክልሉ ባለሀብቶቹን ለማስተናገድ ዝግጁ እንደሆነ ተናግረዋል።

# እኔ ትውልዱን ሸሽቼዋለሁ ... እናንተም ሽሹት

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጽ)**

**ስሚመለከተው ሁሉ...**
**እንሆ ግለሰባዊ አቋም...**

እኔ ከዚህ ትውልድ አይደለሁም ከዚያኛው ከአባቶቼ ትውልድ ነኝ። ከዛኛው አብሮ እየበላ፣ አብሮ እየጠጣ ኢትዮጵያዊነትን በፍቅር ቀለም ከቀለመው አብራክ ነኝ። ከዛኛው..በጨዋነት አገር ካቆመው፣ በፍቅር ጥልን ከገደለው፣ በአንድነቱ ታሪክ ከሠራው ከዛ ትውልድ ዘንዳ ነኝ። እኔ በባዶ እግሩ እየሄደ ጫማ ካለበሰኝ፣ ሳይማር በፈርዐ እግዚአብሔር ሁሉን ካወቀው፣ ፊደል ሳይቆጥር ዘመናዊነትን ካስተማረኝ ከዛ ብሩክ አብራው የበቀልኩ ነኝ።

እኔ ብሔር ሳይል ሃይማኖት፣ ዘር ሳይል ጎሳ ፊደል ቀርጾ፣ የቀን መቁጠሪያ ሠርቶ ታሪክና ቀዳማይነትን ያለበሰኝ የዛ የባለታሪክ ጽንስ ነኝ። ራሴን በገዛ ፍቃዴ አሁን ካለው ከስሜታዊው ትውልድ አገለልኩ። በብሔር ስም ፍቅር ካጣው፣ በእኔነት ጽንፍ አንድነት ካጣው፣ በራስ ወዳድነት ኢትዮጵያዊነትን ከሻረው ከዚህ ትውልድ ተለየሁ። እናም እኔ አባቶቼን ነኝ ስል ሁሉም እንዲሰማኝ ጮኽ ብዬ ተናገርኩ።

እኔ ሰው ነኝ..አባቶቼ ያስተማሩኝ ሰውነትን ነው። እናንተም ሰው ናችሁ ያኛው ትውልድ የነገራችሁ ሰውነትን ነው። ታዲያ ሰውነት በዚህ ዘመን የት ገባ? ዛሬ ላይ የምንባላባቸው ብሔርና ቋንቋ፣ ዘርና በምን ሚዛን ከሰውነት በለጡ? ለዚም ስል ራሴን ከእናንተ አገለልኩ..እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ፣ እኔ የእውነተኛዎቹ የአባቶቼ ፍሬ ነኝ ስል ተነሳሁ። ይሄ ሰው ምን ነካው እንደማትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ደግሞም እናንተ እንጂ እኔ አላበድኩም።

ሰው የሚያብደውና ከተፈጥሮ ሚዛን የሚጎድለው ሰውነትን በሌላ ሲቀይር ነው። ሰው ኋላ ቀር የሚባለው የአባቶቹን የአንድነት ምድር በመለያየት የእኔ..የእኛ ሲል ነው። አገር ድሀ የምትባለው ፍቅርን ያጡ ሕዝቦች ሲኖሩባት ነው። ብዙ የጋራ ታሪኮች እያሉ ሕዝብ ያን የጋራ ታሪክ መጠቀም ሳይችል ሲቀር ነው። የእኛ ድህነት ባለመሥራት የመጣ የሚመስለው ሞልቷል። የእኛ ድህነት የኢኮኖሚ ችግር ብቻ የሚመስለው ብዙ ነው። የእኛ ድህነት የኢኮኖሚ ድህነት አይደለም። የእኛ ድህነት የፍቅር ማጣት፣ የአንድነት ማጣት የወለደው ነው። የእኛ ኋላ መቅረት የከሸፈ የፖለቲካ ሸር የፈጠረው ነው። ዛሬ ላይ ጎልተው የምናያቸው ኢኮኖሚያዊም ሆኑ ማህበራዊ ችግሮቻችን አንድነት በማጣት የተፈጠሩ ናቸው።

ሰው አንድ ከሆነ፣ ሕዝብ በፍቅርና በአንድነት ከቆመ አይደለም ድህነትን፣ አይደለም ኋላ ቀርነትን ሌላም አይበግረውም። ትልቁ ችግራችን የአንድነት ማጣት ችግር ነው። ትልቁ ችግራችን ስልጣን እጃችን ሲገባ አብሮ የተረኝነት ስሜት መሰማቱ ነው። የትኛውም የዓለም ስልጣኔ በሕዝቦች የአንድነት መንፈስ ተጠንስሶ ፍሬ ያፈራ ነው። ሩቅ ሳንሄድ በቀላሉ እንኳን የአድዋን ድል ብናይ አንድነት የፈጠረው ሆኖ እናገኘዋለን።

አስቡት እስኪ..ዓለም ላይ በስልጣኔ ፊት አውራሪ የሆነች፣ በሎጂስቲክና በጦር ኃይል አካዳሚ አንቱታን ያገኘች፣ ከዚህ ሁሉ በላይ በአየርና በየብስ የሚምዘገዘጉ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ የታጠቀች አገር በአንድ ድሀና ባህላዊ መሣሪያ ባነገቡ ሕዝቦች ስትሸነፍ። ይሄን እውነት ምን ትሉታላችሁ? ይሄ እውነት የአንድነት እውነት ነው። ይሄ እውነት ታሪክ የቀየረ፣ ኢትዮጵያዊነትን ከአጽናፍ አጽናፍ ከፍ ያደረገ የአባቶቻችን የአንድነት ክንድ ነው። እኛም ከፍ ለማለት፣ ከኋላቀርነትና ከድህነት እንድንወጣ አንድነት ነው የሚያስፈልገን።

እኔ በምክንያት የተፈጠርኩ፣ በምክንያት የምኖር ወጣት ነኝ። እኔ የአገሬ ድሀ መሆን፣ የወገኔ በቀን ሦስት ጊዜ አለመብላት የሚያሳስበኝ፣ ብሔር ምን እንደሆነ የማላውቅ፣ በፖለቲካ ቅራኔ ጥላቻ የማላውቅ ምክንያታዊ ወጣት ነኝ። ለአገሬ ምርጡን የማስብ፣ ለድህው ወገኔ የምጨነቅ ባለ ራዕይ ወጣት ነኝ። እኔ የኢትዮጵያን ስም በመልካም ከሚያስተጋቡት ምርጦች ውስጥ ነኝ። በዘርና በብሔር፣ በቋንቋና በሃይማኖት ከሚባሉት ውስጥ አይደለሁም። የሚያግባቡንና አንድ የሚያደርጉን ብዙ ነገሮች እያሉ በለያዩን ጥቂት ነገሮች የምሸነፍና ድንጋይ ከሚያነሱት ውስጥ አይደለሁም።

እንደ እኔ ትውልዱን የጠላ፣ እንደ እኔ በምክንያትና በማሰብ የሚኖር ካለ ይከተለኝ። እንደ እኔ ሰውነትን ያገነነ፣ እንደ እኔ ፍቅርና ይቅርታን አንድነትንም ለመልበስ የተሰናዳ ካለ ጎኔ ይቁም። እንደ እኔ ወገኖቹን ሁሉ የሚያፈቅር፣ ኢትዮጵያን ያለ ታማኝ ዜጋ ካለ አብሮኝ ይቁም። በእኔና በእናንተ መካከል የቆመ የማንነት ድንበር፣ ብሔርተኝነትን የሚሸር የህልውና አጥር፣ የአንድነት ምሰሶ ኢትዮጵያዊነት ነው። በዚህ ስም ካልተግባባን በሌላ በምንም አንግባባም። እግዜር ስንት ጊዜ ታዘበን.. አጋንንት ስንት ጊዜ ቀናብን። ሁሉ ነገራችን በእጃችን ያለ ሕዝቦች ነበርን። ፍቅር ቢኖረን የጎደለን አንዳች እንደሌለ እንደርስበት ነበር። አንድነት ቢኖረን በዚህ ልክ በርሀብ፣ በዚህ ልክ በመገፋፋት ባልነወርን ነበር።

ሕዝቤ ሆይ ስማኝ ካለ ፍቅር የምንራመደው መንገድ ወደ ሞት ካልሆነ ወደየትም አያደርሰንም። ስለዚህ ፍቅርን እንወቅ። ኢትዮጵያ መግባቢያ ቋንቋችን ናት። በእያንዳንዳችን ነፍስ ላይ፣ በእያንዳንዳችን ከንፈር ላይ ያለ ቅዱስ ቃላችን ናት። ይሄን እውነት ስላልተረዳነውና ስላልተቀበልነው ነው ዛሬ ላይ በብሔር ስም ብዙ ነገር እየሆንን ያለነው። ሰውነት ከዘር ቢበልጥብን ኖሮ፣ ኢትዮጵያዊነት ከብሔር ቢልቅብን ኖሮ ዛሬ ላይ እነዚህን ሁሉ የሞትና የጦርነት መርዶዎች ባልተጋፈጥን ነበር። እንደ እኔ ትውልዱን ሽሹና ወደ አባቶቻችን መንፈስ እንመንን። በአባቶቻችን የአንድነት ገዳም ውስጥ ፍቅርን ተምረን በቅተን ስንመለስ ምናልባት ያኔ አገርና ሕዝብ ምን ማለት እንደሆኑ ይገባን ይሆናል። እኔ ትውልዱን ሸሽቼዋለሁ..እናንተም ሽሹትና ይሄን ብሔርተኛ ትውልድ ባዶውን እናስቀረው..ከዛም ኢትዮጵያን የሚል ትውልድ እንፍጠር።

በደምና በአጥንት የተቀለመ ኢትዮጵያ የሚል የአንድነት ሐውልት እኮ አለን። በሞትና በጀግንነት የተፈጠረ ሀበሻ የሚል ድንቅ የወል ስም እኮ አለን። ታዲያ ኦሮሞነት፣ አማራነት፣ ትግሬነት ምን አመጣው? በየትኛው መስፈርት ነው ብሔር ከኢትዮጵያዊነት ሊልቅ የሚችለው? አትሳቱ.. ኢትዮጵያዊነት መሪያችን ነው። የተጠለልነው በኢትዮጵያዊነት ትልቅ ዋርካ ስር ነው። ኢትዮጵያዊነትን ሸሽቶ ብሔርተኝነትን መትከል ይሄን ትልቅ የጋራ ዋርካ መገንደስ ነው ።

እኛነትን ሽሮ እኔነትን መትከል ለዘመናት በአባቶቻችን እንባና ደም የጸደቀችውን፣ ጸድቃም የለመለመችውን፣ ለምልማም ሰላሳና ስልሳ መቶም ያፈራችውን ኢትዮጵያን ማሳነስ፣ ማጠውለግ፣ ማምከን ነው የሚሆነው። ኢትዮጵያዊነት ምንድነው ስንባል የምንመልሰው የጋራ እውነት ሊኖረን ይገባል።

> **እኔ ሰው ነኝ..አባቶቼ ያስተማሩኝ ሰውነትን ነው፡፡ እናንተም ሰው ናችሁ። ያኛውም ትውልድ የነገራችሁ ሰውነትን ነው፡፡ ታዲያ ሰውነት በዚህ ዘመን የት ገባ? ዛሬ ላይ የምንባላባቸው ብሔርና ቋንቋ፣ ዘር በምን ሚዛን ከሰውነት በለጡ? ለዚም ስል ራሴን ከእናንተ አገለልኩ.. እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ፣ እኔ የእውነተኛዎቹ የአባቶቼ ፍሬ ነኝ ስል ተነሳሁ፡፡ ይሄ ሰው ምን ነካው እንደማትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ደግሞም እናንተ እንጂ እኔ አላበድኩም**

እኔ ግን እላለሁ ከኢትዮጵያዊነት ውጪ ሌላ ብሔር፣ ሌላ ማንነት የለኝም። የእኔ ብሔር፣ የማንነቴ ጥላ፣ ዋርካዬ ኢትዮጵያ ናት። እናንተም አይኑራችሁ.. መማያችሁ ኢትዮጵያ ትሁን። አገራችን ኢትዮጵያ ለሁላችን የምትበቃ ማህጸነ ለምለም አገር ናት። እኛ ለእሷ እንመቻት እንጂ እሷ ለእኛ የሚሆን ብዙ ነገር አላት። እኛ በፍቅር፣ በአንድነት እጅ ለእጅ ተያይዘን እንቁም እንጂ ማጀቷ ሙሉ ነው። ሌማቷ ጎድሎ አያውቅም። አይደለም ለእኛ ለሌሎች የሚሆን ብዙ ነገር ያለን ሕዝቦች ነን። ግን ይሄ ሁሉ ሙላት፣ ይሄ ሁሉ መትረፍረፍ ያለፍቅር፣ ያለአንድነት ምንም ነው።

በብሔር ሳይሆን በሰውነት አገር እንሥራ። በነውር ሳይሆን በኢትዮጵያዊነት ትውልድ እንቅረጽ። የሚበጀን ይሄ ነው። አገራችንን እያሳነስናት ያለነው ራሳችን ነን። ወጣቱ ራሱን ለአፍታ ቢመለከት እየሄደበት ያለው መንገድ ልክ እንዳይደለ ይደርስበታል። እኔ አማራ ብቻ፣ ኦሮሞ ብቻ ወይም ትግሬ ብቻ አይደለሁም፣ እኔ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰብ ደግፎ ያቆመኝ የብሔረሰብ ልጅ..የብሔረሰብ ቅይጥ ነኝ። እኔ እዚህ ቦታ ሰው ሆኜ እንድቆም አማራው፣ ኦሮሞው፣ ትግሬው፣ ሱማሌው፣ ሲዳማው፣ ወላይታው፣ ጋሞው፣ ጉራጌው፣ አርጉባው ሁሉም ብሔር አስተዋጽኦ አድርጓል። እንዴት ራሴን በክብር ካቆመኝ ከዚህ ሕዝብ መገንጠል እችላለሁ? እንዴትስ ውለታውን ረስቼ ኦሮሞ ነኝ፣ አማራ ነኝ፣ ትግሬ ነኝ እላለሁ? እንዴት በኩራት ካቆመኝ ብሔርብሔረሰብ ተለይቼ ሲዳማ ነኝ፣ ጉራጌ ነኝ እላለሁ? እኔ ሁሉንም ብሔርብሔረሰብ ነኝ።

የእኔ የምለው ብሔር የለኝም። የእኔ ካልኩም ኢትዮጵያዬን ነው የእኔ የምላት። የእኔ ብሔር እሷ ናት። ከእንግዲህ ባለው ታሪካችን፣ ከእንግዲህ ባለው ሕይወታችን ኢትዮጵያን እገርም ብሔርም አድርገን እንድንኖር እፈልጋለሁ። ከእንግዲህ ባለው ማህበራዊ ሕይወታችን፣ ከእንግዲህ ባለው ፖለቲካችን ኢትዮጵያን ርስትም መመኪያም አድርገን እንድንኖር እሻለሁ። አገሩን ብሔሩ ያደረገ ትውልድ በዚህ ዘመን እንዲፈጠር እሻለሁ። አገሩን ሁሉ ነገሩ ያደረገ መንግሥትና ሕዝብ በዚህ ዘመን እንዲበዛ እሻለሁ። ያለዛ አትመልሱኝም። ያለዛ ከምናኔዬ አልመለስም። አገራችሁን ብሔራችሁ አድርጋችሁ ካልጠበቃችሁኝ እየሄድኩበት ካለው የምናኔ ጉዞ አልመለስም።

ብቻችንን ተዐምር የለንም። ብቻችንን አገርና ሕዝብ መሆን አንችልም። ብቻችንን አስፈሪ የመሆን አቅም የለንም። ኃይላችን አንድነታችን ነው። እድገታችን ብዙሀነታችን ነው። አንድ መሆን ከኃይልና ከውበት ባለፈ አስፈሪነትም ነው። ግርማ ሞገስ ነው። አንበሳነት ነው..ኩራት ነው። ታዲያ ወንድማማችነት አይሻልም ትላላችሁ? ታዲያ ፍቅርን ያገነነ፣ አንድነትን የወደደ አገርና ሕዝብ ቢወጣን ምኑ ነው ችግሩ? ልዩነታችንን ለውበት እንጂ ለመለያየት አንጠቀመው። ብዙሀነታችንን ለልማት እንጂ ለሁከት አናድርገው።

ከጉዞዬ ትመልሱኝ ዘንድ..አብሬአችሁም በወንድምነት እቆም ዘንድ በኢትዮጵያዊነት ታረቁኝ። በኢትዮጵያዊነት ማሉልኝ። ከእንግዲህ ኢትዮጵያዊ ነኝ በሉኝ። ያለዛ በዚህ ዘመን ተፈጥሬ የዛ ዘመን ትውልድ እሆናለሁ። ያለዛ እናንተን ትቼ ኢትዮጵያን አፍቅረው ወደሞቱት የዋህ ነፍሶች አዘግማለሁ። ያለዛ ርቄአችሁ በኢትዮጵያዊነት ገዳም ውስጥ ለብቻዬ እመንናለሁ።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## የራስ ቴአትር ትንሳኤ

ተገኝ ብሩ

ለአገራችን ኪነጥበብ ዕድገት ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ። እጅግ ስሙ የናኘ በሥራዎቹም አንቱ የተባለ አርቲስት «ከወደየት ነህ» ቢባል ከእነዚህ የጥበብ ቤቶች አንዱን መጥራቱ አይቀርም። «እዚያ ነው የጥበብ ሀሁን የጀመርኩትና ያደግኩት» ማለት አይቀሬ ነው። በዜማው የተወደደ በግጥምና እንጉርጉሮው የተደነቀም ድምፃዊ መነሻው ቢጠየቅ እነዚሁ የጥበበኞች ምንጭ ወደነበሩት ቤቶች መጠቆሙ የተለመደ ነው።

ለረጅም አመታት በእነዚህ የጥበብ ቤቶች ብዙዎች ኪነጥበባዊ ጥማታቸውን ቆርጠዋል። ኪናዊ አምሮታቸውን ተወጥተዋል። አንቱ መሰኘት፤ በዘርፉ ትልቅ ተፅዕኖ መፍጠርና ዝናን ማትረፍም ችለዋል። የኪነጥበብ አፍቃሪውም ተጋፍቶ ከጥበብ ማዕዳቸው ተቋድሷል። ተሰልፎ የተደገሰውን ኪነ ጥበባዊ ድግስ ተካፍሏል። በጥበብ ቤቶቹ አገር ፍቅር ቴአትር፤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር፤ ራስ ቴአትር እና ሌሎችም ቴአትር ቤቶች ለዘመናት ኪናዊ ሁነት ሲበጅ፣ ኪነት ሲገን፣ ጥበብ ሲንቆረቆር ኖሯል።

የጥበብ ቤቶቹ በአገር ደረጃ ስመጥር የሆኑ የኪነጥበብ ባለሙያዎች አፍርተዋል። በሙዚቃ ቲያትርና መሰል የሥነፅሑፍ ዘርፎች ውስጥ የሚሳተፉ አያሌ ከያኒያን "ቤቴ" እያሉ ይጠሯቸዋል። ቀደም ባሉት አመታት በተመልካች ተጨናንቀው እንዳልነበር ዛሬ ላይ ከነበሩበት ፍፁም በተለየ መልኩ ይገኛሉ።

ይህንን ገፅታቸው ለመቀየርና በፊት የተላበሱትን ግርማ ሞገስ ለማላበስ ብሎም አገልግሎት አሰጣጣቸውና ገፅታቸው እጅግ ባማረ መልኩ ለማነፅ እንቅስቃሴዎች በመደረግ ላይ ናቸው። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ባህልና ቴአትር ቤት ግንባታ ያጠናቀቀ ሲሆን እንዲሁም ከሰሞኑ የአዲስ አበባ ሕፃናትና ወጣቶችን ቴአትር ቤትን ግንባታ እያጠናቀቀ እንደሆነ ገልጿል።

ከእነዚህ መሀል የአፍሪካ የመጀመሪያው ቴአትር ቤት አገር ፍቅር ታድሶና በተሻለ መልክ ተደራጅቶ ሥራውን ለመጀመር እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ነው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትርም ቢሆን ሙሉ ለሙሉ ሥራውን ሳያቆም ጎን ለጎን የቴአትር ቤቱን ሁለንተናዊ ገፅታ በመታደስ ላይ ይገኛል። ለዚህም ሥራው በመፋጠን ላይ ይገኛል።

ሌላኛውና በመዲናችን ከሚገኙ አንጋፋ ቴአትር ቤቶች መካከል አንዱ የሆነው በኢትዮጵያ የጥበብ ጉዞ ውስጥ ትልቅ ቦታ ያለው ቴአትር ቤት ራስ ቴአትር ለበርካታ አመታት ፈርሶ አገልግሎት ሳይሰጥ ቆይቷል። ስመ ጥርና በሙያቸው አንቱታን ያተረፉ በርካታ የኪነጥበብ ባለሙያዎች ለአገር ያበረከተው የራስ ቴአትር በቅርቡ ቀን ሊወጣለት መቃረቡ ታውጇል።

ይህ ለዘመናት የኪነጥበብ ሥራዎችን ለሕዝብ እያቀረበ ቆይቶ በእርጅና ምክንያት የፈራረሰው የጥበብ ቤት በፊት ከነበረው ገፅታው በተሻለ ሁናቴ ለማስገኘትና የጥበብ ቤትነቱን በሚመጥን ዲዛይን ለማዋቀር በአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ሰኔ 25/2014 ዓ.ም የመሠረት ድንጋይ ተቀምጦለት ሥራውን ጀምሯል።

በግንባታ መሠረት ድንጋይ ማስቀመጥ ላይ ታዋቂዎቹ አንጋፋ የኪነጥበብ ሰዎች እንዲሁም በኢትዮጵያ አገር ግንባታ ውጣ ውረድ ውስጥ ትልቅ ዋጋ የከፈሉ አርቲስቶች ተገኝተዋል። በክብር እንግድነት ተገኝተው የግንባታ መሠረተ ድንጋዩን ያኖሩት ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ አስተዳደሩ ለኪነጥበብ ሥራዎች ከፍተኛ ትኩረት እንደሚሰጥና ለዚህም እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ትልቅ ምስክር መሆናቸውን ጠቁመዋል።

«ለኪነጥበቡ ልዩ ትኩረት በመስጠት በመስራት ላይ እንገኛለን» ያሉት ከንቲባዋ በከተማዋ 10 አምፊ ቴአትሮችን በማስገንባት ላይ መሆኑንና አንዳንዶቹ መጠናቀቃቸውን፣ በሌላ በኩልም የማዘጋጃ ቤቱ የባህል አዳራሽ ባማረ መልኩ የተገነባ መሆኑን አንስተዋል። ራስ ቴአትር ብዙ የኪነጥበብ ባለሙያዎች ያፈራ ቤት እንደመሆኑ ደረጃውን የሚመጥ ግንባታ ለማካሄድ እንደታሰበና በዚህም የመጀመሪያውን አዲስ ቴአትር ቤት ግንባታ የመሠረት ድንጋይ እንዳስቀመጡ ጠቁመዋል።


«ቴአትር ቤቱ ባማረ መልኩ ተገንብቶ ለኪነጥበብ ባለሙያውና ለሕዝቡ ትልቅ አስተዋፅኦ እንዲኖረው ይደረጋል» ብለዋል። ጥበብ ትውልድን በመቅረፅና በመገንባት ትልቅ ሚና ስላላት አሁንም ትኩረት ሰጥተን መሥራታችንን እንቀጥላለን በማለት የከተማ አስተዳደሩ ለኪነጥበብ እየሰጠ ያለውን ዋጋ አንስተዋል። በመርሀ ግብሩ ላይ ለኪነጥበብ ባለሙያው መልዕክታቸው ያስተላለፉት ከንቲባዋ «እናንተ ጥበባችሁን ተጠቅማችሁ አገር ግንባታ፣ ሰላምና ፀጥታ ማረጋገጥ ላይ በርትታችሁ ስሩ» ብለዋል።

በዚህ ለዘመናት የኪነጥበብ ባለሙያዎች እያፈራ ቆይቶ በፈረሰ ቴአትር ቤት ላይ በተሻለ ዲዛይንና ምቹ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲኖረው ተደርጎ በሚታነፀው ሕንፃ መሠረተ ድንጋይ የማስቀመጥ ሥነ ሥርዓት ላይ የተገኙት የቀድሞ የቴአትር ቤቱ ባልደረቦች ባዩት መደሰታቸውን ገልፀዋል። ቴአትር ቤቱ አገልግሎት ከመስጠት ተቋርጦና ለብዙ አመታት ፈርሶ በማየታቸው እጅጉን ያዝኑ እንደነበረም አስተያየት ሰጥተዋል።

ቴአትር ቤቱ በፊት በነበሩት ሥራዎች የሌሎች ቴአትር ቤቶች ሥራ በሙሉ በተሻለ መልኩ የሚያቀርብና ሌሎች በከተማዋ ውስጥ የነበሩ ቴአትር ቤቶችን ወጪን በመደጎምና በመሸፈን ጭምር ለቴአትር እድገቱ ትልቅ አስተዋፅዖ የነበረው ቴአትር ቤት እንደነበር የገለፀው ድምፃዊ ፀሐዬ ዮሐንስ ነው።

«ታላቅ የሙዚቃና የቴአትር ባለሙያዎች ያፈራ እጅጉን ትልቅ አስተዋፅዖ የነበረው ቴአትር ቤት ነው፤ በመሆኑም ቤቱ የተሻለ ሆኖ ሊሠራ ይገባል፣ ቤቱ ያሳደገኝ እንደመሆኑ ብዙ ትዝታዎች አሉኝ» ያለው ድምፃዊ ፀሐዬ ዮሐንስ ከፈረሰ በኋላ በአካባቢው ማለፍ እንደማይወድና አሁን ለመሥራት መታቀዱ ጥሩ መሆኑንና መንግሥት ቃሉን ጠብቆ ግንባታውን ጀምሮ እንዲጨርሰው አደራውን አስተላልፏል።






ከራስ ቲያትር ቤት እድሳት ጎን ለጎን የመጀመሪያውን አዲስ ቴአትር ቤት ግንባታ የመሠረት ድንጋይ ተጥሏል፣

«ራስ ቴአትር ለብዙዎች የጥበብ ትምህርት ቤት ነው» ያለው ፀሐዬ፤ በአገሪቱ ውስጥ ያሉ ታላላቅ የኪነጥበብ ባለሙያዎች ያፈራ ቤት ወደፊት በተሻለ ገፅታው ማግኘት እንደሚፈልግ ተስፋውን ገልጿል። የራስ ቴአትር ባልደረቦች ለኪነጥበብ ያላቸው ፍቅርና አንድነት እጅግ የሚያስቀና እንደነበር የገለፀው ድምፃዊ ፀሐዬ ዮሐንስ ይህ አንድነትና ፍቅር ዛሬ ድረስ እንደቀጠለና ባለሙያዎቹ በተለያየ መንገድ እየተገናኙ ሥራዎችን እንደሚሠሩና ማህበራዊ ግንኙነታቸውም እንዳስቀጠሉ ይገልፃል።

አርቲስት ሙሉ ገበየሁ በበኩሉ ራስ ቴአትር ሲመሠረት ጀምሮ ቤቱን በማስተካከልና ለቴአትር ምቹ በማድረግ እንደተሳተፈ ገልጾ ቤቱ በኪነጥበብ ባለሙያ እጅጉን የገነኑና ለኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ትልቅ አበርክቶ ያላቸው ባለሙያዎች ያፈራ እንደነበር ያስታውሳል። ቤቱ ከመፍረሱ በፊት በተለያየ የኪነጥበብ ሥራዎቹ አገራዊ ጉዳይ በማንሳት ኅብረተሰቡ አንድነቱ እንዲጠነክርና አገራዊ ፍቅሩን ያዳብር ዘንድ ትልልቅ ሥራዎችን ሠርቷል።

ባለሙያዎቹም በመከባበር መንፈስ ለኪነጥበቡ እድገት በጋራ በመስራት የሚታወቁ እንደነበሩ የገለፀው አርቲስት ሙሉ ገበየሁ፤የቴአትር ቤቱ ባልደረቦች ለሥራቸው የነበራቸው ፍቅርና በጋራ የመሥራት ወኔና ሙያዊ ፍቅራቸው ለሌሎች ቴአትር ቤቶችም ጭምር አርዓያ ተደርጎ ይታይ እንደነበር ያስታውሳል።

ለአመታት ፈርሶ ያለምንም ሥራ መቆየቱ የሚያስቆጭ እንደነበረና አሁን ላይ መሠረት ተጥሎ የግንባታ ሥራው መጀመሩ በማየቱ እጅግ መደሰቱን ይገልፃል። አርቲስት ሙሉ ወደፊት እንደከዚህ በፊቱ ጉምቱ ሞያተኞች በማፍራት ለአገሪቱ ኪነጥበብ የራሱ የሆነ ጉልህ ሚና ይኖረዋል የሚል እምነት እንዳለው ያስረዳል።

የቀድሞ የራስ ቴአትር ባልደረባ የነበረው አርቲስት ኤልያስ ተባባል በበኩሉ ራስ ቴአትር ለብዙዎች የጥበብ ቤት መሆኑና በሕይወት ዘመኑ በሙዚቃ ሥራው ካሳለፋቸው ውብ ቆይታዎች የራስ ቴአትር ቤት የተለየ እንደነበርና እዚያ ብዙ ተምሮ እንደነበር ከባልደረቦቹም ጋር የነበረው ትስስር አስደናቂ መሆኑን ያነሳል።

አርቲስት እንቁስላሴ ወርቃገኘሁ በበኩሉ ቴአትር ቤቱ እጅግ በጣም ብዙ የጥበብ ባለሙያዎችን ያፈራና ለኢትዮጵያ ኪነጥበብ እድገት ውለታ የዋለ እንደነበር ጠቅሶ እሱና ባልደረቦቹ በቴአትር ቤቱ ውስጥ ለኪነጥበብ እድገት የላቀ ሥራ እንደሠሩና ቤቱ ለኪነጥበብ እድገት ጉልህ ድርሻ እንደነበረው ያስታውሳል።

አሁን ላይ በኪነጥበብ ዘርፍ የሚሳተፉ ወጣቶች ቀድሞ በራስ ቴአትር ቤት ይሳተፉ የነበሩ አርቲስቶች ሥራ ዲስፕሊን ቢከተሉና አብሮነታቸው ከዚያ ቴአትር ቤት ባለሙያዎች ቢማሩ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ገልፆ፤ በራስ ቴአትር ቤት ውስጥ በሥራ በቆየባቸው አመታት ስለጥበብ ብዙ ተምሮ ያንን ኪነጥበባዊ እውቀትና ችሎታ ለሌሎች ለማውረስ ዕድል ገጥሞት እንደነበረ ያስታውሳል።

አርቲስት ደበሽ ተመስገን በራስ ቴአትር ባልደረባነት ለአመታት ተሳትፏል። በጥበብ ቤቱ ውስጥ ኪነጥበብን ተምሮና እራሱን ለሕዝብ እንዳስተዋወቀ በዚህም ቤቱን እጅግ እንደሚወደውና ትዝታው ሁሌም አብሮት እንደሆነ ገልፆ አሁን ላይ በአዲስ መልክ ሊታነፅ መታቀዱ መስማቱ አንዳች ተስፋ በውስጡ እንደፈነጠቀና የተሻለ ተደርጎ ተሠርቶ ማየት እንደሚመኝ ገልጿል።

በራስ ቴአትር ቆይታው አብሮነትን፣ ሙያዊ ፍቅርና የአገራዊ ስሜት እንደተጋባበትና ወደፊት ቤቱ ተሠርቶ በተሻለ ገጽታና በተሻሉ የጥበብ ሥራዎች እንደሚያየው ተስፋ እንደሚያደርግ ገልጿል።

በአገር ደረጃ እድገቱ የጅማሮው ያህል እንዳልሆነ የሚነገርለት የቴአትር ዘርፍ ብዙ መሰናክሎችን እያለፈ መቆየቱና ለቴአትር ምቹ አውድ መታጣቱ እንደሆነ የዘርፉ ባለሙያዎች ደጋግመው ይገልፃሉ። ይህንን ችግር ለመቅረፍ ደግሞ በአዲስ አበባ መስተዳድር ትኩረት ተሰጥቶባቸው እየተሠሩ ያሉ ለቴአትር ጥበብ ብሎም ለአጠቃላይ ኪነጥበባዊ ጉዳይ ማደግ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥሩ ሥራዎች ተጠናክረው ሊቀጥሉ የሚገባ መሆኑን መጠቆም እንወዳለን።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## በአካል ጉዳተኞች ጉዳይ የመገናኛ ብዙሃን ሚና

ሰላማዊት ውቤ

የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ ትልቅ አገራዊ አጀንዳ ቢሆንም በመገናኛ ብዙሃን ተገቢው ሽፋን እየተሰጠው እንዳልሆነ ይነገራል። ሆኖም ከኢትዮጵያ ሕዝብ 17 በመቶው በሰው ሰራሽ አደጋም ሆነ በተፈጥሮ አካሉ የተጎዱ እንደሆነ ጥናቶች ይጠቁማሉ። የትምህርት፤ የጤና፤ የሥራ ዕድልና የሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዳልሆኑም ጥናቶቹ ያመላክታሉ።

በቅርቡ የአዲስ አበባ ሴቶች ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ባዘጋጀው የምክክር መድረክ የአዲስ አበባ ሴቶች ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ከፍተኛ ባለሙያ አቶ አሉላ ሲሳይ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ እንደገለፁት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ያሉ አካል ጉዳተኞች አብዛኞቹ ያሉት ከ19 እስከ 59 ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ ነው። ከነዚህ ውስጥ አብዛኞቹ የትምህርት ተሳትፏቸው ዝቅተኛ ሲሆን 44 በመቶዎች ጭራሽ ምንም ዓይነት የትምህርት ዕድል አላገኙም። 89 በመቶው እስካሁን ምንም ዓይነት የገቢ ማስገኛ ሥራ እንደሌላቸውና የሰው ሰራሽ አካል ድጋፍ አለማግኘታቸው በጥናቱ ታይቷል። ከመሰረታዊ ማህበራዊ ጉዳዮች ተጠቃሚነት አንፃር ሲቃኝም በትምህርት፤ በጤና፤ በትራንስፖርት ያላቸው ተሳትፎ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ ተቃኝቷል።

ችግሩን መንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በስፋት ገብተው የሚቀርፉበት ሁኔታ መመቻቸቱን አቶ አሉላ መግለፃቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የቺሻየር ፋውንዴሽን የአዲስ አበባ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ፕሮግራም አስተባባሪ አቶ ፀጋዬ ዘለቀ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ ይሄንኑ ነው የተናገሩት። እሳቸው እንደሚሉት መገናኛ ብዙሃን ተፅዕኖ ፈጣሪ እንደመሆናቸው መጠን በአካል ጉዳተኞች አካቶ ልማት ትግበራ ወይም ሁለንተናዊ ተሳታፊና ተጠቃሚነት ላይ ለውጥ ማምጣት ከተፈለገ በተገቢው መንገድ መሰራት አለበት። መስኩ 17 በመቶ በሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ላይ የሚሰራ መሆኑንም ማጤን ይኖርበታል።



‹‹እነዚህ የሕብረተሰብ ክፍሎች በተለይ ልማት ተሳትፎ ውስጥ በቸልታ ሊታዩ አይገባም›› ይላሉ አቶ ዘለቀ። የመገናኛ ብዙሃኑ ባለሙያ ይሄን ተገንዝቦ ከዚህ ቀደም ሲሰራበት ከነበረው በበለጠ ሁኔታ በኢትዮጵያ ልማት እንቅስቃሴ ውስጥ የአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ ጎልቶ እንዲወጣ መሥራት እንደሚጠበቅበትም ያስገነዝባሉ። የአካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም የሕብረተሰብ ክፍል የጤና፤ የትምህርት፣ የሥራ ዕድልና የሌሎች የልማት ጥያቄዎች አሏቸው እነዚህን ጥያቄዎቻቸውን አጉልተው ማውጣት የመገናኛ ብዙሃኑ ሚና ሊሆን ይገባል።

ሕብረተሰቡም ሆነ ተቋማት አካል ጉዳተኛ ላይ ያላቸውን አመለካከት በጥሩ መልኩ እንዲቃኝ የማድረግ ሥራ ከመገናኛ ብዙሃን ይጠበቃል ሲል የተናገረው ደግሞ በምክክር መድረኩ የአካል ጉዳተኞች አካቶ ትግበራ የሚዲያው ሚና ምን መሆን እንዳለበት የሚያመላክት የዳሰሳ ጥናት ያቀረበው የአዲስ ሚዲያ ኔትወርክ ጋዜጠኛና የመረጃና ግንዛቤ ስነ አካል ጉዳተኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ዮሴፍ ኃይለማርያም ነው።

እንደ ጋዜጠኛው ጉዳያቸው ከ10 ደቂቃ የአየር ሰዓት ጀምሮ እስከ 30 ደቂቃ ብሎም እስከ አንድ ሰዓት አድጎ በመገናኛ ብዙሃን ሽፋን ማግኘት መቻሉ ይበረታታል። ሆኖም ትልቁ በሚባለው አንድ ሰዓት የሚሰሩት የግል መገናኛ ብዙሃን ናቸው። የመንግስት መገናኛ ብዙሃን ሥራውን የሚሰራው በጨኻት ነው። አካል ጉዳተኛ ያልሆነው ጋዜጠኛ የሴቶች ፤የሕግ የህፃናት፤ የኢኮኖሚ ፤የትምህርት ተብሎ ፕሮግራም እንደሚሰራው የአካል ጉዳተኛን አለመሥራቱ የአመለካከት ችግር መኖሩን ያመለክታል።

‹አስፈፃሚ አካላት እንዴት አካል ጉዳተኞችን አካተው መሥራት እንዳለባቸው በሕግ ተቀምጧል› የሚለው ዮሴፍ አንድ ፕሮግራም ሲሰራ፤ ሲታቀድ አካል ጉዳተኛውን ታሳቢ የማድረግ ግዴታ ሊኖር ይገባል ይላል ጋዜጠኛ ዮሴፍ። ጋዜጠኛው ለአካል ጉዳተኛ መረጃ እንዴት እንደሚያደርስና ስለ አካል ጉዳተኛው መብት እንዴት እንደሚያወራም በህግ አግባብ የተቀመጠ ቢሆንም እስካሁን ወደ መሬት አውርደው እየሰሩበት ያለው ጥቂቶች ናቸው።

አካል ጉዳተኞች 17 በመቶ የአገሪቱን ዜጎች ቁጥር ሽፋን የያዙ ናቸው። በአገሪቱ ልማት በተለይ በዋና ከተማዋ አዲስ አበባ ያላቸው ተሳትፎ ምን መሆን እንዳለበት አሳይ ፤አስነብብ፤ አስደምጥ ፤አሳውቅ ፤ይላል። ብቻም ሳይሆን ይሄን መሰረት አድርጎ መረጃን ለአካል ጉዳተኛው፤ ለመንግስት የሥራ ኃላፊ፤ አካል ጉዳተኛ ላልሆነው ሕብረተሰብ ንገር እንደሚልም ያክላል።

ሆኖም መገናኛ ብዙሃኑ ይሄን መተግበሩ ላይ ገና የሚቀሩ ብዙ ክፍተቶች እንዳሉባቸውም ጋዜጠኛ ዩሴፍ ይጠቁማል። እንደጋዜጠኛው ቋንቋ አጠቃቀም ላይም ችግር አለ። አካል ጉዳተኛውን አካለ ስንኩል ወይም ጎዶሎ ብለው የሚጠሩ ጋዜጠኞች እንዳጋጠሙት ዮሴፍ ያስረዳል። እንዲሁም አካሉ የጎደለና ያልጎደለ የሕብረተሰብ ክፍል በንጽጽር ሲያስቀምጡ አካሉ ያልጎደለውን ጤነኛው ብሎ የማሰብ የአካል ጉዳት ያለበትን ደግሞ በሽተኛ ብሎ የማሰብ አባዜ እንዳለ ዮሴፍ ያብራራል።

ይሄን ዓይነቱ የተዛባ አተያይ በበርካታ ጋዜጠኞች ዘንድ እንደሚንጸባረቅና ሊስተካከልም እንደሚገባ በውይይት መድረኩ ላይ ግንዛቤ ተይዞበታል።

አቶ መኮንን ማናየ ይባላሉ። የዊይማ (WEEMA) ኢንተርናሽናል የትምህርትና የማህበራዊ አካታችነት ፕሮግራም ማናጀር ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት አካል ጉዳተኞች በትምህርትም ሆነ በሌሎች ጉዳዮች በስፋት ተሳታፍና ተጠቃሚ አይደሉም።

ተጠቃሚ አለመሆናቸውና ተጠቃሚ መሆናቸውን ሕብረተሰቡም ሆነ ራሳቸው የሚገነዘቡት በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ነው። ሆኖም አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ በማድረጉ በኩል መገናኛ ብዙሃን ክፍተት አለበት። ለማሳያ እንደጠቀሱትም ህትመት ዘርፉ ላይ የሚወጡትን ጽሑፎች ዓይነ ስውራን አያነቧቸውም። እንዲሁ በሬዴዮ የሚተላለፈውን መስማት የተሳናቸው አይከታተሉትም።

በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች በተለይ በአዲስ አበባ የሚመረቁ ፕሮጀክቶች አካል ጉዳተኛውን ያካተቱ መሆን አለመሆናቸውን የተመለከተ ሽፋን መስጠት አለባቸው። እኛም መንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አካል ጉዳተኞችን ተሳታፊና ተጠቃሚ በማድረጉ፤ መገናኛ ብዙሃን ደግሞ ይሄን በማስተጋባቱና በመፈተሹ ረገድ ከፍተኛ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን መገንዘብ ይገባል አልን።

# ዓለም አቀፍ



## በሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር የተጠረጠሩ 130 ሰዎች አውሮፓ ተያዙ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የአውሮፓ አገራት ጥምር ፖሊስ ኃይል /ዩሮፖል/ ባካሄደው መጠነ ሰፊ ዘመቻ በሰዎች ሕገ-ወጥ ዝውውር ተሳታፊ ሳይሆኑ አይቀሩም የተባሉ 130 ሰዎችን በቁጥጥር ሥር ማዋሉ ተገለጸ።

በዘመቻው ከ22 አገራት የተወጣጡ 22 ሺህ 500 ሕግ አስከባሪ አካላት ተሳታፊ እንደነበሩ ሮይተርስ የዜና ወኪል የአውሮፓ የፖሊስ ተቋም ዩሮፖልን ጠቅሶ ዘግቧል።

በዚህ ኦፕሬሽን ተሳታፊ ከነበሩ አገራት መካከል ቦስኒያ እና ሄርዜጎቪና፣ ሞንቴኔግሮ፣ ሰሜን መቄዶንያ፣ ሰርቢያ፣ ዩክሬን እና ብሪታኒያ ተጠቃሽ ናቸው።

በአውሮፓ ኅብረት የድንበር ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ፍሮቴክ የተመራው ጥምር የፖሊስ ኃይል ባደረገው ዘመቻ በሰዎች ዝውውር ከተጠረጠሩት በተጨማሪ፣ በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ተጎጂ ሳይሆኑ አይቀሩም የተባሉ ከ100 በላይ ተጎጂዎች መለየታቸው ተገልጿል።

ፖሊስ በተለያዩ አገራት ድንበር ላይ ባደረገው ክትትል በመቶዎች የሚቆጠሩ ሐሰተኛ የጉዞ ሰነዶችን መያዙን አሳውቋል።

በዚህ ኦፕሬሽን አንድ ሚሊዮን ሰዎች ላይ ምርመራ የተደረገ ሲሆን፤ ከፍተኛ የሰዎች ሕገ-ወጥ የሰው ዝውውር ይካሄድባቸዋል በተባሉ የድንበር አካባቢዎች ላይ በ200 ሺህ ተሽከርካሪዎች ላይ ምርመራም መደረጉም ታውቋል።

አውሮፓ ከተለያዩ አህጉራት ጥቃቶችን በመሸሽ እንዲሁም የተሻለ ሕይወትን ፍለጋ ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ሰዎች የሚሰደዱባት አህጉር ናት።

በየብስና በባሕር በሚደረጉ ሕገ ወጥ ጉዞዎች አማካይነት ወደ ተለያዩ የአውሮፓ አገራት ለመግባት በሚደረገው ጥረት ውስጥ የበርካታ ሰዎች ሕይወት ሲጠፋ ቆይቷል።

እነዚህ ጉዞዎች በአብዛኛው የሚካሄዱት በሕገ ወጥ የሰዎች አዘዋዋሪ ግለሰቦችና ቡድኖች አማካይነት በመሆኑ፣ የአውሮፓ አገራት ትኩረታቸውን በእነሱ ላይ አድርገዋል።

በዚህም በተለያዩ ጊዜያት በአፍሪካ እና በሌሎች አገራት ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ሕገ ወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎችን የአውሮፓ ፖሊስ ከዓለም አቀፉ የፖሊስ ተቋም ኢንተር ፖል ጋር በመሆን ሲያድኑ ቆይተዋል።

## ቦሪስ ጆንሰን ሁለት የካቢኔ አባሎቻቸው ሥራ በመልቀቃቸው ጫናው በርትቶባቸዋል

በጋዜጣው ሪፖርተር



የዩናይትድ ኪንግድም ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን ከፍተኛ ባለሥልጣኖቻቸው አስተዳደራቸውን ተችተው ሥራ መልቀቃቸውን ተከትሎ ከፍተኛ ጫና ውስጥ ገብተዋል።

የገንዘብ ሚኒስትር ሪሺ ሱናክ እና የጤና ሚኒስትር የነበሩት ሳጂድ ጃቪድ በ10 ደቂቃ ልዩነት ሥራቸውን በገዛ ፍቃዳቸው መልቀቃቸውን አስታውቀዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን ተቺዎች የጠቅላይ ሚኒስትሩ የፖለቲካ ሕይወት “አብቅቶለታል” ያሉ ሲሆን ሌበር ፓርቲ በበኩሉ የቦሪስ ጆንሰን አስተዳደር በብልሹ አሰራር የተሞላ ነው ሲል አስታውቋል።

በብዙ ውጣ ውረዶች ውስጥ እያለፉ የሚገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን ትናንትና ከምክር ቤት አባላት ለሚነሱት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በፓርላማ ቀርበዋል።

ከጥቂት ሳምንታት በፊት የመተማመኛ ድምጽ የተሰጠባቸው ቦሪስ ጆንሰን፤ ምንም እንኳ ተቃውሞ ቢበዛባቸውም በሥልጣናቸው እንደሚቆዩ ገልጸዋል።

ሥልጣናቸውን በገዛ ፍቃዳቸው በለቀቁት ሁለቱ የካቢኔ አባላት ምትክም ሌሎች ፖለቲከኞችን ሾመዋል።

የጤና ሚኒስትር የነበሩት ሳጂድ ጃቪድ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አስተዳደር ብሔራዊ ጥቅምን ባማከል ሁኔታ አገር እየመራ አይደለም ሲሉ፤ የገንዘብ ሚኒስትር ሪሺ ሱናክ ሕዝቡ መንግሥት አገሪቱን በአግባቡ እንዲያገለግል ይጠብቃል ብለዋል።

የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች የቦሪስ ጆንሰን ካቢኔ አባላት ሁለቱን ግለሰቦች በመከተል ከሥልጣናቸው እንዲወርዱ እየጠየቁ ይገኛሉ።

ወግ አጥባቂው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል አንድር ሚሼል የቦሪስ ጆንሰን ጉዳይ “አብቅቶለታል” ሲሉ ለቢቢሲ ተናግረዋል።

ምንም እንኳ የምክር ቤት አባሉ ይህን ይበሉ እንጂ፣ አሁንም በርካታ ተጽእኖ ፈጣሪ የሆኑ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የካቢኔ አባላት ድጋፋቸውን ለቦሪስ ጆንሰን እንደሰጡ ናቸው።

ከእነዚህም መካከል ቦሪስ ጆንሰንን በመተካትሊቀጥሉ ይችላሉ የተባለላቸውና የወግ አጥባቂ ፓርቲ መሪ የመሆን ዕድል አላቸው የሚባሉት የውጭ ጉዳይ ሚኒሰትሯ ሊዝ ትረስ ይገኙበታል። ሚንስትሯ፤ መቶ በመቶ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ድጋፌን እስጣለሁ ብለዋል።

ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯ በተጨማሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ዶሞኒክ ራብ እና መከላከያ ትኒስትሩ ቤን ዋላስ በሥራቸው እንደሚቀጥሉ በመግለጽ ከስልጣን ገሸሽ ማለትን ለችግሮች መፍትሄ እንደማይሆን የሚያሳስብ መልዕክት አስተላልፈዋል።

አዲስ ዘመን
ሐሙስ ስፖርት



ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ኢትዮጵያ የመጨረሻውን የዓለም ቻምፒዮና ቡድን አሳውቃለች

ብርሃን ፈይሳ

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በኦሪጎን የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ተሳታፊ የሚሆነውን የመጨረሻውንና ጠንካራውን ብሔራዊ ቡድኑን አሳውቋል። ቡድኑ ከዚህ ቀደም ከነበረው መጠነኛ ልዩነት የታየበትም ነው።

ከጥቂት ቀናት በኋላ በአሜሪካዋ ኦሪጎን የሚካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ተሳታፊ የሚሆኑ አገራት ዝግጅታቸውን በማጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ። በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በተካሄደው የሰዓት ማሟያ መሠረትም በዕጩነት የተያዙ አትሌቶች ልምምዳቸውን ሲያደርጉ ቆይቷል። አሁን ደግሞ የመጨረሻዎቹንና በቻምፒዮናው ላይ አገርን የሚወክሉ አትሌቶችን ማንነት ፌዴሬሽኑ ይፋ አድርጓል። ቡድኑ በሁለቱም ጾታ ከ800 ሜትር እስከ ማራቶን ድረስ ከነተጠባባቂዎቻቸው 47 አትሌቶችን በመያዝ ወደ አሜሪካ የሚያቀና ይሆናል።

ፌዴሬሽኑ ከዚህ ቀደም ካሳወቃቸው የቡድኑ አባላት የሚሳተፉባቸው ርቀቶች ላይ ወቅታዊ አቋማቸውን ተከትሎ መጠነኛ ማስተካከያዎችን ማድረጉም ታውቋል። በዚህም መሠረት በሴቶች 1ሺ500 ሜትር ሴቶች የዶሃው ዓለም ቻምፒዮና የነሐስ ሜዳሊያ ባለቤቷ ጉዳፍ ጸጋይ የሚመራ ይሆናል። አትሌቷ በ5ሺ ሜትርም በተጠባባቂነት ተይዛለች። ሌላኛዋ ጠንካራ አትሌትና በዶሃው የዓለም ቻምፒዮና እንዲሁም በቶኪዮ ማራቶን 10ሺ ሜትር የብር እና ነሐስ ሜዳሊያ ባለቤቷ ለተሰንበት ግደይም በ5ሺ እና 10ሺ ሜትር ርቀቶች እንደምትሮጥ ተረጋግጧል።

በተመሳሳይ በወንዶች በኩል ወጣቶቹ አትሌቶች ሰለሞን ባረጋ እና በሪሁ አረጋዊ በ5ሺ እና 10ሺ ሜትር አገራቸውን እንደሚወክሉ ታውቋል። የቶኪዮ ኦሊምፒክ የ10ሺ ሜትሩ ቻምፒዮን እንዲሁም የዶሃው የዓለም ቻምፒዮና 5ሺ ሜትር ባለብር ሜዳሊያው ሰለሞን አሁን ካለበት ወቅታዊ አቋም አንጻር በሁለቱም ርቀቶች የሜዳሊያ ባለቤት የሚሆንበት ዕድል የሰፋ እንደሚሆን ይጠበቃል። በቡድን ሥራ እና ለአገሩ ልጆች ምቹ ሁኔታን በማመቻቸት ተመስጋኝ የሆነው አትሌት በሪሁ አረጋዊም በቻምፒዮናው ከፍተኛ ሚናን ከመወጣት ባለፈ የሜዳሊያ ሰንጠረዡ ከሚጠበቁ አትሌቶች መካከል ይካተታል።

ኢትዮጵያ ውጤታማ ከሆነችባቸው ርቀቶች መካከል አንዱ በሆነው ማራቶንም የመጨረሻዎቹ ዕጩዎች ታውቀዋል። በዚህም መሠረት በወንዶች የዓለም ቻምፒዮናው ሌሊሳ ዴሲሳ፣ የለንደን ዓለም ቻምፒዮና የብር ሜዳሊያ ባለቤቱ ታምራት ቶላ እንዲሁም በዶሃ ዓለም ቻምፒዮና የብር ሜዳሊያ ያጠለቀው ሞስነት ገረመው እንደሚሮጡ ታውቋል። በሴቶች በኩል ደግሞ ጎይቶም

# ዋልያዎቹ ለቻን ቅድመ ማጣሪያ ዝግጅት ተጠሩ

ብርሃን ፈይሳ

በቻን ዋንጫ ተሳታፊ የሚሆኑ ቡድኖች የሚለዩበት ማጣሪያ ከመካሄዱ አስቀድሞ የሚደረገው የቅድመ ማጣሪያ ጨዋታ በሐምሌ ወር አጋማሽ ይጀመራል። በቅድመ ማጣሪያው ላይ ተሳታፊ የሚሆነው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን(ዋልያዎቹም) ጥሪ ተደርጎላቸዋል።

ለሰባተኛ ጊዜ በአልጄሪያ አዘጋጅነት የሚካሄደው የቻን ዋንጫ በቀጣዩ የፈረንጆች ዓመት የመጀመሪያ ወር ይጀመራል። በአገር ውስጥ ሊጎች ብቻ የሚሳተፉ የእግር ኳስ ተጫዋቾች የሚካፈሉበት የዚህ ውድድር የማጣሪያ ጨዋታዎችም በሐምሌ ወር 2014ዓ.ም አጋማሽ መካሄድ ይጀመራሉ። የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) በበላይነት የሚመራው ይህ ውድድር 18 ቡድኖችን ያሳትፋል።

በዚህ ውድድር ተሳታፊ ለመሆን የሚችለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድንም (ዋልያዎቹ) ጥሪ ተደርጎላቸዋል። ሐምሌ 14 እና 24/2014 ዓ.ም ታንዛኒያ ላይ ለሚደረጉት ጨዋታዎች የዋልያዎቹ አሠልጣኝ ውበቱ አባተ ለ23 ተጫዋቾች ጥሪ ማስተላለፋቸውን የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን አሳውቋል። ዋልያዎቹ የመጀመሪያ ጨዋታቸውን ከደቡብ ሱዳን አቻው ጋር የሚያደርግ ሲሆን፤ ቅድመ ዝግጅቱን ለማድረግም ከሐምሌ 4/2014ዓ.ም ጀምሮ አባላቱ እንደሚሰባሰቡም ፌዴሬሽኑ አመላክቷል።

በአሰልጣኝ ውበቱ አባተ ምርጫ መሠረትም ግብ ጠባቂዎች፤ ፋሲል ገብረሚካኤል፣ በረከት አማረ እና አላዛር ማርቆስ ጥሪ ተደርጎላቸዋል። ተከላካዮችም ሱሌማን ሀሚድ፣ ሄኖክ አዱኛ፣ ጊት ጋትኩት፣ ያሬድ ባየህ፣ ሚሊዮን ሰለሞን፣ ምኞት ደበበ፣ አስራት ቱንጆ እና ረመዳን የሱፍ ናቸው። በአማካዮች በኩል አማኑኤል ዮሐንስ፣ ጋቶች ፓኖም፣ ከነአን ማርከነህ፣ ቸርነት ጉግሳ፣ ሱራፌል ዳኛቸው፣ በዛብህ መለዮ እና መስኡድ መሀመድ ተጠርተዋል። አማኑኤል ገብረሚካኤል፣ ዳዋ ሁጤሳ፣ ብሩክ በየነ፣ በረከት ደስታ እና ይገዙ ቦጋለ ለአጥቂነት ጥሪ የተደረገላቸው ተጫዋቾች ናቸው።

## ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የምግብ ጥራትና ደህንነትን የማረጋገጥ ተግባር በሞጆ ደረቅ ወደብ

ታምራት ተስፋዬ

የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 1112 /2011 ኢ.ም በተሰጠው ስልጣን መሠረት አገር ውስጥ የሚመረቱና ከውጭ የሚገቡ ምግብ መድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች ጥራት፣ ደህንነት፣ ፈዋሽነት ያረጋግጣል። በዚህም ኅብረተሰቡን ጥራት፣ ደህንነትን ብቃቱ ካልተጠበቀ ምግብና መድኃኒት ይከላከላል።

ይህን ኃላፊነቱን ለመወጣትም በዋና መስሪያ ቤትም ሆነ በቅርንጫፎች ጣቢያዎቹ የተደራጁ የተለያዩ የቁጥጥር ክፍሎች አሉት። እንደ ባለስልጣን መስሪያ ቤት በአገሪቱ የተለያዩ ክልሎች ሰባት ቅርንጫፎች አሉት። የማዕከላዊ ቅርንጫፍም ከእነዚህ አንዱ ነው።

በማዕከላዊ ቅርንጫፍ በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙ አምስት መግቢያ መውጫዎች አሉ። በኢትዮጵያ አየር መንገድ ካርጎና በመንገደኞች አገልግሎት ሁለት ቅርንጫፍ ቢሮ አለ። ቃሊቲ ወደብና ተርሚናል፣ በአዳማ እንዲሁም በሞጆ ወደብና ተርሚናል ቢሮዎች አሉት።

አቶ ግዛው ካሳ በኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን የሞጆ ደረቅ ወደብ መግቢያና መውጫ ጣቢያ የምግብ ኤክስፐርት ናቸው። በእነዚህ መግቢያ መውጫ ቁጥጥር ጣቢያ የምግብ ደህንነትን በማረጋገጥ ረገድ ምን እንደሚከናወን፣ በዘንድሮው በጀት አመት ያለፉት አስራ አንድ ወራት አፈጻፀም በሚመለከት ቆይታ አድርገናል።

አቶ ግዛው እንደሚገልጹት፣ ተቋሙ ቁጥጥር የሚያደርግባቸው ምርቶች መግቢያ መውጫዎች ላይ ሲደርሱ የጥራት፣ የደህንነት፣ ፈዋሽነት እና ብቃት ደረጃቸው ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋል። ምርቶች ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ሲገቡም ሆነ ከአገር ወደ ውጭ ሲወጡ መሟላት ያለባቸው ከደህንነት ከጥራት፣ ከብቃት አንጻር የተለያዩ መስፈርቶች አሉ። ባለስልጣኑም በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሠረት ይህን የማረጋገጥ ሥራ ይሠራል።

በህጋዊ መንገድ ማረጋገጫ አግኝተው ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶችን በሚመለከት የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላት አለማሟላታቸውን ይፈትሻል። ያረጋግጣል። መስፈርቱን የሚያሟሉትን ወደ አገር እንዲገቡ ፈቃድ ይሠጣል። የማያሟሉት ደግሞ እንዳይገቡ ክልከላ ያደርጋል።

የምግብን ጥራት ደህንነት ማረጋገጥ ረገድ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች አሉ። አንድ አስመጪ ወደ አገር ውስጥ ምግብ ከማስገባቱ አስቀድሞ የሚያቀርባቸው ሰነዶች አሉ። ከባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተሰጠ የምግብ አስመጪነት የብቃት ማረጋገጫ እንዳለው ይታያል። የሚገቡት ምርቶች በባለስልጣኑ የምግብ ፈቃድ ዳይሬክቶሬት መመዝገብ አለባቸው። ለዚህ የሚሠጥ የገበያ ፈቃድ ሰርተፍኬት ማግኘት አለበት። ከዚህ ባሻገር የጤና ሰርተፍኬት ማቅረብ ግድ ይላቸዋል።

እነዚህን አሟልቶ የመጣ አካል ‹‹ይፈተሽልኝ›› ሲል አገልግሎት ይጠይቃል። ከዚህ በኋላ ምግቡን የሚያመርተው አካል ማነው በምን ዓይነት መልኩ ጥራትና ደህንነቱን ይጠብቃል የሚለው ይቃኛል። በአስመጪው በኩል ለተቋሙ የሚቀርቡ መረጃዎች ይገመገማል። ምግቡ በባለስልጣኑ እውቅና እንደተሰጠው ይታያል። ከዚህ ባሻገር ምግቡ አሟልቷል በሚል በተቀመጠው መዘርዝር ነው የቀረበው የሚለው በባለሙያዎች በጥንቃቄ ይፈተሻል። ይመሳከራል። እነዚህ መሟላታቸው ሲረጋገጥ ናሙና በመውሰድ ወደ አካላዊ ፍተሻ ሂደት ይገባል።

አቶ ግዛው እንደሚገልፁት፣ በዚህ ሂደት የአስተሻሸግና ገላጭ ጽሑፍ ረገድ የተቀመጡ መስፈርቶች አሉ። የመጠቀሚያ ጊዜ፣ ምግቡን የሚመገብ ማድረግ ያለብን ጥንቃቄ፣ ምግቡ ከምን ከምን እንደተሰራ መግለፅን ጨምሮ የተለያዩ መስፈርቶች ተቀምጠዋል። እነዚህ መስፈርቶች መሟላታቸው መግቢያ መውጫ ላይ ይፈተሻል። ይረጋገጣል።

አንድ ምግብ መግቢያ መውጫው ኬላ የሚደርሰው በተለያዩ የትራንስፖርት አማራጮች ተጓጉዞ ነው። በጉዞ ወይንም በአቀማመጥ ወቅት ምግቡ ብልሽት ሊያጋጥመው ይችላል። መግቢያ መውጫ ላይም ምግቡ በአግባቡ መጓጓዙን እንዲሁም መቀመጡ ይፈተሻል። ይረጋገጣል።



አቶ ግዛው ካሳ

የተቀመጡ መስፈርቶችን መሟላታቸው ሲረጋገጥ አንድ ምርት ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ፈቃድ ያገኛል። የማያሟላ ምግብ ከሆነ ደግሞ ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ ወይንም እንዲወገድ ይደረጋል። በዚህ መልክ ቁጥጥር የሚደረግባቸው የምግብ ምርቶች ህጋዊ አስመጪ ኖራቸው በህጋዊ መንገድ ቀረጥ ተከፍሎባቸው መንግሥት አውቋቸው የሚገቡ ናቸው።

አቶ ግዛው እንደሚያስረዱት፣ በሞጆ መውጫ መግቢያ ጣቢያ፣ መስፈርት የማያሟሉ ምርቶች የሚያጋጥሙበት ጊዜ አለ። ለአብነት የጤና ሰርተፍኬት ማቅረብ ሲገባቸው ሳይዙ የሚመጡ ይስተዋላሉ። የመጠቀሚያ ጊዜ የተቃረበ ወይንም ያለፈባቸውና አካላዊ ጉዳት በተለይም ከአጓጓዝ ጋር በተገናኘ እንዲሁም የገላጭ ጽሑፍና አስተሻሸግ ችግር ያለባቸው ምርቶች ይመጣሉ። ይህ ሲሆን ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ ወይንም እንዲወገድ ይደረጋል።

በዚህ የቁጥጥር ሂደትም ባለፉት አስራ አንድ ወራት የተለያዩ ምርቶች የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላታቸው ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ ገብተዋል። በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ 158 ሺ 968 ነጥብ 9 1 ሜትሪክ ቶን ምግብ ወደ አገር ውስጥ ገብቷል።

ከዚህ ውስጥ አንድ ሺ 591 ነጥብ 11 ሜትሪክ ቶን የሚሆነው የሕፃናት ምግብ ሲሆን 45ሺ 89 ነጥብ 86 ሜትሪክ ቶን የሚሆነው አጠቃላይ ምግቦች የሚባሉ ናቸው። ሰባት ሺ 996 ነጥብ 68 ሜትሪክ ቶን የሚሆነው ማጣፈጫን ጨምሮ የምግብ ጭማሬዎች ሲሆን ፣103 ሺ 965 ነጥብ 37 ሜትሪክ ቶን የሚሆነው ደግሞ የምግብ ጥሬ እቃ ነው። 159 ሺ ነጥብ 93 ሜትሪክ ቶን የምግብ ጨው እንዲሁም 165 ሺ ነጥብ 96 ሜትሪክ ቶን ተጨማሪ ምግቦች ወደ አገር ውስጥ ገብተዋል።

ይህን ያሕል መጠን ምግብ ወደ አገር ውስጥ ከማስገባት ባሻገር ጥራትና ደህንነት መስፈርት ባለማሟላት ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ፣ ገብቶም እንዳይሰራጭ የተደረጉም አሉ። በዚህ ሂደት 576 ነጥብ 665 ሜትሪክ ቶን የሚሆን ምግብ መስፈርቱን ባለማሟላት ወደ አገር እንዳይገባ ተደርጓል። በዚህም በበጀት አመቱ የምግብን ደህንነት ከማስጠበቅ አንስቶ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ምርቶች ወደ አገር በማስገባትና የማያሟሉትን ከማስመለስ ረገድ ስኬታማ ተግባራት ተከናውናዋል።

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482
http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ